# ምዕራፍ ስምንት

## የራስ ዐሊና የደጃች ውቤ ጦርነት

በራስ ዐሊ የምስፍንና ዘመን በሸዋ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ፥
በጐጃምና በዳሞት ደጃች ጐሹና ደጃች ብሩ ፥ በደምቢያ ደጃች
ክንፉ ፥ በስሜንና በትግሬ ደጃች ውቤ ከቀድሞ ዠምሮ የየግል
አውራጃቻቸውን ያስተዳድራሉ ። ከነዚህ ውስጥ ዋናው የመንግ
ሥት እንደራሴ ራስ ዐሊ ፥ በግዛትና በሥልጣን ይጣሉ የነበሩት
ከደጃች ውቤ ጋር ነበር ። ራስ ዐሊ ዋና የመንግሥቱ እንደራሴ
እንደ መሆናቸው መጠን ከነራስ ማርዬ ዠምሮ የተላለፈ የወሎ ፥
የየጁ ፥ የራያና ያዘቦ ፥ ይልቁንም የበጌምድር የተደራጀ ደንበኛ
የጦር ሠራዊት ነበራቸው ። ደጃች ውቤ ደግሞ ፥ በበኩላቸው
ካባት ግዛታቸው ከስሜን ያዘጋጁት ጦር አዲስ ከሚገዙት የ44
ነጋሪት አገር ከሚሆነው ከትግሬና ከሐማሴን የሰበሰቡት ጦር
የሚያኮራቸው ነው ። ይልቁንም በናይብ ግዛት ፥ በአርኪቆ (ደሆኖ)
እና በምጥዋ በኩል ባሸከራቸው በብላታ ኮከቤ አማካይነት
ከቱርኩ ባሻ ወኪል ከናይብ ግንኙነት እያደረጉ የጦር መሣሪያና
ሽቀጥ ስለሚያገኙ ፥ በሀብትም በጦር መሣሪያና በወታደርም
በኩል ስለ ደረጁ ፥ የራስ ዐሊን ሥልጣን ለመቃወም ብርቱ ባላጋራ
ሆነው ነበር ።

ከራስ ወልደ ሥላሴና ከትልቁ ራስ ዐሊ ዠምሮ ትግሬዎ
ቹም ፥ አማሮቹም የቤሩ ጓንጉልን ወገኖች ኦሮሞዎችን ከጐንደር
ሥልጣን አሶጥተው ለመያዝ የሚያደርጉትን የጦርነት ክርክር
ርሳቸው በዘመናቸው እፍጻሜ ለማድረስ ሙሉ ተስፋ ነበራቸው ።
ነገር ግን ፥ ይህ ምኞታቸው በትልቅ ጦርነትና በመጨረሻም
በድል አድራጊነት እስኪረጋገጥ ድረስ ለራስ ዐሊ እንደ ታዛዥ
እየገበሩ ፥ እንደ ዘመድም ልጃቸውን ወይዘሮ ሂሩትን ድረው
የወዳጅነትና የመተማመን መልክ እያሳዩ ቆዩ ። በሌላው ወገን
ደግሞ ፥ የጐንደርን እንደራሴነት ለመቀማት የሚችሉበትን

ዘዴ ማዘጋጀታቸውን ይቀጥሉ ነበር ። እንዲያውም አሳባቸው
በእንደራሴነት ብቻ ሳይወሰን ዘውድ ጭነው ንጉሠ ነገሥት ለመ
ሆን ምኞት ስለ ነበራቸው ፥ ባለፈው እንዳነበብነው አለቃ ሀብተ
ሥላሴን ወደ እስክንድርያ ልከው አቡነ ሰላማን አስመጡ ።
የሚነግሡበትንም የደረስጌ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ሺምፐር
ዊልሄም በሚባል የውጭ አገር መሐንዲስ መሪነት ባማረ ሥራ
አሠሩ ።

ይሁን እንጂ ፥ ይህ ሁሉ ሥራና ምኞት ከራስ ዐሊ ዦሮና
ማስተዋል ሊያመልጥ አልቻለም ። ቢሆንም የሚስታቸውን
አባት በዚህ ላይ የበቃ ምክንያት ሳያገኙ በግንጋኔ ራስ ዐሊ
ደጃች ውቤን ሊወጉ አልፈለጉም ። ስለዚህ በበኩላቸው የጦር
ወታደራቸውንና መሣሪያቸውን ብቻ እያደራጁ ፥ ሁሉም በው
ስጥ እየተጠራጠሩ ላዩን እየተዛመዱ ኑሯቸውን ቀጠሉ ። በመጨ
ረሻ ደጃች ውቤ ኃይላቸውን ሲተማመኑ ፥ ጦርነቱን ለመጀመር
ምክንያት በመፈለግ የተለመደውን ግብር ከለከሉ ። ልጅንም
ሂሩትን ላክልኝ ብለው ወደ ራስ ዐሊ መልእክት ላኩ ፤ ራስ ዐሊም
አልክም ብለው መልስ ሰጡ ። በዚህ መካከል ራስ ዐሊ የደጃች
ውቤን ወገኖች እነ ደጃች መርሶንና ከትግሬ ባላባቶችም ውስጥ
ለማስከዳት ይሞሩ ዠመር ።

ደጃች ውቤ ደግሞ ፥ ከራስ ዐሊ ጋራ ያሉትን የጐጃሙን ገዥ
ደጃች ጐሹን ከራስ ዐሊ ነጥለው ወደ ራሳቸው ለመሳብ ተጣ
ጣሩ ። «ከራስ ዐሊ ተለይተህ ወደኔ ብትመጣ ልጄን ሂሩትን
ከራስ ዐሊ ነጥቄ ላንተ ነው የምድራት ። ከቤጌምድርም ግዛት
በያዝኸው በጐጃም ላይ ትጨምራለህ» እያሉ በመልክት ያባብ
ሏቸው ዠመር ። ከብዙ ማባበልም በኋላ ደጃች ጐሹ ልባቸውን
ወደ ደጃች ውቤ ፥ ሰውነታቸውን ከራስ ዐሊ ጋራ አድርገው
ብዙ ቀን በማመንታት ሰነበቱ ። የእቴጌ መነን ባለቤት የነበሩት
ንጉሡ ዐፄ ዮሐንስም በራስ ዐሊና በናታቸው በእቴጌ መነን
ሥልጣን ብዛት ፥ በርሳቸው ሥልጣን ማነስ ቅሬታቸውን በልባ
ቸው ይዘው ኖሮ ባሁኑ ጊዜ አሳባቸውን ከደጃች ውቤ ጋር
አደረጉ ።

እንደዚህም ሆኖ ፥ የውስጥ ለውስጡ ዐድማውና ዝግጅቱ የፖ
ለቲካውም ዘዴ ሥራውን ብዙ ጊዜ ከቀጠለ በኋላ ፥ በመጨረሻ



ደጃች ውቤ ከግብጽ ያስመጧቸውን ጳጳስ አቡነ ሰላማን አስ
ከትለው ፥ በ1834 ዓ. ም. በጥር ወር ወደ ራስ ዐሊ ከተማ ወደ
ደብረ ታቦር መጡ ። መምጣታቸውን በሰሙ ጊዜ ውስጡን
ከደጃች ውቤ ጋር የተስማሙት ደጃች ጐሹ ዞረው ለደጃች ውቤ
ገቡ ። ንጉሡም ዐፄ ዮሐንስ ከቤተ መንግሥቱ አዳራሽ አምል
ጠው ለደጃች ውቤ ገቡ ።(1) ስለዚህ ደጃች ውቤ ደጃች ጐሹ
ንና ንጉሡን ዐፄ ዮሐንስን ፥ እንደዚሁም ጳጳሱን አባ ሰላማን
ይዘው መነሣታቸው ፥ ራስ ዐሊንና ወገኖቻቸውን ለጊዜው እሥ
ጋት ላይ መጣሉ የታወቀ ነው ።

ቢሆንም ፥ ደጃች ውቤና ራስ ዐሊ በየካቲት ወር ደንበኛውን
ጦርነት ዠመሩ ። አቡነ ሰላማም «ከራስ ዐሊ ጋር ሆነህ ደጃች
ውቤን የወጋህ ገዝቻለሁ» ስላሉ ፥ በራስ ዐሊ ወገን በሥጋት ላይ
ሥጋት ጨመረ ። ቢሆንም ከራስ ዐሊ ወገን ያለው ግዝትና ስብ
ከት የማይፈታው ብዙ ጦር ስለነበረ ፥ ከደጃች ውቤ ጦር ጋራ
ጉጥሞ በጀግንነት ይዋጋ ጀመረ ። የደጃች ውቤም የስሜንና የወ
ገራ ፥ የትግራይ ጦር በርትቶ እየተዋጋ ብዙ ሰዓት በመመከቱና
በፍጹም ለእግረኛ ጦር የማይበገር መሆኑም ስለ ታወቀ ፥ ከኋላ
ተጠባባቂ የነበረው የራስ ዐሊ የፈረሰኛ ጦር ከውጊያው ተደባ
ለቀ ። በዚህም ጊዜ የደጃች ውቤ ወታደር የራስ ዐሊን የፈረሰኛ
ወታደር በነፍጥ እየመታ ሲጥለው ራስ ዐሊ ይመለከቱ ነበርና ፥
ከእንግዲህ ወዲያ ምን ተስፋ አለ ብለው ከጦርነቱ ቦታ ሸሽተው
ወደ ላስታ በመሔድ በዋድላ ገዳም ገብተው ተቀመጡ ።

ደጃች ውቤም ፥ የራስ ዐሊ ፈረሰኛ ወታደር የርሳቸውን ጦር
በነፍጥም ፥ በጐራዴም እየመታ ሲጥለው እያዩ ይኸንኑ እመስለ
ሥጋት ላይ ነበሩና ድል የሆኑ መሰሏቸው ሸሹ ። እነዚህ ሁለቱ
ታላላቅ ሰዎች የጦርነቱ ድል ወደ ማን መሆኑን ፍጻሜውን ለመ
ጠበቅ አቅቷቸው መሸሻቸውን የሰማ ሁሉ ሣቀባቸው ። በኋላ
ግን ፥ ደጃች ውቤ የራስ ዐሊን መሸሽ ርግጠኛውን በሰሙ ጊዜ
አንሰራርተው ፥ አጠገባቸው ያለውን ጥቂት ጦር ይዘው ተመለሱና
ከራስ ዐሊ ሰዎች ጋራ ተዋግተው ድል አደረጉ ። የደብረ ታቦር
ንም ከተማ ያዙ ። በራስ ዐሊም አዳራሽ ገብተው ካቡነ ሰላማና
ከመኳንንቶቻቸው ጋር ደስታ ሲያደርጉ ፥ ደጃች ዐሊጋዝ የተባለው

1 ኩልቦ በ2ኛው ቮሊዩም ምዕራፍ 14 ገጽ 303

ደፋር የራስ ዐሊ የጦር አለቃ ጭፍሮቹን አስከትሎ እጁን ለመስጠት ፣ መሣሪያውንም ለማስረከብ የመጣ አስመስሎ እዘናጋና በደጃች ውቤ ላይ አደጋ ጥሎ ማረከና አሰራቸው ። ዐሊጋዝም ደጃች ውቤን እንዳሰረ ለመንገርና ለማስረከብ የበላዩን ራስ ዐሊን ቢፈልግ ፣ ቢያስፈልግ እርሳቸው በዋድላ ገዳም ስለ ተደበቁ ሊያገኛቸው አልቻለም ። በዚሁም ነገር በዚያ ጊዜ ያልተገረመና ያልሣቀ አለመኖሩን ከዚህ ቀጥሎ ያለው የሁለት ሰዎች ንግግር ያስረዳናል ።

የዚህን የጦርነት ወሬ ያልሰማ አንድ ሰው ፣ የሰማውን ሰውዬ እመንገድ አግኝቶ ፣—

«እባክህ የራስ ዐሊና የደጃች ውቤ ጦርነት በምን አለቀ?» ብሎ ጠየቀው ።

«ከተዋጉ በኋላ ደጃች ውቤ ተማርከው ታሰሩ ። ራስ ዐሊ ደግሞ ሸሹ» ሲል መለሰለት ።

«ኧረ ባክህ በወግ (በሚገባ) አድርገህ አውራኝ!» ብሎ እንደገና ሲጠይቀው ፣

«እነሱ ራሳቸው በወግ ያልሆኑትን ፣ እኔ እንዴት አድርጌ በወግ ላውራህ!» አለውና እየሣቀበት መንገዱን ቀጠለ ። ያኛውም እየተገረመ ሔደ ይባላል ።

የሆነ ሆኖ ፣ ዐሊጋዝ ጌታው ራስ ዐሊ ያሉበትን አሰልሎ «ድሉ የኛ ነው ፣ ጠላትዎንም ደጃች ውቤን ማርኬ በእጄ ናቸው» ብሎ ልኮ ነበርና ፣ ራስ ዐሊ ይኸን በሰሙ ጊዜ ከተደበቁበት ከዋድላ ገዳም ተነሥተው በወጡ በ15ኛው ቀን ተመልሰው ደብረ ታቦር ገቡና ከሚስታቸው ከወይዘሮ ሂሩት ተገናኙ ። የጉጃሙ ደጃች ጉሹ ራስ ዐሊ በሸሹበትና ደጃች ውቤ ደብረ ታቦር በገቡበት መካከል ፣ ከደጃች ውቤ ጋራ ቀድሞ ባገኙት ተስፋ መሠረት ከወይዘሮ ሂሩት ተገናኝተው ነበር ይባላል ። በኋላ ግን ፣ የራስ ዐሊ ጦር በዐሊጋዝ እየተመራ መጥቶ በደጃች ውቤ ላይ አደጋ ጥሎ ማሸነፉን ባዩ ጊዜ የነገሩ አያያዝ ስላላማራቸው ፣ ሁሉንም ነገር ትተው አገራቸው ጐጃም ገብተው ዝም ብለው ተቀመጡ ።



እንግዲህ ራስ ዐሊ ከዋድላ መጥተው ደብረ ታቦር በገቡ ጊዜ ፣ እስረኛውን ደጃች ውቤን ይገድሏቸዋል ወይም ያስሯቸዋል እየተባለ ሲፈራ አሸናፊው ራስ ዐሊና ተሸናፊው ደጃች ውቤ በድርድር መታረቃቸው ተሰማ ። እርቁም የተፈጸመው ቀጥሎ ባለው ዐይነት ነው ።

ሀ. ደጃች ውቤ ሊያነግሡዋቸው ከግብጽ አገር ያስመጡቸውን ጳጳሱን አቡነ ሰላማን ለራስ ዐሊ ለመተው ።
ለ. ወደ ግዛታቸው ከተመለሱ በኋላ የተለመደውን ግብር ሊልኩ ።

ራስ ዐሊ ይኸን ግዴታ በሸማግሌ ፊት ካስገቡ በኋላ ፣ የቀድሞ ግዛታቸውን በሙሉ መርቀው ደጃች ውቤን በሰላም አሰናበቷቸው ። በዚህ ጊዜ ደጃች መርሶ የሚባሉ የደጃች ውቤ ወንድም(*) የስሜንን ባላገር ለጦርነት ቀስቅሰው ውቤን አላስገባም ብለው ውጊያ ገጠሙ ። ራስ ዐሊም ቢልኩባቸው እንቢ አሉ ። ስለዚህ ራስ ዐሊ ደጃች ውቤን ግዛታቸውን መርቀው መላክ ብቻ ሳይሆን ፣ ያንኑ የታወቀውን የጦር አለቃቸውን ዐሊጋዝን ልከው ደጃች መርሶን አስወግተው ፣ ደጃች ውቤ በቀድሞ ግዛታቸው ገብተው እንዲደላደሉ ረዷቸው ። ደጃች መርሶም ተሸንፈው በዋልድባ ገዳም ገብተው ተቀመጡ ።

እኩታማቸው እደብረ ታቦር ድረስ መጥተው ፣ ጠብ እጫሪ ሆነው ወግተው እስከ መሸሽ ያደረሷቸው ደጃች ውቤ በእጃቸው ከወደቁላቸው በኋላ ፣ በመግደልና በምትካቸው ሌላ ታማኝ በመሾም ፋንታ ራስ ዐሊ ይኸን የመሰለ ቸርነት ማሳየታቸው የልብ ደግነት ነውን? ወይስ ባለቤታቸውን ወይዘሮ ሂሩትን ለማስደሰት ብለው ይሆን? ወይም ደጃች ውቤን ባስር ወይም ብገድል የትግሬና የስሜን ባላባቶች በያለበት እየተነሡ ከርሳቸው የበለጠ ማስቸገራቸው አይቀርምና ፣ ብዙውን ሰው ባንድ ሰው እያስገዙ ዝም ለማሰኘት ይሆን? ፍርዱን ላንባቢ እንተዋለን ።

---

* ደጃች መርሶ ባባታቸው በደጃች ኃይለማርያም በኩል የደጃች ውቤ ወንድም ፣ እናታቸው ወይዘሮ ሂሩት ናቸው ። ደጃች ውቤ ግን የተወለዱት ካንዲት ከጃናሞራ (ስሜን) ሴት ነው ። መርሶ የተወለዱት ከደንበኛ ሚስት ፣ ውቤ ግን ዲቃላ ናቸው ። በዚህ ዐይነት ለግዛት የታደሉት ከዋናው ልጅ ይልቅ ዲቃላው ናቸው ማለት ነው ።

ይኸም ብቻ ሳይሆን በጠቡ ጊዜ ወደ ደጃች ውቤ ተደርበው የነበሩትን የናታቸውን ባለቤት ዐፄ ዮሐንስንም መልሰው በዙፋናቸው እንዲቀመጡ ፈቀዱላቸው ። ደጃች ጐሹ ግን ፣ ቀርበው ባለፈ ጥፋታቸው ይቅርታ ጠይቀው ሳይታረቁ ዝም ብለው አገራቸው ገብተው በመቀመጣቸው ፣ በዚህ ላይ ደግሞ ራስ ዐሊ ደብረ ታቦርን ትተው ፣ ወደ ዋድላ በሔዱበት ጊዜ ባለቤታቸውን ወይዘሮ ሂሩትን አገባሁ ብለው በመድፈራቸው ምክንያት ሊወጉ ይገባቸዋል ተባለና ፣ በዚሁ ዓመት በ1834 ዓ. ም. ጦር ሐዶ ሲወጋቸው ከረመ ። በመጨረሻም ታረቁና በሁለቱ መካከል ሰላም ተመሠረተ ። ሁኔታው የራስ ዐሊን ፍጹም ታጋሽነትና ደግነት ያሳያል ። በእርግጥ የኚህን መስፍን ደግነትና ቸርነት ፣ ብዙ ጊዜ አብሮአቸው የቆየው አርና ዳባዲ የሚባለው የፈረንሣይ ተወላጅ ወዳገሩ ሲመለስ በጻፈው መጽሐፍ ላይ ገልጾታል ።[1]

ከዚህ ጊዜ ወዲህ ፣ ደጃች ውቤና ራስ ዐሊ በሰላም እስከ 5 ዓመት ድረስ ኖሩ ። በ5ኛው ዓመት ላይ ደግሞ ፣ ግጭት ቀስቅሰው እስከ ሦስት ዓመት ድረስ የደፈጣ ጦርነት ሲያደርጉ፣አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሲታረቁ እስከ 1843 ዓ. ም. ደረሱ ። ራስ ዐሊ የበላይ ፣ ደጃች ውቤ የበታች መስለው እኝህም ቢያስገብሩ ፣ እኛም አንዳንድ ጊዜ ቢገብሩ ፣ ሁለቱም ኃይለኞች በመሆናቸው ፣ አንዱ አንዱን ሊያሸንፈውና ለዘለቄታ ሊደምስሰው አልቻለም ። በመካከሉ ግን ፣ የቋራው ካሣ ሁለቱንም አጥፍተው ከብዙ ዘመን ጀምሮ እነ ራስ ወልደ ሥላሴ ፣ እነ ደጃች ሰባጋዲስ ፣ እነ ራስ መርድ ፣ እነ ደጃች ዘውዴ ደክመው ያልሆኑላቸውን ዘመነ ምስፍና አስወገደው፣የንጉሠ ነገሥትን ሥልጣን እንደገና በጥንቱ በነኢያሱና በነበካፋ ዐይነት መሥርተው አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ከፈቱ ። የርሳቸውን የጦርነት እርምጃ ከትግሬም ፣ ከጐጃምም ፣ ከቤጌምድርም ፣ ከሸዋም የተነሣው የጦር መሪ ሊያግደው አልቻለም ።[2]

1 Douze Ans dans la haute-Ethiopie O Arnauld d' Abbadie (Fragments inedits) pp. 66-67

2 Hist. Pol. et Religieux - J.B. Coulbeaux, Vol. II, pp. 379-380 Storia di Abyssinia L. Dei Sabelli pp.



ደጃዝማች ውቤ ኃይለማርያም
(ከወልደማዪር ቲዎፊል መጽሐፍ)

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## የግብጽ ጦር ለጥቂነት ፣ የደጃዝማች ክንፉ ጉብዝና ፡ የነራስ ዐሊ ለቤቱታ ለሉዊ ሬሊፕ ፣ የወይዘሮ መነንና ያዒ ዮሐንስ ጋብቻ

ከእቴጌ መነን ባለቤት ካፄ ዮሐንስ ማልሳይ በፊት ፣ ዐፄ ሣህለ ድንግል በዙፋን በተቀመጡበት ራስ ዐሊ ዋና እንደራሴ ፣ ደጃች ውቤ የስሜን ፣ የትግራይና የትግሬ ገዥ ፣ ደጃች ክንፉ የደምቢያና የጯራ ገዥ በነበሩበት ሰዓት ፣ ከቱርክ ሡልጣን በታች ግብጽንና ሱዳንን ደርቦ ይገዛ የነበረው መሐመድ ዐሊ ይባላል ።

መሐመድ ዐሊ የተወለደው እንደ ኤ. አ. በ1769 ዓ. ም. ነው ። አባቱ ኢብራሂም አጋ የአልባንያ ተወላጅ ነው ። የተወለደው በመቄዶንያ (ግሪክ) ነው ። እነ ትልቁ እስክንድር የተወለዱበት ይህ የመቄዶንያ አውራጃ በዚህ ዘመን እንደ ሌላው የባልካን አገር የታላቁ የኦቶማን ቱርክ ግዛት ሆኗል ። መሐመድ ዐሊ በልጅነቱ ትምባሆ ነጋዴ ነበር ። በኋላ በቱርክ መንግሥት ውስጥ ወታደርነት ተቀጥሮ ከቱርክ የጦር ሠራዊት ጋር በቅድሚያ በግሪክ አገር (1824—28) ፣ ቀጥሎ በሶርያ ፣ ከዚያም ግብጽን የወረረውን ናፖሊዮንን ሊወጋ መጣ ። ግብጽን ለመያዝ እንግሊዝና ፈረንሣይ በተጋጋለ ሁኔታ በሚፋለሙበትና የቱርክ ሡልጣንም በተቻለው መጠን ፣ እነዚህን ሁለት የሠለጠኑ የአውሮፓ ኃያላንን በሚመክትበት ሰዓት መሐመድ ዐሊ ባንድ ወገን ከአውሮፓውያኑ ፣ በሌላው ወገን ግብጽን ከሚያስተዳድሩትና ከተጠሉት የማምሉክ ባለሥልጣናት ጋር እየታገለ ፣ ከወታደርነት ተግባሩ ዐልፎ በመልካም አስተዳደሩ ፣ ቀና ፍርድ በመስጠቱ በግብጽ ሕዝብ ዘንድ ዝናው ባጭር ጊዜ ውስጥ ተስፋፋ ። ከቱርክ ሡልጣን አገዛዝ ሥር ለመውጣት ከታገለ በኋላ ፣ ሳይሆንለት ቀርቶ ታማኝነቱን ቀጠለ ።

የቱርክ ሡልጣን ሳሊም የመሐመድ ዐሊን ዝናውን ከችሎቱ ጋር አመዛዝኖ በቂነቱን ከተረዳ በኋላ ፣ በ1805 ዓ. ም. የግብጽ

ፓሻ ብሎ የግብጽ አስተዳዳሪ እንዲሆን ሾመው ። የርሱም ሥልጣን በቅድሚያ በላዕላይ ግብጽ ቀጥሎም በታሕታይ ግብጽ እየተስፋፋ ሲሔድ ፤ ወደ ደቡብ ዐልፎ ያን ጊዜ ኑብያ—ስናር እየተባለ የሚጠራውን ፤ ዛሬ በጠቅላላው በሱዳን ስም የታወቀውን አገር ብዙ ወታደር እያዘጋጀ በመላክ በ1821—22 ዓ. ም. ወረረ ። ከዚያም ለግብጽና ለሱዳን ሕይወት የሚሰጠውን አባይን ጭምር ከምንጩ ለመያዝ ዐቀደ ። ዕድሜው ወደ 60 ዓመት በተጠጋበት ሰዓት እርሱ ሥልጣኑን አደላድሎ በካይሮ ተቀምጦ በበላይ እየመራ የአባይ ውሃ የሚተላለፍበትን ፤ የወርቅ ሀብት ሞልቶበታል እየተባለ የሚወራውን የኑብያን አገር በእጁ ለማድረግ በሁለተኛ ልጁ በእስማኤልና በአማቹ በመሐመድ ቢይ ኤል — ዲፍተርዳር የሚመራ ሁለት ክፍለ ጦር ወደ ሱዳን ልኮ ኑብያንና ስናርን ፤ ጎርዶፋንን አስያዘ ።

ኑብያዎቹ በበኩላቸው በሚሊክ ሸንዲ መሪነት አገራቸውን ከጠላት ለመከላከል በተነሡ ጊዜ ፤ ኢስማኤል እነሱን ለመደምሰስ ብዙ ኑብያዎችን ገደለ ። በዚህም ጊዜ አለቅዬውንም በንቀት መልክ በትምባሆ መጠጫው መትቶ ካዋረደው በኋላ ገደለው ። ይኸንንም ያለቃቸውን ውርደት መሸከም ያቃታቸው ኑብያዎች ኢስማኤልንም ገደሉት ። የዚህን ወሬ አማችዬው መሐመድ ቤይ ከጎርዶፋን በማሥጋሜ ደርሶ ፤ የኑብያን አገር እንዳልሆነ አድርጎ በጦር ኃይል ከደመሰሰ በኋላ ፤ የእስማኤልን ደም ለመበቀል 30,000 ኑብያውያንን አሳረደና በዚህ ዐይነት የጭካኔ ሥራ የግብጽን የበላይ ገዥነት በሱዳን ላይ አረጋገጠ ። ከተማውንም በካርቱም ላይ አደረገ ([1])

በዚህ ዐይነት ፤ በኢትዮጵያ ወሰን ላይ የሚገኘውን የስናርን ወረዳ ከያዘ በኋላ የመተማን ከተማ እየተሻገረ ፤ በደምቢያና በቋራ ግዛት እየገባ ያልታሰበ ወረራ በማድረግ ብዙ ሰው እየማረከ መውሰዱን ፤ ብዙ ከብትና ንብረት መዝረፉን የዚሁ ወረዳ ገዥ ስመ ጥሩው ደጃች ክንፉ ሰሙ ። አገሬውም በያለበት ተሸበረ ። ወረራውም እንደ መዓት ተቆጥሮ በየወረዳው ፤ በየደብሩ ምሕላና እግዚኦታ ተያዘ ። ደጃች ክንፉም ፤ «አይዟችሁ! እኔ

1 Coup d' oeil sur la Chronologie de la Nation Egyptiene - Joseph Cattaui Pacha - pp. 348-357.



ሳልሞት አትሞቱም» እያሉ ሕዝቡን ከማረጋጋት ጋር([1]) ወደ መተማ ሔደው ፤ ከግብጽ ጦር ጋር ተዋግተው ብዙ ጊዜ በመመለስ በበጌምድር ዝነኛ ሆነው ፤

«የክንፉ ጐራዴ ጥቁር የነበረ
እየቀላ ሔደ ቱርክ እየመሰለ»

ተብሎ ተገጥሞላቸዋል ። በኋላ ግን ፤ የግብጽ ጦር አጥቂነት እየከበደ ስለ ሔደና አገራቸውን ደምቢያን ስለ ወረረ ፤ ይኸንኑ ለበላይ አለቃቸው ለራስ ዐሊ አስታወቁ ። እርሳቸው ፤ ለስሙ ቢሆንም ፤ በዙፋን ላሉት ላፄ ሣህለ ድንግል ለስሜንና ለትግራይ ገዥ ለደጃች ውቤ ፤ ለዕጨጌው ለአባ ማኅፀንተ ሚካኤል ነግረው ፤ በዚሁም ጊዜ በጐንደር ከሚገኙት ከነአንቷን ዳባዲ ጋር በነገሩ ከተመካከሩበት በኋላ ፤ «የመሐመድ ዐሊን ጦር በውጊያ አንችለውም ፤ በፈረንጅ አገር ላሉት የክርስቲያን መንግሥታት ማመልከቱ ይሻላል» ተብሎ ከዚህ እንደሚከተለው በቅድሚያ ለፈረንሣይ ንጉሥ ለሉዊ ፊልፕ ደብዳቤ ጽፈው ለመላክ ወሰኑ ።([2]) ደብዳቤው በቅድሚያ ፤ «ነገረ ሰቆቃው ወላሕይ ዘተፈነወት እምኃበ ንጉሥ ሣህለ ድንግል ፤ ወይጨጌ ማኅፀንተ ድንግል ፤ መምህር ዘደብረ ሊባኖስ ፤ ራስ ዐሊ ርእሶሙ ለመኳንንት ፤ ደጃዝማች ውቤ ወደጃዝማች ክንፉ» በማለት የዋይታና የለቅሶአቸውን ምሬት ከማውሳት ጋር በአርእስቱ የመንግሥቱን ሠሪዎች የክብር ደረጃቸውን በመጠበቅ ይጀምራል ። ይኸውም ማለት በክብር አንደኛ ንጉሡ መሆናቸውን ፤ ከዚያ ከዋናው እንደራሴ ከራስ ዐሊ ፤ እጨጌው መብለጣቸውን ያሳያል ።

1 ወበመዋዕሊሁ (ለደጃች ክንፉ) ተሰምዓ ከመ መጽአ ትርኩ (ቱርክ) ወተዓየነ በመተማ ። ወሰሚዖ ደንገጸ ወሐዘነ ኵሉ ሀገር ወገብሩ ምህላ ኵሎሙ ምስለ አንብዕ ብዙኅ ። ወይቤ ደጅአዝማች ክንፉ ኢትፍርሁ ወኢትደንግጹ ዘእንበለ እሙት አነ ኢትመውቱ Chronaca reale-C. Rossini pp. 81-82 ትርኩ የሚለው ቱርክን ያን ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ የዘመተውን መልኩ ነጣ ያለውን የግብጽን ጦር ሁሉ ያገራችን ሰው ቱርክ ይለዋል ።

2 ሉዊ ፊሊፕ (Louis Philippe) በፈረንሣይ ዙፋን የነበረበት ጊዜ እንደ አው ቁ. 1830 — 1848 ።

የሆን ሆኖ ፣ ከዚሁ አያይዞ ደብዳቤውን ለፈረንሣይ ንጉሠ ነገሥት ለመጻፍ የመከሩዋቸውን እነ አንቷንን እንደዚህ ሲል ያወሳል ። «ያንተን ደህንነት የክርስቲያን ጠባቂ መሆንህን ሐበሻን ሊያዩ የመጡ እንጦንዮስ ወልደ አብዲ ፣ ሚካኤል ወልደ አብዲ ቢነግሩን መከራችንን ላክንብህ»([1]) ካለ በኋላ ከዚሁ ቀጥሎ ወደ ፍሬ ነገሩ በመግባት ፣ «የመሐመድ ዐሊ ሠራዊት ቱርክ አገራችን መጥቶ ቤተ ክርስቲያናችንን አቃጠለው ፤ ወንጌላችንን ተኰሰው ፤ ሺህ አምስት መቶ ክርስቲያን ገደለ ፤ ሁለት ሺህ ከስድስት መቶ ክርስቲያን ማርኮ አታክልት አጠጭ አደረገው ።.......... ከመዲናው (ከከተማው) ጐንደር ሊደርስ የሁለት ቀን ጐዳና ቀርቶበታል ። ምነው ፣ አንተ ትልቁ ንጉሥ እያለህ እንዲህ መሆናችን?.......... አሁንም ኃይልህን ሰምተናልና እንደ ሥልጣንህ አድርገህ ቱርክን መልስልን ፣ ከመሐመድ ዐሊ ልከህ.........» በማለት ይደመድማል ። ሰነዱ በዚሁ ቃል ለእንግሊዝ ንግሥት ለቪክቶሪያ መጻፉን ይጠቅሳል ።([2])

የዚህን ጉዳይ ካንድ ተክለ ሃይማኖት ከሚባል ኢትዮጵያዊ (ካቶሊክ) ጽሑፍ የተገኘ ብለው ሙሴ ኮንቲ ሮሲኒ ወደ ኢጣልያ የተረጐሙት ጽሑፍ በመጠኑ ከዚህ ለየት አድርጐ በማብራራት ያቀርባል ። በዚህ ጽሑፍ ላይ ቱርኮች በሰናር በኩል መጥተው አገር መውረራቸውን ፣ እነርሱንም ደጃዝማች ክንፉ ተዋግተው ማሸነፋቸውን ፣ የዚህን ወሬ የግብጽ ንጉሥ መሐመድ ዐሊ በሰማ ጊዜ ቁጥሩ የበረከተ ጦር መላኩን ፣ አንድ ባሻ ዘይኑ የሚባል የዐድዋ እስላም ወንድሙ በጐንደር የነጋዴዎች ኃላፊ የነበረና ሁለቱም ከብረው የነበሩ የራስ ዐሊ ወገኖች የሆኑ ወደ መሐመድ ዐሊ መሔዳቸውን ፣ ራስ ዐሊ በኢትዮጵያ ላይ ለመንግሥና ዘይኑ የትግራይ መስፍን ለመሆን ፍላጐት እንደ ነበራቸው ካወሳ በኋላ ፣ ወደ ወረራው ጉዳይ ተመልሶ ደጃች ክንፉ የመሐመድ ዐሊ የበረከተ ጦር መምጣቱን ባዩ ጊዜ ፣ «የመጣውን ጦር አምላክ ካልመለሰው በቀር ፣ እኛ የማንችለው ነንና ምሕላ

1 Antoine d' Abbadie ወንድሙ Michel Arnauld d' Abbadie

2 Bibl. National Paris የአንቷን ዳባዲ ፋይል ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ካጼ ልብነ ድንግል እስከ ዐጼ ቴዎድሮስ — ተ.ጸ.መ. ምዕ.85 ገጽ 340.343



ይዛችሁ ጸልዩልን» ብለው ወደ ጐንደር መላካቸውን ፣ ከዚህ አቶ ተክለ ሥላሴ የሚባል ብልህና ታሪክ ዐዋቂ ፣ «ለፈረንሣይ ንጉሥ ለፊሊፕ ደብዳቤ ጽፋችሁ በፈረንሣዩ በአንቷን እጅ ላኩ» ብሎ መምከሩንና በዚሁ መሠረት ደብዳቤው ተጽፎ የንጉሡ የሣህሉ (ሣህለ ድንግል) እና የዕጨጌ ፊልጶስ([1]) ማኅተም ተደርጐበት ተላከ ካለ በኋላ ፣ ሁኔታውን በመደምደም እንደዚህ ይላል ። «......... ቱርኮቹ በተ ጠጉ ጊዜ (ወደ ጐንደር) ሁሉም መራራ ለቅሶ አለቀሱ ። ጌታም (አምላክ) በጸጋው ለቅሶአቸውን ሰምቶ እነርሱን ከውድቀት አድኖ በቱርኮቹ ላይ በሽታ (ሕማመ ፈንጸት) አስነሥቶ ፈጃቸው ። የተረፉትም ሸሹ ። የተጻፈውንም ደብዳቤ አንቷን (እንጦንዮስ) ከጐንደር ወደ ግብጽ ወስዶ ለፈረንሣዩ ቆንሲል በማስረከብ ፣ የኢትዮጵያውያንን መከራና ለቅሶ በዝርዝር ገለጸለት ። ከዚህ በኋላ የፈረንሣዩ ቆንሲል ወደ መሐመድ ዐሊ ገብቶ ፣ የግብጽ ጦር ወደ ክርስቲያኖቹ ወደ ኢትዮጵያውያን አገር እንዳይዘልቅ እንዲያደርግ ነገረው ። የአውሮፓ ነገሥታትም የግብጹ ንጉሥ ወደ ኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር እንዳይገባ ፣ በሚጻጻፈውም ደብዳቤ ላይ ፣ «የኢትዮጵያ ንጉሥ» እያለ ይጽፍ የነበረውን እንዲተው አስገደዱት ።([2])

መቼም በትግራይ ግንባር በወልቃኢትና በቁናሞች በኩል ከደጃዝማች ውቤ ፣ በደምቢያና በቋራ በኩል ከደጃዝማች ክንፉ ጋር የወሰን ግጭቱ ከተለመደ ቆይቷል ። ከግብጾቹና ከቱርኮችም ወታደሮች ቁጥጥር ሥር ካሉት የኑብያና የሰናር ፣ የጋላበትና የገዳሪፍ ተወላጆች ውስጥ በጥፋት ከዚያ እያመለጡ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት የሚመጡት ብዙ ናቸው ። ከነዚህም መካከል የመሐመድ ዐሊን ልጅ እስማኤልን የገደለው ሚክኔሚር የሚባል ሰው የግብጽ ጦር ሲያባርረው በሽሽት ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ራሱን በማዳኑ ፣ ይኸን በመሳሰለ ሰበብ ሁሉ ሱዳን ባሉት ግብጾችና በኢትዮጵያውያኑም መካከል ሰላም አልነበረም ።

1 ፊልጶስ ማለቱ ጸሐፊው የተሳሳተ ይመስላል ። አባ ፊልጶስ የነበሩት በራስ ጉግሣ ጊዜ (1790 — 1818) አካባቢ ነው ። ባሁኑ በራስ ዐሊ ጊዜ ያሉት እጨጌ በፊተኛው ደብዳቤ ላይ የተጠቀሱት ማኅፀንተ ድንግል ናቸው ። ዋዜማ ብ.ጌ. ኅሩይ ገጽ 113 ።

2 Fonti Storiche Etiopiche per il secolo XIX-1-Vicende del Etiopia..... ai Tempi di Ras Ali.....pp. 27-30.

የኢትዮጵያ መሳፍንትም ፣ የእስላሞቹ የቱርክና የግብጽ ጦር ባጠቃቸው ቁጥር ፣ አጠገባቸው ባሉት ተቀማጮች ወይም አገር ጐብኝዎች እየተመከሩ ፣ የክርስቲያኖቹ የእንግሊዝና የፈረንሣይ ነገሥታት እንዲያድኗቸው መማጠናቸው የተለመደ ነው ። እሁንም እነ ራስ ዐሊ በነዊሊያም ኮፊንና በነዳባዲ በኩል ለንግሥት ቪክቶሪያ ፣ ለፈረንሣይም ንጉሥ ለሉዊ ፊሊፕ በጻፉት አቤቱታ መሠረት በካይሮ የሚቀመጡት የፈረንሣይና የእንግሊዝ ቆንሲሎች እነ ኮሎኔል ካምቢል በነገሩ እየገቡ ወረራው ለጊዜው እንዲታገድ ማድረጋቸው እርግጥ ነው ።[1]

ዐፄ ሣህለ ድንግልና ራስ ዐሊ ለፈረንሣይ ንጉሥ የጻፉዋት ደብዳቤ ቀንና ዓ. ም. የላትም ። ነገር ግን ፣ ሉዊ ፊሊፕ የነገሠበት ዘመን እንደ ኤው. አ. 1830—1848 ዓ. ም. ሲሆን የግብጾችም ወረራ የተከናወነው እንደ ኢት. አቆ. 1832 እና 1835 ዓ. ም. መካከል ላይ ነው ።[2] ይኸውም ማለት የደምቢያ ገዥ ደጃዝማች ክንፉ ከመሞታቸው ከ1841 ዓ. ም. ሰባት ወይም ስምንት ዓመት በፊት ማለት ነው ። በዚህ የጊዜ አካባቢ የልጅ ካሣ ዕድሜ በ23 እና በ24 ዓመት እንደሆነ ይገመታል ። ይኸም ደንበኛ የጐልማሳነት ጊዜያቸው ነው ማለት ነው ።

ልጅ ካሣ በሽፍትነትም ፣ በታማኝነትም በነበሩበት ሰዓት ወደ መተማ ጠረፍ እየዘመቱ መመለሳቸው ፣ በዚያ በዘረፉና በምርኮ ካገኙት ውስጥ ለእነ እቴጌ መነን በገጸ በረከት መልክ ማቅረባቸው ተገልጿል ። ነገር ግን ፣ የመሐመድ ዐሊ ጦር አገራቸው ደምቢያንና ቋራን በወረረበት በዚያ ዘመን ፣ ካጐታቸው ከደጃዝማች ክንፉ ጋር ወይም ብቻቸውን ያደረጉትን ጦርነት ታሪክ ጸሐፊዎቻችን ለይተው አልጠቀሱትም ። የጸሐፊ እጦት እንጂ ፣ በዚህ የጐልማሳነት ዕድሜያቸው የትውልድ አገራቸው በመሐመድ ዐሊ ጦር ሲወረር ዝም ብለው ይቀመጣሉ ማለት ዘበት ነው ። ባንድ ቦታ ላይ ጊዜውንና ምክንያቱን ሳይለይ መተማ ሔደው ቆስለው ተመለሱ የሚለው ፣ በዚሁ ከመሐመድ ዐሊ ጦር ጋር ሲዋጉ መሆን አለበት ።

1 The Survival of Ethiopian Independence - S. Rubenson, pp. 68-71

2 እንደ ኤ.አ. 1848 ዓ. ም.



አለቃ ዘነብ ወሩን ጠቅሰው ዓመቱን በመዝለል ፣ «ደጃች ካሣ በመጋቢት ደቦርኪ ወደ ቱርክ ዘመቱ ። ወታደሩም የቱርክን ሠፈር ባየ ጊዜ፣ ያለ ፈቃዳቸው ሔደ (ሸሸ) ። ብዙውን ክርስቲያን በነፍጥ (በጠመንጃ) ፈጀው ። ደጃች ካሣም ሰዋቸው እንዳለቀ ባዩ ጊዜ ጥቂት ዕልፍ ብለው (ወደኋላ አፈግፍገው) ድንኳን ተተከለ ። ቱርክም በተራዛሚ ነፍጥ የድንኳኑን ተራዳ በመታው ጊዜ ነቅለው ከስዋራ ሥፍራ ተከሉ ።..........ተዚያም ወዳገራቸው ተመለሱ» ብለው የዘረዘሩት ምናልባት ከደጃች ክንፉ ሞት ወዲህ ያደረጉትን ጦርነት ይሆናል ።[1]


የሆነ ሆኖ ፣ ራስ ዐሊና ደጃዝማች ውቤ ስለ ተስማሙ ፣ የጐጃሙ ደጃዝማች ጐሹ ፣ ሌሎቹም የወሎና የላስታውም መሪዎች ይነስ ይብዛ ፣ በዋናው እንደራሴ በራስ ዐሊ ውስጥ በተጠቃለሉበት ሰዓት ከግብጾችም ጋር በሱዳንና በኢትዮጵያ ድንበር የሚደረገው ግጭት ስለ ቆመ ፣ ወይዘሮ መነን ከልጃቸው ከራስ ዐሊ ጋር በመስማማት ንጉሡን ሣህለ ድንግልን ከቤተ መንግሥት አስወጥተው ፣ በርሳቸው ፈንታ ያፄ ተክለ ጊዮርጊስን ልጅ ዐፄ ዮሐንስን አነገሡ ።

ከዚህ ንግሥ በኋላ ፣ ወይዘሮ መነንና ዐፄ ዮሐንስ በ1841 ዓ. ም. ላይ በይፋና በሥነ ሥርዓት ተጋብተው ፣ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ወይዘሮ መነን መባላቸው ቀርቶ እቴጌ መነን እየተባሉ መጠራታቸውን ታሪከ ነገሥት መዝግቦት ይገኛል ።[2]

ዳሩ ግን ፣ ጋብቻው በፍቅር የመፈላለግ ሳይሆን የፖለቲካ ጋብቻ ከመሆኑ በቀር የሚቀጥለው ጊዜ በካሣ አነሣሥ ንጉሡም ፣ እቴጌይቱም ፣ እንደራሴው ራስ ዐሊም ምቹ የሰላምና የዕረፍት ጊዜ አልገጠማቸውም ። ቀድሞ በነ ራስ ስሑል ሚካኤል ዘመን ፣ በ18ኛው ምዕተ ዓመት ፣ የነገሥታቱ የተሟላ ሥልጣን እንደ ወደቀ ሁሉ ፣ አሁን ደግሞ በተራው 19ነኛው ክፍለ ዘመን የመሳፍንትን ውድቀት ፣ የነገሥታትን ሥልጣን መያዝና ያገር አንድነትን አብሣሪ ዘመን ሆነ ።

1 አለቃ ዘነበ ገጽ 13

2 ወእመ. ዕሥራ ወአርባቱ ለዝንቱ ወርኅ (ነሐሴ 1841 ዓ. ም.) ነግሠ ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ወልዱ ለንጉሥ ተክለጊዮርጊስ ። ወእምዝ ነግሠት ይእቲኒ (እሷም ማለት መነን) ወተሠይመት እቴጌ እስከ ኮነት ሎቱ ብእሲተ ወፈጸመ ላቲ ሥርዓተ መንግሥት..........



መሐመድ ዐሊ (የግብጽ ገዥ)
(ከአባ ማስያስ መጽሐፍ)

# ምዕራፍ ዐሥር

## የደጃዝማች ካሣ ለጥቂነት ፤ የደጃዝማች ወንድይራድና የእቴጌ መነን ውድቀት

በደጃች ውቤና በራስ ዐሊ የጦርነት ፍልሚያ መካከል (1840 — 1844 ዓ. ም.) ካሣ በትውልድ አገራቸው በቋራና በደምቢያ እየተዘዋወሩ መሣሪያ ከያዘ ወታደርም ፣ ከጀሌም ፣ ከባላገርም እየሰበሰቡ የወታደርነት አቅዋማቸውን ከዕለት ወደ ዕለት ያጠነክራሉ ። በጐንደርና በደብረ ታቦር በሹመትም ፣ በደጅ ጥናትም በነበሩበት ሰዓት አንዳንድ የሚያበሳጭ ነገር እየገጠማቸው ሲናደዱ ባለቤታቸው ተዋበች ፣ «ምን ያናድድሃል! እነሱም በኃይል ገዥ ሆኑ እንጂ ፣ ገዥ ሆነው አልተወለዱም ። ለምን አንሸፍትም?» አሏቸው ይባላል ። በዚህም ላይ ከየጁ የሚወለዱት እነ ራስ ዐሊ ገዥዎች በመሆናቸው ፣ እየቆጫቸው ለየመኳንንቱ ይሰብኩ ነበር ይባላል ።

የዚህን ጉዳይ ጸሐፊው ፣ «ልጅ ካሣ በራስ ዐሊ ሰፈር ብዙ ቀን ተቀመጡ ። ከዚያው ሁነው ብዙ ወታደር ሲያባብሉ ነበር ። ......ሰዉ ደግሞ እጅግ ይወዳቸው ነበር» እያሉ በራሳቸው አነጋገር ካብራሩ በኋላ ፣ ከዚህም አያይዘው ስለ አሸፋፈታቸው እንደዚህ ይላሉ ። ‘ያን ጊዜ ልጅ ካሣ ቀለበኛ (ቀለብተኛ) ይዘው ወደ ቋራ ወረዱ ። ከርሳቸውም ጋር የራስ ዐሊ ቀለበኛ ብዙ መኳንንትና ወታደር ወረደ ። ደግሞ ቀለብ የሌላቸው መኳንንት ስለ ፍቅር ከርሳቸው ጋር ወረዱ ። የአገር መጥን ከቤታቸው አሰናድተው ሙሉ ክረምት በሲሳይ አከረሙት ። ከወረደው ሁሉ ታላላቅ ሰውም መሐላ አደረጉ ......»(1)

---

1 ቶዜላ ገጽ 4—5 ጸሐፊው ቀለበኛ የሚለው ምንም የተወሰነ ሥራና ሹመት ሳይኖራቸው በጐንደርና በደብረ ታቦር ግብር እየጠበቁ ምሳቸውን በመብላት ፣ ወይም ድርጎ ተወስኖላቸው በደጅ ጥናት ሥራ ፈተው የተቀመጡትን መኳንንትና ግብረ በላ ወታደር ነው ።

በምዕራፍ ሁለት ፣ በደምቢያና በወሎ ወይም በየጁ መሳፍንት መካከል ከዐፄ ኢዮአስ ዠምሮ የነበረውን የመቶ ዓመት ቅራኔ በሰፊው አንብበናል ።

በመካከሉ ዕርቅና ሰላም እየወረደ ፣ እነዚህ ሁለት ተቃራኒዎች አብረው በስምምነት የኖሩበት ጊዜ ቢኖርም ፣ ከካሣም ጋር ያው ቅራኔ ዐልፎ ዐልፎ መታየቱ አልቀረም ። በቅርቡ የደምቢያው ገዥ ደጃች ማሩ በመስፍኑ በራስ ይማም መደምሰሳቸውን ፣ በዚህም ጊዜ ካሣ በማኅበረ ሥላሴ ገዳም እንዳሉ ከራስ ይማም ጦር ጋር የመጡት የራያና የአዘቦ ኦሮሞዎች ፣ በጓደኞቻቸው ላይ የደረሰውን ግድያና ዝርፊያ ራሳቸው ተመልክተው ቂሙ ከልባቸው እንደማይጠፋ የታወቀ ነው ።

ካሣ በመሳፍንቱ በነራስ ዐሊ ላይ የንቀት መንፈስ ሲያድርባቸው በራስ ዐሊና በእቴጌ መነን ዘንድ እርሳቸው ደግሞ ፣ «ቆለኛ የፍየል እረኛ ፣ ወይም ሽፍታ ፣ ቀማኛ ፣ ዕብድ» እየተባሉ ዐልፎ ዐልፎ መሰደባቸው አልቀረም ።

በዚህ ምክንያት ፣ ካሣ ከ1830—38 ዓ. ም. ድረስ ወደነራስ ዐሊ ቤት ሲወጡ ሲገቡ ፣ ሲጣሉ ሲታረቁ ካሳለፉ በኋላ ፣ ከ1839 ዓ. ም. ዠምሮ እላይ እንደ ተባለው ወታደር ሲበረክትላቸው ፣ መኳንንት ሲያብሩላቸው በገሃድ ለዘለቄታ በራስ ዐሊ መንግሥት ላይ መሸፈታቸው ታወቀ ። በዚህም ጊዜ ልጅ ካሣ ሲባሉ የነበረው ቀርቶ በሹማምንቶቻቸውና በራሳቸው ፈቃድ ፣ እንደ አጐታቸው እንደነደጃች ክንፉ ፣ ደጃዝማች እየተባሉ ይጠሩ ዠመር ። በመዠመሪያ በጥቅምት 14 ቀን 1839 ከጐንደር የተላከባቸውን ጦር በቀላሉ ደምስሰው ፣ ከተላኩት መኳንንት መቶ ጠበንጃ በመማረክ በይበልጥ ጦራቸውን ለማደርጀት እየቀናቸው ሔዱል ።

የዚህም ወሬ ጐንደር ሲሰማ ፣ በነእቴጌ መነን ዘንድ ድንጋጤንና መገረምን አትርፏል ። በዚህ ጊዜ ነው ከእቴጌ መኳንንት አንዱ ደጃዝማች ወንድይራድ የእቴጌይቱን ንዴትና ብስጭት ለማብረድ ሲሉ ፣ «ይኽን የኮሶ ሻጭ ልጅ አሁን እንደ ሙጭሙጭላ(*)አንገቱን አንቄ አመጣልሻለሁ አይዞሽ» ብለው የፎከሩላቸው ። ፉከራው ለይስሙላ ይሁን ፣ ወይም በእርግጥ ደጃች ካሣን ተዋግቶ እማርካለሁ ብለው ከልብ ተማምነው መሆኑ አይታወቅም ።

* ይኸው ቃል አንዳንድ ጊዜ ሙጭልጭላ ወይም ጭዉጭላ ይባላል ። ይኸም የባላገርን ሁሉ ዶሮና ጫጩት እየበላ የሚያስቸግረው በሸዋ መጠማጥ የሚባለው ነው ።



ዳሩ ግን ፣ ደጃች ወንድይራድ በዚህ ዐይነት የኩራትና የንቀት ንግግር የአራት ደጃዝማቾች ጦር ይዘው ወደ ጭልጋ ከዘመቱ በኋላ ፣ ውጊያው ጫቆ በሚባል ሥፍራ ተዠምሮ ሲዋጉ ሳያስቡት በጦር ተወግተው በደጃዝማች ካሣ ወታደሮች ተማረኩ ። ካሣም አንድ ጊዜ ፣ «የኮሶ ሻጭ ልጅ» ሌላ ጊዜ «ሙጭሙጭላ» እያሉ የሰደቡዋቸው ወንድይራድ መማረካቸውን ሲያዩ ፈጣሪያቸውን አመስግነው ፣ ከድሉ በኋላ ግብር ገብቶ ሌላው ጠጅና ጮማ ሲጋበዝ ካሣ ፣ «እናቴ ከገበያ ኮሶ ሳይሸጥላት የቀረ (የተረፈ) አለ ። እህል ጠፍቷልና ይኽን ተመገብ» ብለው በምሬት እየቀለዱ ፣ የኮሶውን ብጥብጥ በታላቅ ጥዋ እያስሞሉ በማጠጣት ተበቀሉዋቸው ።(1)

አሁንም የደጃች ወንድይራድ መሸነፍ በጐንደር ሲሰማ ውስጣዊ ድንጋጤን መፍጠሩ የታወቀ ቢሆንም ፣ በእናትና ልጁ በእቴጌ መነንና በራስ ዐሊ ዘንድ ለስሙ በይፋ የንቀት መግደርደር አልቀረም ። ራስ ዐሊ በበኩላቸው «ወደቋራ ስዘምት ደጃች ውቤ ጐንደርን ወሮ ፣ ሥልጣኔን ቀምቶ ፣ አጠገቡ ባሉት በአባ ሰላማ እጅ ተቀብቶ ሊነግሥ ይችላል» የሚለውን እውነተኛውን የጥርጣሬ ስሜታቸውን ሸሽገው በንቀት ፣ «ለካሣ ጦሬን አልጭንም» ብለው በደብረ ታቦር እንዳሉ እናታቸው እቴጌ መነን ወደቋራ እንዲዘምቱ አደረጉ ።

ስለዚህ ፣ ደጃች ወንድይራድ በጥቅምት ወር (1840 ዓ.ም.(*) ከተሸነፉና በኅዳር ወር ሌሎች መኳንንት ልከው በጣቁሳ (ሰቀላ ዋርካ) ላይ ካዋጉ በኋላ ፣ በሚያዝያ ወር ጣና ባሕር አጠገብ የሜጫው ገዥ ብሩ ኃይሉ ተዋግቶ ፣ ከደቅ ደሴት ተመትቶ በሸሸት ወደ ቆራጣ ከሔደ ወዲህ ፣ በመጨረሻ እቴጌይቱ በሰኔ ወር የሰባት ነጋሪት አገር (**) አሰልፈው ፣ ባለቤታቸውን ዐፄ ዮሐንስን አስከትለው ወደቋራ (ሉሃ)ተጓዙ ። በጉዞም ላይ እቴጌይቱ በሠራዊታቸው

1 አለቃ ዘነብ ገጽ 12
* የዚህን ጦርነት አንዳንድ ጽሑፍ 1838 ዓ. ም. ላይ ያደርገዋል ። ነገር ግን አይመስልም ።
** የሰባት ነጋሪት አገር ማለት ፣ ሰባት ደጃዝማቾች ነጋሪት እያስመቱ ወደ ቤተ መንግሥት ለመግባትም ፣ ለመዝመትም መብትና ሥልጣን ያላቸው የሚያስተዳድሩዋቸው አውራጃዎች ማለት ነው ።

ብዛት በመተማመን ፣ «ይህ ቆለኛ ወዴት አባቱ ሊገባ ነው ይሆን?» እያሉ የንቀትና የትምክህት አነጋገር ተናገሩ ይባላል ።

በበኩላቸው ደጃች ካሣም የእቴጌ መነንን በዐዋጅ ብዙ ጦር ሰብስበው ከጐንደር መነሣታቸውን ሰላይ መጥቶ በነገራቸው ጊዜ ፣ «ይች ቆፍጣጣ! (*) እኔ የመይሳ ልጅ በጦር ወግቸ ባቄላ ያላስፈጨኋት እንደሆነ ታዘቡኝ» ብለው ለአሽከሮቻቸው እንደ ፎከሩ የዘመኑ ጸሐፊ ያመለክታሉ ። በዚህ ዐይነት የሁለቱ ጦር ሠራዊት ፊት ለፊት በተያየበት ወቅት ፣ ካሣ በትንሽ ጦር ብዙውን የርሳቸውን ሠራዊት ለመመከት በድፍረት ቆመው መጠበቃቸው ገርሟቸው አሁንም ኩሪይቱ እቴጌ ፣ «ይህ የፍየል እረኛ! አያፍርም ከኔ ጋር ሊዋጋ ቆሟል» አሉ ይባላል ።

የሆነ ሆኖ ፣ ጦርነቱ ሊዠመር ሲል ደጃች ካሣ ወዲያና ወዲህ እያሉ ፣ ለየክፍሉ የወታደር አለቃ የጦር መላ እየሰጡ ባለ ጠበንጃውንና ባለሰይፉን ፣ ባለሾተሉን በየሥፍራው መድበው ፣ «የኔ ሰልፈኛ የሆንህ የመለከት (ጥሩምባ) ድምፅ ሳትሰማ ጦርነቱን እንዳትዠምር ። መለከት በተነፋ ጊዜ ግን ፣ ፊትህን ሳታዞር ግባበት» ብለው አስጠንቅቀው እንደቆዩ ፣ ጦርነቱ ግራና ቀኝ ተዠመረ ። እርሳቸው የተመረጡትንና የሚያምኗቸውን ባለ ጠበንጃዎች እየመሩ በመካከል ገብተው ፣ የእቴጌይቱን ጦር ከሁለት ለያይተው በውጊያ በመበታተን በቀጥታ ወደ እቴጌይቱ ሲያመሩ ፣ አንድ ዠግና ጐበዝ እቴጌይቱን እንደ ተመኙት በጭናቸው ላይ ወግቶ ማርኮ ወደ ደጃች ካሣ መጥቶ ግዳይ ጣለላቸው ። እርሳቸውም ማራኪውን ፣ «እንኳን ቀናህ» የሚል ቃል ወርውረው ፣ እቴጌይቱን የሚጠብቁ ዘበኞች አዘው ወደፊት ቀድመው «በለው! ያዘው! ማርከው!» እያሉ የተረፈውን ጦር በፍጹም መደምሰሳቸውን ፣ እቴጌይቱንም «የፍየል እረኛ!» እያሉ ይሳደቡ የነበረውን ለመበቀል በዋሻ አስገብተው ባቄላ አስፈጩአቸው በማለት ጸሐፊው የእቴጌይቱን የጦርነት ፍጻሜ በዚህ ዐይነት ይደመድማሉ ። በመደምደሚያው ላይም ፣ 'ባፍ ይጠፉ በለፈለፉ' የሚለውን ተረት አክለውበታል ።(1)

---

* አርጊት

1 ስሙ ያልታወቀው ጸሐፊ የጻፈውና ፋዜላ ያሳተሙለት ገጽ 7—5 አለቃ ዘነብ ገጽ 13 አለቃ ወልደማርያም ገጽ 2—3



በኋላ ግን ፣ ራስ ዐሊ የእናታቸውን ተሸንፎ መማረክ እንደ ሰሙ ወዲያው ጦር በካሣ ላይ በመጫን ፣ በስሜን በኩል የሥልጣን ባላንጣ ለሆኑባቸው ለደጃዝማች ውቤ ምቹ ሁኔታ ላለመፍጠር ሲሉ ፣ ከአርማጭሆ ዠምሮ ቋራን ጭምር ግዛቱን እስጥግለሁ የሚል ተስፋ ለካሣ ሰጥተው በመስማማት እናታቸውን አስመለሱ ። ይሁን እንጂ ፣ በሚቀጥለው ጊዜ ውቤም ፣ ዐሊም ሁለቱም በወጣቱ በደጃዝማች ካሣ በየተራ ሲደመሰሱ ይታያል ።

# ክፍል ሁለት

## የዘመነ መሳፍንት ማክተም

# ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

*ጠላትን በመናቀ የሚመጣ የመሸነፍ ፍዳ ፤ ደጃች ካሣ ደጃች ጐሹን ጉራምባ ላይ ፤ ራስ ዐሊን አይሻል ላይ ድል እንዳደረጓቸው*

ደጃች ካሣ ፥ በመዠመሪያ እንሣሣቸው ላይ ደጃች ወንድይራድን ፥ ይልቁንም እቴጌ መነንን በውጊያ ያሸንፋሉ ፥ ወደፊትም ደጃች ጐሹን ፥ ቀጥለው የዋናውን እንደራሴ የራስ ዐሊን ጦር አፈራርሰው ፥ ሊነግሡ የሚዘጋጁትን ደጃች ውቤንም ድል አደርገው ይነግሣሉ ብሎ የጠረጠረ ያለ አይመስልም ።

እቴጌይቱንም ድል አድርገው ከማረኩ ወዲህ ፥ ይኸው ንቀት እንዳላቋረጠ በደጃች ጐሹ ደብዳቤና በተገጠመው ግጥም ላይ ይታያል ። ደጃች ጐሹ በጐጃም የመሳፍንቱ የዘር ግንድ ላይ እንደሚታየው ፥ የታላቅ ራስ ኃይሉ የልጅ ልጅ የወይዘሮ ድንቅነሽና የዳሞቱ ባላባት የደጃች ዘውዱ ልጅ ናቸው ።

እርሳቸውም የጐጃም ገዥ በነበሩበት ሰዓት ፥ ከዚህ በፊት ግብጾች አገር በወረሩበትና እነራስ ዐሊ ለሉዊ ፊልፕ በጻፉት ደብዳቤ ላይ ስማቸው መጠቀሱን እንባቢ እንደሚያስታውሰው፥ በጐንደር አንቷንና አርኖ ዳባዲ የሚባሉ ሁለት የፈረንሣዊ ወንድማማች ነበሩ ። አንቷን ዳባዲ የቀለም ሰው ስለሆነ ፥ ከጐንደር ሊቃውንትና ከነደብተራ አሥጋኸኝ ጋር ስለ መጻሕፍት ፥ ስለ ታሪክ ፥ ስለ ቋንቋ በመነጋገር ጊዜውን ያሳልፍ ነበር ። ሰውም አንቷን የሚባለውን ስሙን በኢትዮጵያ አጠራር 'እንጦንዮስ' እያለ ይጠራው ነበር ። እርሱም የኢትዮጵያን ባህል በመጠኑ ዜማና ቅኔ ቀጻጽሎ ከካህናት ጋር በቅኔ ማኅሌትም ይቆም ነበር እየተባለ ይወራል ።

ወንድሙ ደግሞ ሚሸል አርኖ ዳባዲ ፥ አንድ ጊዜ ለደጃች ውቤ ፥ አንድ ጊዜ ለደጃች ጐሹ ፥ እንደዚሁም ለራስ ዐሊ ሎሌነት እያደረ የጦር መሣሪያ ፥ ጠመንጃና ጥይት እያቀበለ ከብዙ

መኳንንት ጋር ተዋውቆ ወዳጅና ባለሟል ሆኖ ነበር ። የበለጠ
ግን የቆየው ከደጃዝማች ጐሹ ጋር ነበር ። ሙሉ ስሙ በፈረን
ሣዊ ሚሸል አርኖ ዳባዲ የሚባለውን መኳንንቱ ሚካኤል ፣
አንድ አንድ ጊዜም ራስ ሚካኤል ይሉት ነበር ።

ስለዚህ ደጃች ጐሹ ፣ ከደጃዝማች ካሣ ለውጊያ ከተሰለፉበት
ጊዜ ትንሽ ቀደም ብሎ ለዚሁ ለሚካኤል እንደዚህ ሲሉ ጽፈው
ለታል ። «ዛቲ ጦማር ዘተፈነወት እምኃበ ደጃዝማች ጐሹ ፣ ትብ
ጻሕ ኃበ ራስ ሚካኤል ። እጅጉን እጅጉን እንዴት አለህ ፣ እግዚ
አብሔር ለመገናኘት እስቲያበቃን ። ፈረሱን መልካም ፈረስ
ይገፎልሃለሁ ፤ አሁን መንገዱ ቢቸግር ነው የቀረ ። አሁንም
የላከህብኝ የዕቃው ነገር የምወደውን ዕቃ አንተ ታውቀዋለህ ።
ኩላሊት ኪዳነ ማርያም ተቀብሎ ተኔ ያድርስልኝ ። ተካሣ ጋር
የተዋጋን እንደሆነ ጐንደር እገባለሁ ፣ እንገናኛለን ። ወደቆላ የሸሸ
እንደሆነ ሰው ባገኝ ፈልጌ እሰድልሃለሁ ፈረሱን ። በቅሎም
ችግሮህ እንደሆነ ጨምሬ እሰድልሃለሁ ፤ ቢሆን ቢሆን አንተም
እንድትመጣ ። መልካም አገር የምትቀመጥበት አቆይሃለሁ ።
እጅግ ናፍቄሃለሁ ።»

ደብዳቤው የተገኘው በፓሪስ ቤተ መጻሕፍት በአንቷን
ዳባዲ ፋይል ውስጥ ነው ። ቀንና ዓመተ ምሕረት የለውም ። ነገር
ግን ፣ ደጃች ካሣ ከነእቴጌ መነን ከተዋጉ ወዲህ ወደፊት እንደም
ናነበው ከራስ ዐሊ በ1845 ዓ. ም. ከመዋጋታቸው ቀደም ብሎ
ስለሆነ ፣ ምናልባት ደብዳቤውን የጻፉት በ1843 ዓ. ም. ይሆናል ።

በደብዳቤያቸው ውስጥ ፣ «የዕቃው ነገር የምወደውን ዕቃ
ታውቀዋለህ» የሚሉት ጠበንጃና ጥይት ሳይሆን አይቀርም ።
ይኸም ከደጃች ካሣ ጋር ለመዋጊያ እንዲያገለግል ነው ። ፈረን
ሣዩ ደጃች ጐሹንም ፣ ደጃች ውቤንም ፣ ራስ ዐሊንም ጌቶቼ እያለ ፣
ግብር እየበላ ጭፍራውን አበጅቶ እነዚሁኑ በፈራረቃ እያጀበ
እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ መኰንን ተስማምቶ ፣ ተመሳስሎ የሚ
ኖር ነበር ። በተረፈ «ከካሣ ጋር የተዋጋን እንደሆነ ጐንደር
እገባለሁና እንገናኛለን ፣ ወደ ቆላ የሸሸ እንደሆነ ሰው ባገኝ
ፈልጌ እልክልሃለሁ» ሲሉ በእቴጌይቱ ላይ እንደ ነበረው
የንቀት ስሜት ፣ እርሳቸውም በእርግጥ ደጃች ካሣ ፈርተው የሚ
ሸሹ ፣ አለዚያም ቢዋጉ የሚሸነፉ መሆኑን አምነውበት ነበር



ማለት ነው ። የሁሉም መሳፍንት በዚህ ጊዜ በደጃች ካሣ ላይ
ያላቸው የንቀት ግምት ተመሳሳይ ነው ። ነገር ግን የናቁት ሁሉ
እየተሸነፉ ተዋረዱ ። እቴጌ መነን ፣ የራስ ዐሊ እናት ፣ ካሣን
ሊወጉ ሲጓዙ ፣ «ይህ ቆለኛ ወዴት ሊገባ ይሆን ?» ያሉትን የን
ቀት አነጋገርና በኋላም መሸነፋቸውን ስናነበው ፣ ጠላትን መናቅ
ራስን አዋርዶ ጠላትን ማክበር መሆኑን በደንብ እንመለከታለን ።
ለደጃች ካሣም የጠቀማቸው መናቃቸው ነው ። ከመናቃቸውም
የተነሣ ፣ መሳፍንቱ በየተራ እየተዋጉ በመጥፋት ፈንታ ከመዠ
መሪያው ላይ ሁሉም ኃይላቸውን አስተባብረው ካሣን ለመደም
ሰስ አለመምከራቸው ፣ ሳያውቁት በስሕተት ለካሣ የድል አድራ
ጊነት እርምጃ በገዛ እጃቸው አመቺ ሁኔታ እንደ ፈጠሩላቸው
ይታያል ።

ከእቴጌ መሸነፍ ወዲህ ፣ በራስ ዐሊና በደጃች ካሣ መካከል
ምንም እንኳ ዕርቅ ቢደረግ ነገሩ ምቹ ጊዜ ለመፈለግ እንጂ ፣
ከልብ ሁኖ ለብዙ ጊዜ የሚቆይ ሰላም ለማድረግ አልነበረም ።
ስለዚህ ራስ ዐሊ እናታቸውን በዕርቅ መንገድ ካገኙ በኋላ ፣ ከጐ
ጃሙ ገዥ ከደጃች ጐሹ ጋር ስምምነት አድርገው ወደ ደምቢያ
ጉዞ ዠምረው ነበር ። በዚህ ጊዜ ፣ ደጃች ካሣ አንዳንዱን በየተራ
እንጂ እነዚህን ኃይል የሚሰማቸውን ሁለት ታላላቅ ገዥዎች
ባንድ ጊዜ ለመግጠም በዚያ ጊዜ የነበራቸው ኃይል ስለማይፈቅ
ድላቸው ፣ ደምቢያን ለቀው መውጫ መግቢያውን ወደሚያውቁ
ትና ተወልደው ወዳደጉበት አገር ወደ ቋራ ሔዱ ። ራስ ዐሊም
ደጃች ካሣ በጭራሽ የሸሹ መስሏቸው የደምቢያን ግዛት ለደጃች
ጐሹ ሰጥተው ወደ ሥፍራቸው ወደ ደብረ ታቦር ተመለሱ ።
ደጃች ጐሹም በጐጃም ግዛታቸው ላይ ደምቢያ ስለ ተጨመረ
ላቸው ደስ ብሏቸው ፣ ከልጃቸው ከብሩ ጐሹ ጋራ ጦራቸውን እያ
ደራጁ ተቀምጠው ሳለ ፣ ደጃች ካሣ የራስ ዐሊን መራቅና የደጃች
ጐሹን ብቻ መሆን በሰሙ ጊዜ ፣ ከቋራ ተነሥተው ደጃች ጐሹን
ለመውጋት በፍጥነት ወደ ጉር አምባ (ደምቢያ) ጥግ ገሠገሡ ።

ደጃች ጐሹ ዠግንነት ከኃይል ጋር የሚሰማቸውና የጦር
ሠራዊታቸው አያሌ ስለ ነበረ ፣ ከግጥሚያው በፊት አዝማሪያ
ቸው አዝማሪ ጣፋጭ የሚባለው በሠራዊቱ መካከል እንዲህ

እያለ ይዘምር እንደ ነበር ፡ አለቃ ወልደ ማርያም የመዘገቡት ታሪካዊ ጽሑፍ ያስረዳል ።(*)

«እያችሁት ብያ የኛን ዕብድ
አምስት ጋሞች ይዞ ጉር አምባ ሲወርድ ።
ያንጓብባል እንጂ መች ይዋጋል ካሣ
ወርደህ ጥመድበት በሸንብራው ማሳ ።
ወዶ ወዶ በሴቶቹ በነጉንጭት ለምዶ ።
ሐሩ ቋዱ ፡ ለውዞ ገውዞ አለ ቋራ
መንገዱ ቢጠፋ እኔ ልምራ ።»

ከዚህ በኋላ ፡ በኅዳር 19 ቀን 1845 ዓ. ም. ጦርነቱ እዚሁ ጉር አምባ (ጐርጐራ አጠገብ) እሚባለው ሥፍራ ላይ ሆኖ ሲዋጉ ለመዠመሪያ ጊዜ ደጃች ጐሹ ድል አድርገው የደጃች ካሣ ጦርም ተፈቶ መሸሽም ዠምሮ ነበር ። ነገር ግን ፡ ደጃች ካሣ ከሹማምንቶቻቸው ከነገልሞና ከጥቂቶች ደፋሮች ወታደሮቻቸው ጋር ሆነው በጥብቅ ሲዋጉ ፡ ደጃች ጐሹ በፈረስ እፊት ቀድመው 'በለው' እያሉ በሚያዋጉበት ጊዜ በጥይት ተመትተው ወደቁ ። ሠራዊታቸውም ገሚሱ ተበተነ ፤ ገሚሱም ወደ ደጃች ካሣ ዞረ ። ደጃች ጐሹም እንደ ቆሰሉ ጥቂት ቆይተው ሞቱ ።[1] በዚህ ጦርነት ላይ የባላምባራስ ገልሞን ዤግንነትና ጉንጩን በጦር መመታቱን አቶ ገሪማ አስፋፍተው ጽፈውለታል ።[2]

ደጃች ጐሹ ፡ ምንም እንኳን በጦርነት ተጋጥመው ቢቆስሉና በኋላም ቢሞቱ ፡ ደጃች ካሣ ብዙ ጊዜ በደጃች ጐሹ ቤት ተቀምጠው ስለ ነበረ ፡ ስለ ደጃች ጐሹ መቁሰልና መሞት ደስ ሳይላቸው ሥርዓተ መቃብራቸውን በክብር አስፈጸሙላቸው ። አስቀድሞም ከጦርነቱ በፊት ፡ «እባክዎ እኔና እርስዎ አባትና ልጅነንና መዋጋት አይገባንም ። ደምቢያን ለቀው ይሒዱልኝ» ብለው ለምነዋቸው ነበር ይባላል ። የሆነ ሆኖ ፡ ጐሹን ድል

* አዝማሪ ጣፋጭ በፊት የደጃች ካሣ የነበረ ፡ በኋላ ወደ ደጃዝማች ጐሹ የዞረ ነው ይባላል ።

1 የፉዜላ መጽሐፍ በገጽ 9 ላይ «ተማርከው ታሰሩ» ያለው ስሕተት ይመስላል ።

2 አባ ታጠቅ ካሣ ..... ገጽ 52—53



ካደረጉ በኋላ ፡ ራስ ዐሊ እንዳይቀየሙ ካህናትና አንድ ከርሳቸው ጋር የነበረ ሼክ ዐሊ የሚባል ልከው እንደ ነበረ ተመዝግቧል ።[1] ይሁን እንጂ መልእክቱ «መባሁ ፡ አንተም ታጥቀህ ጠብቀኝ» ለማለት ይሁን ወይም «በደረሰው ነገር ይቅርታ ፡ ወደፊት እንታረቅ» ለማለት ይሁን አይለይም ።

በዚህ ጊዜ ፡ አልቃሽ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ገጠመች ።

«ጐሹ እንደ አርዮ ፡ ዐሊ እንደ ዳዊት
ከጥንት አይዶለሞይ ተልኮ መሞት ።»[2]

ዳግም «ያንጓብባል እንጂ መች ይዋጋል ካሣ» ብሎ የተናገረው አዝማሪም ፡ በጠቋሚ ተይዞ እደጃች ካሣ ፊት ቀረበ ። «እንደምን ብለህ ሰደብኸኝ ?» ብለው ቢጠይቁት ፡ ከጭንቀት የተነሣ ምሕረት ያገኘሁ መስሎት ፡—

«አወይ ያምላክ ቁጣ ፤ አወይ የግዜር ቁጣ
አፍ ወዳጁን ያማል ሥራ ሲያጣ
ሽመል ይገባዋል ያዝማሪ ቀልባጣ»
ብሎ በራሱ ስለ ፈረደ ፡ በሽመል ተደብድቦ ሞተ ይላሉ ።[3]

በዚህ ጊዜ ፡ ራስ ዐሊ የደጃች ጐሹን ድል ሆኖ መሞት ሲሰሙ ፡ በመጋቢት 27 ቀን 1845 ዓ. ም. (እንደ አው.አቆ. ሚያዝያ 5 ቀን 1853 ዓ. ም.) ደጃች ያዘውን ፡ ደጃች በለውን ፡ ደጃች አቤን ፡ የላስታውን ብሩ ዐሊን አድርገው ፡ ከደጃች ውቤም ወታደር ጨምረው ላኳቸው ። እነዚህም እንደዚያው እንደ ደጃች ጐሹ ጐርጐራ ፡ ብችኝ ከተባለው ቀበሌ ተዋግተው ድል ሆኑ ። ከዚህ በኋላ ፡ ደጃች ካሣ ሰውም ብረትም እየሰበሰቡ ራስ ዐሊን ለመውጋት ይዘጋጁ ዠመር ። ራስ ዐሊም በተለመደው የንቀት አነጋገር ፡ «ምንም ቢሆን ለካሣ ጦር አልጭንም» እያሉ ይግደረደሩ የነበረው ቀረና ፡ አሁን ጦርነቱ በሥልጣናቸውና በቀጥታ

1 አለቃ ወልደማርያም ገጽ 2 — 4

2 መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ ምዕ. 11 — 12

3 አለቃ ዘነብ ገጽ 13 — 14

በራሳቸው ላይ ዐይኑን አፍጦ ስለ መጣ ፤ የጦር ሠራዊት አዘጋጅ ተው ጦርነት ከማድረጋቸው በፊት የደጃች ጐሹ ልጅ ፤ ብሩ ጐሹ ፤ ከርሳቸው ጋር ሆኖ ደጃች ካሣን እንዲወጋ ሲያባብሉት ፤ እንዲሁም ደጃች ካሣ ፤ ብሩ ጐሹን «ካባትህም ያጣላን ጊዜ ነው ። አሁንም ያባትህን ግዛት እመልስልሃለሁ» በማለት ተስፋ ሰጥ ተው ፤ ከጐናቸው እንዲሰለፍ ለማግባባት ይጣጣሩ ነበር ። ብሩ ጐሹ ግን ፤ ሁለቱ ተዋግተው ሲተላለቁ እኔ ተርፌ ወደ ሥልጣን እሸጋገራለሁ በሚል ምኞት ለጊዜው ከማንኛውም ወገን ሳይሆኑ እንዲሁ ተራቸውን ይጠብቁ ነበር ።

ከዚህ በኋላ ፤ ራስ ዐሊ ሰኔ 23 ቀን 1845 ዓ. ም. ቁጥሩ እስከ መቶ ሺህ የሚደርሰውን የጦር ሠራዊታቸውን ይዘው እጣና ሐይቅ አጠገብ ጕርጕራ በተጠጉ ጊዜ የደጃች ካሣን ጦር በሩቁ አይ ተው ፤ «ሠርገኛ እንዳንለው በዛ ፤ ጦረኛ እንዳንለውም አነሰ» ብለው አሁንም የምፀትና የንቀት ቃል ተናገሩ ። የሆነ ሆኖ ፤ ሁለቱ አይሻል (ጕጃም) ላይ ተጋጥመው ፤ ጦርነቱም ተፋፍሞ ሲዋጉ የራስ ዐሊ ሰው ሽሽት ዠምሮ የደጃች ካሣ ሰው ያባርር ዠመር ። ራስ ዐሊም በናቁት ጦር ሲሸነፉ ከአይሻል ፈቀቅ ብለው ወደሌላ ሥፍራ ሔዱ ። በዚያም የተረፈውን ጦራቸውን ሰብስበው እንደገና ከፊተኛው ውጊያ በ3ኛው ወር ፤ በሰኔ 23 ቀን 1845 ዓ. ም. ተጋጠሙ ። ዳሩ ግን ፤ የደጃች ካሣ ጦር አሸና ፊነት ሲሰማው ፤ የራስ ዐሊ ሰው የካሣን ጦር በፍጹም የማይበገር መሆኑን በፍርሃት እያመዛዘነ ለሽሽት ያወላውል ዠመር ። ይሁን እንጂ ፤ ራስ ዐሊ በመጨረሻ ባላቸው ዐቅም በርትተው ከተከላከሉ ወዲህ አሁንም ደጃች ካሣ ድል ስላደረጓቸው ፤ «ይህ በትር የእግዚአብሔር ነው እንጂ የካሣ አይደለም» ብለው ተስፋ ቆረጡና በ1845 ዓ. ም. በዚሁ በሰኔ ወር መጨረሻ ደውለው ደምበጫ ገቡ ። ከዚያም በግሥጋሤ ሔደው ማኅደረ ማርያም ገቡ ። በዚያም ካህናቱ ቀርበው «ድል አድራጊው እርስዎን ሲል መጥቶ ደብራችንን ይበረብርብናል» ብለው መፍራታቸውን ስለ ገለጹላቸው ወደ ደራ ሸሹ ። በዚያም የደራው ባላባት ዋቄ ዲቦ ይዞ አሰራቸው ። በዚህ ጊዜ የሸዋ ንጉሥ ኃይለ መለኮት ሰምተው ከአንኮበር ወደ ደራ ዘምተው ፤ ዋቄ ዲቦን ወግተው ካሰሩ በኋላ ፤ ራስ ዐሊን ፈተው አብረው ካሣን ለመከላከል አስበው ነበር ።



ነገር ግን ፤ የደጃች ካሣን በትር ደጋግመው የቀመሱት ራስ ዐሊ ፤ «ይህ ሰው እኛን ለመቅጣት ከአምላክ የተላከ ነውና አንችለ ውም ። እርስዎም ወደ አገርዎ ተመልሰው ቢከላከሉ ይሻላል» ብለው መክረዋቸው ኃይለ መለኮት ወደ አንኮበር ተመለሱ ። ባንዳንድ ጽሑፍ ደግሞ ፤ ኃይለ መለኮት ዐሊን ይዘው አንኮበር ከሔዱ በኋላ ፤ ወደ አገሬ መመለስ እፈልጋለሁ ቢሏቸው ሸኚ ጨምረው ላኳቸው የሚል ይገኛል ። የሆነ ሆኖ ፤ ራስ ዐሊ በየጁ ዐልፈው ራያ ወሰን ገብተው ተቀምጠው ብዙ ቀን ከቆዩ በኋላ ሞቱ ።(1)


አለቃ ዘነብ የዚህ የአይሻልን ጦርነት እንደዚህ ሲሉ አስፍ ረውታል ። «በሰኔ ራስ ዐሊ የዶምቢያን ፤ የቤጌምድርን ጦር ሁሉ አስከትተው ወደ ጐጃም ሔዱ ። በሰኔ23 ቀን አይሻል ላይ ተዋጉ ፤ ብዙ ሰው አለቀ ። ደሙ እንደ ጐርፍ ሆነ ፤ ሬሳውም እንደ ካብ እስቲሆን ድረስ ፤ ራስ ዐሊም ሸሹ ። ድል የደጃች ካሣ ሆነ ። ወታደሩን አገሩንም ሁሉ ነፍጡንም ደጃች ካሣ ያዙ ።»

በበኩላቸው አለቃ ወልደማርያም የውጊያውን ጽናት ፤ የሰዉን እልቂት ሲገልጹ እንደዚህ ብለዋል ። «እግዚአብሔር ኃይሉን ለካሣ ሰጥቶ የራስ ዐሊ መንግሥት አልቋልና ቢገጥሙ የራስ ዐሊ ሰው እንደ ቅጠል ረገፈ ። የሰውም ሬሳ ቢነባበር በአይሻል ሜዳ ከአውድማ የገባ ነዶ መሰለ . . . »(2) የሆነ ሆኖ ደጃዝማች ካሣ ከዚህ ድል በኋላ ኃይላቸው እየገነነ ሔዶ ወደፊት ዋና አማካሪ የሆናቸው ፕሎውዴንና ሊቀመኳስ ያደረጉት ቤል የተገናኙዋቸው ከራስ ዐሊ ድል መሆን በኋላ ነው ።

---

1 አለቃ ዘነብ ..... ገጽ 15 — 17

2 መጽሐፈ ታሪክ ዘቴዎድሮስ — Chronique De Theodore - M. Viedailnlet ገጽ 5 — 6



ራስ ዐሊ አሉላ
(ከአባ ማስያስ መጽሐፍ)

# ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት

*የደጃዝማች ብሩ ጎሹ ዣብት ፤ የደጃች ውቤ መሸነፍ ፤ ደጃች ካሣ ሥርዓተ ንግሥ ተደርጎላቸው ቴዎድሮስ ተብለው እንደ ነገሡ*

የራስ ዐሊ መሸነፍ ፣ የዘመነ መሳፍንትን ፍጻሜ የሚያበሥር ታላቅ ደወል ነው ። ከሰባ ዓመት በላይ ከዳዊት ፣ ከሰሎሞን እን ወለዳለን ፣ የፋሲል ፣ የኢያሱ ዘር ነን የሚሉትን የነገሥታት ዘር እንደ ልባቸው እየለዋወጡ ፣ ለስሙ በዙፋን እያስቀመጡ ግንብ ጠባቂ ብቻ በማድረግ ሙሉውን የእንደራሴነቱን ሥልጣን ለራሳ ቸው ይዘው ሲያስተዳድሩ የኖሩት ፣ ከየጁና ከወሎ የኦሮሞ ባላ ባት የሚወለዱት የመጨረሻው መስፍን ራስ ዐሊ በሰኔ 23 ቀን 1845 ዓ. ም. የተሸነፉለት የመሳፍንት አገዛዝ ለዘለቄታው አከ ተመ ። በዚህ ፈንታ ከዚህ ጊዜ ዠምሮ የነገሥታት አገዛዝ ከቴ ዎድሮስ በዮሐንስ በኩል ዐልፎ እስከ ምኒልክ ፣ እስከ ኃይለ ሥላሴ ድረስ ባዲስ መልክ እየፋፋ መጣ ። ቢሆንም ከመሳፍንቱ ውስጥ እንደ ታላቁ ራስ ዐሊ ፣ እንደ እነታላቁ ራስ ጉግሣ ያሉ ለኢትዮጵያ ታላቅነት የሠሩ በዚያው በዐቅማቸውና በደረጃ ቸው አገርን እንዳገለገሉ መዘንጋት የለበትም ።

ደጃች ካሣ ፣ ከዚህ ከፍተኛ ድል በኋላ የደምቢያንና የቤጌ ምድርን ግዛት በደንብ አደላድለው በመያዝ ፣ ታማኞቻቸውን በየ ሥፍራው ካስቀመጡና ታላላቆቹ ከተሞች ጐንደርና ደብረ ታቦር ከነቤተ መንግሥታቸው ፣ ከነሀብታቸው በእጃቸው ሲገቡ ከእር ሳቸው የበለጠ እንደሌለ የታወቀ ሆነ ። ጐንደርን ከያዙ በኋላ ዓመቱን ዕረፍት አድርገው የጐጃምን ግዛት አረጋግጠው ለመያዝ ከጉራምባው ጦርነት ወዲህ ፣ አባትየው ደጃች ጐሹ ሲሞቱ ልጅ የው ደጃች ብሩ አምልጠው ዳሞት ገብተው ነበርና እርሳቸውን ለማባረር ሔዱ ። በሔዱም ጊዜ ዙረትና ሽሽት የሰለቸው የደጃች ብሩ ሰው እየመጣ ገባላቸው ። ብሩም ምንም ያህል መቋቋም

ሳያደርጉ ፣ በጐጃም ተይዘው ወደ ደጃች ካሣ በቀረቡበት ሰዓት ደን ጊያ በማጅራታቸው ተሸክመው በመውደቅ ምሕረት ለመኑ ።[1]

ከዚህ በኋላ የደጃች ብሩን ሀብትና የጦር መሣሪያ ሚስትዮዋ ይዘው በጂበላ ተራራ ተቀምጠው ነበርና ደጃች ብሩንና የቤት ዮዋን ወንድሞች አስረው እፊት እፊት እያስሔዱ ከተራራው ጥግ ሲደርሱ ፣ «አምባውን ልቀቂ ፤ አለዚያም ወንድሞችሽን ግደ ያቸው» ብለው የማስፈራሪያ ቃል ላኩባቸው ።(*) ሴትዮዋም ከባ ልዮው ጋር ውስጡን ጠበኛ ኖረው ፣ «ለባሌ ለብሩ አይስጡኝ እንጂ አምባዎን ይቀበሉኝ» ብለው ላኩ ። በዚሁ አምባውን ከነ ሀብቱ ተቀብለው የጐጃምን ግዛት ካደላደሉ በኋላ ፣ ለአምባው ብላታ ደስታ የሚባሉትን ሾመው በሰኔ ወር 1846 ዓ. ም. ወደ አምባጫራ ፊታቸውን አቀኑ ።

በ አ ም ባ ጫ ራ ም ፣ በጐንደርም ሲዘዋወሩ አስታርቃለሁ በሚል መልክ አቡነ ሰላማ መጥተው ተገናኝተው ነበርና ጳጳሱ አንደኛ ፣ የደጃች ካሣን ብርታት በመመልከት ፣ ሁለተኛ ከዚህ በፊት ከጸጋ ልጆች በኩል የተዋሕዶ ሃይማኖታቸውን ከማጽናት የተነሣ ፣ የክርስቶስ አምላክነት በጥምቀት በጸጋ ነው የሚሉትን በገዘቱበት ምክንያት የደረሰባቸው መከራና ስደት የሚታወስ ነው ። አሁን ግን ፣ ደጃች ካሣ ወደፊትም ሲነግሡ ካሮች የሚታገ ሉበትን ፣ «ወልደ አብ ወልደ ማርያም ፣ በተዋሕዶ ከበረ» የሚለ ውን እምነት እንደሚያጸኑ ለጳጳሱ ታመኑላቸው ።

ከጸጋ ልጆች ጉን ፣ «በቅብዓት ከበረ (አምላክ ሆነ)» ለሚሉ ትም የደብረ ወርቅ ቅባቶች ፣ «ወልድ ቅብዕ ነው ፤ ቀቢና ተቀቢም ርሱ ራሱ ነው እንጂ በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቶ የጸጋ ልጅ ፣ በቅ ብዓትም የተነሣ አምላክ አልሆነም» የሚል ተዘጋጅቶ ሐምሌ 8 ቀን 1847 ዓ. ም. በጽሕፈት ታወጀ ። ደጃች ካሣ ፣ « አቡነ ሰላማ የሚሉትን ሃይማኖት ያልተቀበለ ከላይ አንገቱ ፣ ከታች ባቱ ይቆ ረጣል» ሲሉ ዐዋጁን በዐዋጅ አጸኑ ። አቡኑና ደጃች ካሣ ጉን

1 አለቃ ዘነብ ገጽ 17

* ወንድሞችሽን ግደያቸው ማለት ፣ ትርጉሙ እምቢ ካልሽ እኔ እገ ድላቸዋለሁ ማለት ነው ።



ለጐን ሆነው ይኸን ዐዋጅ ሲያስነግሩ ፣ ተራው ሕዝብ ክርስቲያ ኑና ለዚህ ሃይማኖት በፊተኛው ጊዜ ይቆረቆሩ የነበሩት ሁሉ ዐዋጁን በደስታ ፣ በጭብጨባ ተቀብለው ፣ «ከዚህ ሃይማኖት አን ወጣም ። ቃልዎ ይድረስን» እያሉ በመሐላ አጸኑ ።

በነርሱ አንጻር ፣ የጐንደርና የሸዋ ሊቃውንት ካቶሊኮችም የሁለት ባሕርይንና የጸጋን እምነት በማገናዘብ ፣ ከተዋሕዶ ርቀው የነበሩት አንዳንዶቹ በፍርሃት ግዘቱን ሲቀበሉ ፣ የቀሩት ደግሞ አንቀበልም እያሉ በዚህ ምክንያት ከውስጣቸው የታሰረም የተ ጋዘም አለ ። በዚህም ጊዜ የደጃች ውቤ ልጅ ጎንጉልና በተለይ ብላታ ኮከቤ የሚባሉ ብልጣ ብልጥ በፊት ከደጃች ውቤ ጋር ሆነው ወደ አውሮፓም ፣ ወደ ምጥዋም የሚላላኩ ነበሩ ። ኮከቤ በዕርቅ እያመካኙ ወደ ደጃች ካሣ እየተመላለሱ ላዩን ለደጃች ውቤ ፣ ውስጡን ከኃያሉ ከደጃች ካሣ ጋር ለመስማማት እመዋ ከር ላይ ነበሩ ።

ደጃች ካሣ ፣ በዚህ ዐይነት ድርጅት ከአቡኑ ጋር በመስማማት እስከ ታኅሣሥ ወር 1847 ዓ ም ዕረፍት አድርገው ከቆዩ በኋላ ፣ ወደ ደጃች ውቤ ለመዝመት ዐቀዱ ። ከዘመቻው በፊት ለደጃች ውቤ በሰላም እንዲገቡ ፣ ያልገቡ እንደሆነ ለርሳቸው እንደማይ በጃቸው አስረድተው የማስጠንቀቂያ መልእክት ላኩባቸው ። ውቤ ከጥንት ዠምሮ ደጃች ማሩና ራስ ይማም ፣ ደጃች ሰባጋዲስና ራስ ማርዬ በሚዋጉበት ጊዜ ፣ በዘዴና በብልጠት ካንዱ ጐራ ወደ ሌላው እየተዘዋወሩ ሌሎቹን በማዋጋት ከአሸናፊው ጋር በጋ ብቻ ፣ በአምቻ እየተዛመዱ ራሳቸውን ከአደጋ ጠብቀው ይኖሩ ነበር ። አሁንም ከራስ ዐሊ ጋር ተዋግተው ቢሸነፉም ፣ ለዐሊ እየገበሩ በሰላም መጥፎውን ጊዜ አሳልፈው ፣ ጳጳሱም አቡነ ሰላማ ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው በደብረ ዳሞ ገዳም ቢሆኑም ፣ በዚ ያው በግዛታቸው ስለሚገኙ ባሠሩት በደረስጌ ማርያም ለመን ገሥ አመቺ ጊዜ ሲጠባበቁ ፣ በመካከሉ የደጃች ካሣ ድል አድራ ጊነት እየተቀጣጠለ በላያቸው ላይ ዐይኑን አፍጥጦ መጣ ። የነ በረ ብልጠታቸውም በዚህ ጊዜ ሊያዋጣቸው አልቻለም ።

ስለዚህ እንዲገቡ የሚለው የደጃች ካሣ መልእክት ሲደር ሳቸው ፣ «እያ ! ምንኛ የጠገበ ነው ? ሳልዋጋ ይገባል ብሎኝ ነው» ብለው በዘመኑ የስሜንኛ አነጋገር ለወገኖቻቸው ከተናገሩ በኋላ ፣

«አልገባም» የሚል የመጨረሻ መልስ ሰጡ ። ጳጳሱም «ለደጃች ካሣ ቢገቡ ይሻላል» ብለው ቢያባብሏቸው ውቤ አልተበገሩም ።

ከዚህ በኋላ ፣ ደጃች ካሣ በዐዋጅ ጦራቸውን አስከትተው ፣ «ከኔ የተለየህ ለራስህ ዕወቅ ፤ በምን ጠፋሁ እንዳትል ። አይዞህ ወታደር ! እኔ ደስ ከሚልህ (አገር) አገባሃለሁ» የሚል ቃል ዐወጁ። ከዚሁም ዐዋጅ መደምደሚያ ላይ ሰው ሁሉ ከራስ ዐሊ ውድቀት ወዲህ «መቸ ይነግሡ ይሆን ? ስመ መንግሥታቸውስ ማን ይባል ይሆን ?» እያለ መጠያየቅ አብዝቶ ነበርና ፣« . . . እኔ በመራሁህ ተንዝ ስሜን (መጠሪያዬን) ስሜን (በስሜን አገር) እነግርሃለሁ» ብለው ፣ ወደ አምባጫራ ዐልፈው ወገራ ፣ ከወገራ ወደ ስሜን ሔደው ደረስጌ አጠገብ ፣ በተለይ ቧሂት ከሚባለው ሥፍራ ከሚጠባበቁዋቸው ከደጃች ውቤ ጋር ሩቅ ለሩቅ ተያዩ።

በዚህ ጊዜ ፣ ከራስ ዐሊ ጋር የነበረው ዦን ቤል በኋላ ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ብለው የሾሙት ፣ በአሁኑ ጊዜ ከርሳቸው ጋር ነበርና በመነጥር አይተህ ንገረኝ ብለውት የደጃች ውቤን ጦርና ድንኳኑን አይቶ በነገራቸው ጊዜ ፣ «እያሳድረኝ አላሳድረውም» ብለው «ፎከረው እንኳን ይኸን ቁርጥማታም ወሎን መትቼ ፣ የሸዋውን ንጉሥ እይዘዋለሁ ። ስሜን ስሜን እነግርሃለሁ ያልሁህ ወታደር ፣ ስሜ ቴዎድሮስ ነው» ብለው ተናገሩ ። ወዲያው በደጃች ውቤ ጦር ሠፈር ብዙ ባለጠበንጃ አለ እየተባለ ይወራ ነበርና ወታደራቸውን ለማደፋፈር ሲሉ ፣ «የውቤ ነፍጥ ፣ የውቤ ነፍጥ ቢልህ ፣ የተለጐመው ጨርቅና ባሩድ ነው ፤ አይነካህም . . . ሁሉንም አሳይሃለሁ» ብለው ተዋጊውን ከማበረታታት ጋር ፎከረው ፣ ጦርነቱ በየካቲት 3 ቀን 1847 ዓ. ም .ተዠመረ ።

ሁለቱም ወገኖች ፣ በጀግንነት ሲዋጉ የጦርነቱ ዕድል ወደ ማን እንደሆነ በሚያወላውልበት ጊዜ ፣ አንዱን የጦርነት ጐራ ደህና አድርጎ መክቶ የነበረው ደጃች እሸቴ የሚባለው የደጃች ውቤ ልጅ በጥይት ተመትቶ ከፈረሱ ላይ ወደቀ ። በዚህ ጊዜ በሠራዊቱ መካከል ፍርሃትና ድንጋጤ ሆነ ። በዚህ ላይ ደግሞ ያስታራቂ መላክተኛ ሆኖ ከደጃች ውቤ ፣ ወደ ደጃች ካሣ ሲመላለስ የነበረው ብላታ ኮከቤ የጦርነቱን አዝማሚያ በመመልከት ከደጃች ውቤ ከድቶ ከነጭፍራው ወደ ደጃች ካሣ ዞረ ። በመጨረሻም ራሳቸው ደጃች ውቤ እንደ ቆሰሉ ተማርከው ፣ የማረካቸው



የደጃች ካሣ ወታደር እየነዳቸው ወደ ጌታው ቀርቦ ፣ «እንኳን ቀናዎት» አላቸው ።

ደጃች ካሣ ውቤን እንደ ተያዙ ሲያዩዋቸው ፣ «እሳቱ የመይሳ ልጅ . . . አንት ቆፍጣጣ(*)፤ ቁርጥማታም ሽማግሌ ! በክብረት (አክብሬ) ግባ ብዬ ብልክብህ ምን ብለህ ሰደብኸኝ ? እሁንም ነፍጤንና ገንዘቤን አግባ» ብለው በተቆጧቸው ጊዜ የራስ ገብሬ የልጅ ልጅ ፣ የስሜንና የትግሬ ጌታ የነበሩት መከረኛው ውቤ «እግዜር ያሳይዎ ፤ የነበረኝ ነፍጥና ገንዘብ አንድ ሳያመልጥ ከእጅዎ ገባ ። ሌላ ምን አለኝ ?» ብለው ቢመልሱ ፣ የደጃች ውቤ የደለበ ብዙ ሀብትና መሣሪያ እዚያው ስሜን ቤቴል (አምባ ጠዘን) በሚባል ተራራ ተከማችቶ መቀመጡን ካሣ ያውቁ ነበርና ፣ «የግድ ትሰጠኛለህ ወስዳችሁ እሰሩ» ብለው አዘዙ ።[1]

በጦርነቱ ላይ ከደጃዝማች ካሣ ወገን በጅሮንድ አደላና አዛዥ እሸቱ ሲሞቱ ፣ ከደጃች ውቤ ወገን ደጃዝማች ማዕጠንቱና ሲዋጉ ከፈረስ ቆስለው የወደቁት ልጃቸው ደጃች እሸቴ ሞቱ ። እነዚህ በጣም የታወቁ ስለሆኑ ጸሐፊዎቹ አወሱዋቸው እንጂ በዚህ ጦርነት ስማቸው ያልተወሳ ብዙ ሹማምንትና ብዙ ወታደር ከሁለቱም ወገን እንደ ሞቱ የታወቀ ነው ። ያገራችን የዚያን ዘመን ጸሐፊ ይኸን የመሳሰለውን ታላላቅ ጦርነት ሁሉ ዝርዝር ሁኔታ ሳያሰፍር በአጫጭር መሥመሮች ስለሚወስናቸው ፣ በጦርነቱ ላይ ከሁለቱም ወገን ያሉት ከሹማምንቱም ፣ ከወታደሩም ጀግንነት ያሳዩትን አይገልጽም ። በሁለቱ ወገን ያለውንም የጦር ሠራዊትና የመሣሪያ ቁጥር ፣ ጦርነቱም የቆየበትን ሰዓት ስለማይጠቅስ ፣ ምንም እንኳን የርስ በርስ የማያኰራ ጦርነት ቢሆንም ፣ ብዙ ታሪክ እንደ ተዳፈነ መቅረቱ ያሳዝናል ።

የሆነ ሆኖ ፣ የካቲት 3 ቀን ደጃች ካሣ ይኸን ድል ካገኙ በኋላ በሦስተኛው ቀን ፣ በየካቲት 5 ቀን 1847 ዓ. ም. ራሳቸው ደጃዝማች ውቤ እነግሥበታለሁ ብለው ባሠሩት ፣ በነዶክተር

---

* በዛሬው አማርኛችን ጐፍጣጣ ወይም ጐባጣ ሽማግሌ

1 አለቃ ዘነብ ገጽ 11 — 12 ፣ አለቃ ወልደ ማርያም ገጽ 6 — 7 ፋዜላ ገጽ 11 — 12
Histoire Pel. et Religieuse d'Abyssinie - J.B. Coulbeaux - Vol. II pp. 407-417

ዊልሄልም ሺምብር እጅ አማምረው ባስጌጡት በደረስጌ ማርያም ዕጨጌው በግራ ፣ ጳጳሱ በቀኝ ተቀምጠው መጽሐፈ ተክሊል እየተነበበ በአቡነ ሰላማ እጅ ሥርዓተ መንግሥት ተደርሶላቸው በመቀባት ቴዎድሮስ በተባለው ስመ መንግሥታቸው በይፋ ነገሡ ።(1) ሲነግሡ የ35 ወይም የ36 ዓመት ሙሉ ጐልማሳ ናቸው ። በዚሁም ቀን ወይዘሮ ተዋበች አብረው ቆርበው ፣ ለር ሳቸውም አክሊል ተደርጎላቸው የእቴጌነት ደረጃ ተቀበሉ ።(2)

ከዚህ በኋላ ፣ ዐዋጅ ነጋሪ ወጥቶ ነጋሪት እየተጐሸመ ፣ «ከዛሬ ዠምሮ ደጃዝማች ካሣ ስማቸው ፣ 'ቴዎድሮስ' ተብሎ ንጉሠ ነገሥት ሆነዋልና ደጃዝማች ካሣ ብለህ የጠራህ ትቀጣ ለህ» ተብሎ ተነገረ ። ከሌላው ሁሉ ስመ መንግሥት ቴዎድሮስን የመረጡበት ምክንያት ግልጽ ነው ። ቴዎድሮስ በአምስተኛው መቶ ዓ.ም. መዠመሪያ ላይ በሰማዕትነት የሞተ የግሪክ ቅዱስ ነበር ። ከዚያ ወዲህ ፣ በዚህ ጻድቅ ስም ብዙ የአውሮፓ የክርስቲ ያን ነገሥታትና ጳጳሳት ክርስቲያኖችም ይጠሩበታል ። በኢት ዮጵያም ያፄ ዳዊት ልጅ ፣ ያፄ ዘርዓ ያዕቆብ ወንድም በ1404 እና በ1407 ዓ. ም. መካከል የነበረው ንጉሥ ለመዠመሪያ ጊዜ ተጠርቶበታል ። በማናቸውም ዘመን በኢትዮጵያ አስተዳደር በታበላሸበት ፣ ድልወትና ምንዝርና በበዛበት ሰዓት ነገሩ ከካህ ናት ፣ ከመነኮሳት ወይም ከባሕታውያን እየመነጨ ፣ «ቴዎድሮስ የሚባል ንጉሥ ከወደ ምሥራቅ ተነሥቶ በዘንግ (ያለ ሰይፍ ፣ ያለ ጦርነት) ይገባል ፤ የተበላሸውን አስተዳደር አስወግዶ ሺህ ዓመት ይነግሣል ፤ በዘመኑም ሰላምና ትክክለኛ ፍርድ ይሆናል ፣ ግዛቱም እስከ ባሕር ነው» እየተባለ በሕዝብ አፍ ይነገራል ።

በዚሁ መሠረት ፣ በኋሁ በራስ ዐሊ ዘመን ካፄ ዮሐንስ ሣልሳይ ቀደም ብለው ላጭር ጊዜ በንጉሠ ነገሥቱ ዙፋን ላይ በተቀመጡት ባፄ ሣህለ ድንግል ዘመነ መንግሥት ፣ አንድ ዕጓለ አንበሳ የሚባል መነኩሴ በቀሃ ወንዝ (ጐንደር አጠገብ) በኩል ወደ ጐንደር ጥሩምባ እያስነፋ መጥቶ «ነግሻለሁ» ሲል ዐወጀ ። ስሜም ቴዎድሮስ ነው ፣ ግዛቴም እስከ ባሕር ዳርቻ ፣ ዘመኔም እስከ ሺህ ዓመት ነው» እያለ እየሰበከ ጐንደር ከተማ

1 የዐድዋው (መምሣህ) ተወላጅ ጽፈውት Vicende Del Ethiopia በሚል አርእስት ኮንቲ ሮሲኒ ያሳተሙት ገጽ 517
2 የኢትዮጵያ ታሪክ ካፄ ልብነድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ ገጽ 343



ሲገባ ፣ ዐፄ ሣህለ ድንግል አሲዘው በጉባዔ አንገቱን በሰይፍ አስቆርጠውታል ።(1)

አሁንም በራስ ዐሊ ዘመን የአስተዳደሩን መበላሸትና የቴ ዎድሮስን አነሣሥ አለቃ ዘነብ ከዚሁ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ እንደዚህ ሲሉ አትተዋል « . . . ዘመዶቻቸው (የራስ ዐሊ) እጅግ ደሃ በበደሉ ጊዜ የአበሻ ሰዎች ሁሉ ፍርድን ፣ መልካም መሥራትን ፣ እግዚአብሔርን መፍራት ፣ በተዉ ጊዜ በስም ክርስ ቲያን ተብለው በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ፈንታ አስማት ፣ ምንዝርና ስካር ፣ ቧልትና ጥመት ባደረጉ ጊዜ እግዚአብሔር አምላክ ቀናዒ ነውና ንጉሥ ቴዎድሮስን አስነሣ ፣ ሁሉን የሚ ቀጣ»(2)ስለዚህ በዚሁ መንፈስ ካሣ ታላላቆቹን መሳፍንት ዐሊንና ውቤን ከደመሰሱ በኋላ ፣ የቴዎድሮስን ሥያሜ መርጠው ዳግማዊ ቴዎድሮስ ሆኑ ማለት ነው ።

ዐፄ ቴዎድሮስ በደረስጌ ማርያም ሥርዓተ ንግሣቸውን ካከ በሩ በኋላ ፣ ቤቴል ወደሚባለው የደጃች ውቤ ሀብት ወደ ተከማቸ በት ተራራ ሔዱ ። በደረሱም ጊዜ የደጃች ውቤ ልጅ ፣ ደጃች ጓንጉል ፣ በፊት ከጦርነቱ ቦታ ሸሽተው እዚሁ ተራራ ሥር ይገኙ ስለ ነበረ ፣ አሁንም የንጉሡን መምጣት ሲመለከቱ ለመመ ከት ምንም ዐቅም እንደሌላቸው በመረዳት ሮጠው ወደ ንጉሡ መጥተው ፣ በተራራው ያለውን ሀብት ለማስረከብ ዝግጁ መሆ ናቸውን ፣ በተራራው ላይ ያለው ሀብት መብዛቱን ፣ ለቁጥር እስኪያስቸግር ድረስ የወርቅና የብሩ ዕቃ ፣ ብርጭቆና ብርሌው እንደ ሣር ቅጠል መበርከቱን ጸሐፊው አለቃ ዘነብ አመልክተው ከዚሁ ጋር በማያያዝ ሁለት መድፎች ጥይታቸው ለሸክም ያስቸ ገረ ፣ ጥሬው ብርም በብዛት ተገኝቶ ለመኳንንትም ፣ ለሠራዊትም

1 አለቃ ዘነብ ገጽ 3
2 አለቃ ዘነብ ገጽ 19 ፣ ቶዜላ ያሳተሙትና ያለቃ ወልደማርያም የጻፉት ታሪክ ለማስረከብ የተገደደው እርሱ ከጦርነቱ ቦታ ሸሽቶ ከሔደ ወዲህ አባቱን አስረው እንደ ያዙ ለአባትህ ትራራ እንደሆነ አምባውን አስረክብ ፣ እምቢ ታልክ እገላቸዋለሁ ብለው ስለ አስፈራሩት ለአባቱ ራርቶ አስረከበ ብለዋል ። ቶዜላ ገጽ 11 አለቃ ወልደማርያም ገጽ 7
የዘነብ ጽሑፍ ቤቴል የሚለው

መታደሉን ይጠቅሳሉ ። ሁለተኛው ጸሐፊ በበኩላቸው አንድ ጋን መርፌና እሾህ ሳይቀር መታየቱን ፣ ብዙ የታሰሩ መኳንንት ተገኝተው መፈታታቸውን ፣ ንጉሠ ነገሥቱ በአምባ ጠዘን የነበረውን ዕቃ ሁሉ ተቀብለው ካበቁ በኋላ ደጃች ውቤን አስጠርተው ፣ «ይህ ሁሉ ገንዘብ ምን ይሆነን ብለው ከአምባ አስቀመጡት ?» የሚል ጥያቄ እንዳቀረቡላቸው ፣ «ለክፉ ቀን ይሆናል» ብዬ ነው ብለው መመለሳቸውን ፣ ቴዎድሮስም «ከዛሬ የሚከፋ ምን ቀን አለ የማይበሉት ፣ ንፍገት ነው እንጂ ፣ ወይ አስቀድሞ መብላት ወይም ለወታደር መስጠት ይሻል ነበር እንጂ ፣ ያኖሩትን ከበሉ ምን ክፉ ቀን አለ» ብለው እንደ መለሱላቸው ያረጋግጣሉ ።(1) የወርቁ ቁጥር መጠኑ አይታወቅም ። ለግን በጸፈው ላይ 40,000 የማሪያ ቴሬዛ ብርና 7,000 ጠበንጃ አብሮ መገኘቱን ለይቶ ይጠቅሳል ። (2)

ከሁለቱ ጸሐፊዎች አለቃ ዘነብ የአምባውን ሀብት የተረከቡት ሥርዓተ ንግሣቸውን በደረስጌ ካከበሩ በኋላ መሆኑን ሲጽፉ ስማቸው ያልታወቀው ጸሐፊ ደግሞ ከንግሡ በፊት እንደ ተረከቡ አድርገውታል ። አለቃ ዘነብ የራሳቸው ያፄ ቴዎድሮስ ጸሐፊ ትእዛዝ ስለ ነበሩ ፣ ስማቸው ያልታወቀው ጸሐፊ ግን ካፄ ቴዎድሮስ ሞት በኋላ ባፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት በወሬ ጥየቃ የጻፉት ስለሆነ ፣ ምናልባት ከርሳቸው የአለቃ ዘነብን አባባል መቀበሉ ይቀላልና እንደ አለቃ ዘነብ አጻጻፍ ቴዎድሮስ በየካቲት 3 ቀን አሸንፈው በየካቲት 5 ቀን ሥርዓተ ንግሣቸውን ካከበሩ በኋላ ወደ ሀብት ስብሰባ ተዛውረዋል ማለት ነው ።

በዚህ መካከል ጐንደርን ያህል ወይም አክሱምን የመሰለ ታሪካውያን መናገሻ ከተማዎች እያሉ ፣ ባንድ የአውራጃ ከተማ በደረስጌ የነገሡበትን ምክንያት አናውቀውም ። ጐንደርም በእጃቸው ገብቷል ፤ ትግሬንም በውቤ ላይ ድልን ካገኙ በኋላ ለባልጋዳ አርአያ ድምፁ ሰጥተው እጅ ያደረጉት ያህል ነው ። ምናልባት ለመንግሥ ወደነዚያ ከተሞች በመጓዝ ጊዜ አናባክን ፤ እዚሁ በአፍላው ይንገሡ ተብሎ ይሁን ወይም በሁለቱም ታላላቅ ከተሞች በተለይ በጐንደር ምንም ከተማው ቢያዝ

1 ቶዜላ ..... ገጽ 10 — 12 ፣ አለቃ ዘነብ ..... ገጽ 18 — 19
2 Theodore II - Le Nouvel Empire D'Abyssinie pp. 51-52.



በውስጡ ያለው ነዋሪው ፣ መኳንንትና መሳፍንት ባፄ ቴዎድሮስ ላይ ያለውን ጥላቻ ወይም ንቀት በመገንዘብ ይሁን በግልጽ አይታወቅም ።

የሆነ ሆኖ ፣ ከድሉ በኋላ ከዳተኛውና ብልጡ ብላታ ኮከቤ «ለርስዎ ስል ጌታዬን ደጃች ውቤን ከድቼ ብዙ ሥራ ስለ ሠራሁ ሹመትና ሽልማት ይገባኛል» ሲሉ ለዐፄ ቴዎድሮስ አመለከቱ ። ዐፄ ቴዎድሮስ በጠባያቸው ከከዳተኛ ይልቅ ደፋርና ሐቀኛ ስለሚወዱና ለጌታው ያልታመነ ለኔም አይታመንም በማለት ፣ «እኔ ጌታውን ከሚከዳ አሽከር ጋር አንድነት የለኝም» ብለው በመሾምና በመሸለም ፈንታ አሰሩዋቸው ። በትግሬም ግዛት አላይ እንዳልነው የደጃች ውቤ ጭፍሮች የነበሩት ቀርተው በደጃች ውቤ ላይ እየሸፈቱ ሲታሰሩ ፣ ሲፈቱ የነበሩት ባልጋዳ አርአያ ድምፁ በዚህ ጊዜ ከዐፄ ቴዎድሮስ ጋር ተባብረው ነበርና የትግሬን ግዛት ሰጧቸው ።

ደጃች ውቤን ግን ፣ ከነቤተሰባቸው ወደ እስራት ሰደዱዋቸው ። ውቤ በግዞት ላይ ሳሉ ጸሐፊው እንደሚለው በዘመናቸው ሌላውን ማሰርም ፣ እጅ መቁረጥም ይወዱ ነበር ይባላል ። አሁን በሌላ ሰው ላይ ያደርጉት የነበረው በቀጥታ በራሳቸው ላይ ደርሶ በተራራው ላይ ያለውን ሀብት ለማስረከብ እምቢ ባሉበት ጊዜ እጃቸው እስኪደማ ድረስ በጭራ ገመድ ታስረው ካስረከቡ በኋላ ደግሞ ፣ በጽኑ እስራት ሲሠቃዩ እንደዚህ ብለው የሐዘን ግጥም ገጠሙ ይባላል ።

«መከራን በሰው ላይ እንደዚያ ሳቀለው
እንዲህ (እንደዚህ) ይከብዳል ለተሸከመው ሰው ።»(1)

ብስጭታቸውም እየባሰ በሔደ መጠን ፣ «ለምን ከነዘመዶቼ አስረው ያጉላሉኛል ? ከኔስ ለመለያየት አንድ የጠበንጃ ጥይት ጣት (ምላጭ የምትስብ) አይበቃምን ?» ብለው ላፄ ቴዎድሮስ ላኩ ። ነገር ግን፣ ንጉሡ ላጭር ጊዜ ልጃቸውን ጥሩ ወርቅን አግብተው ከፈቷቸው በኋላ እንደገና ታስረው ፣ በድምሩ 13 ዓመታት

1 ቶዜላ ..... ገጽ 12

ያህል ቆይተው ወደ መጨረሻው ታማሚ ሆነው በ1860 ዓ. ም. ሞቱ ። ይኸም ዓመት ራሳቸው ቴዎድሮስ ከእንግሊዞች ተዋግ ተው ራሳቸውን የገደሉበት ዓመት ነው ።

ያፄ ቴዎድሮስ አነሣሥ ለመሳፍንቱ ሐሣርና መከራ ሲያወርድ ፣ ለተርታው ሕዝብ ግን ለካህኑም ለባላገሩም ፣ በተለይ ለተበደለው ወገን ተድላና ደስታ እንደሚያመጡ ተገምቷል ። ይኸንንም የሚያስረዳን በነገሡበት ቀን አንድ ደብተራ እንደዚህ ብሎ የተቀኘው የአማርኛው መወድስ ቅኔ ነው ። ቅኔው እንዲሠ ምርለት የተሳካው በቀድሞ ስማቸው በካሣ ነው ።

«ሚ ይበዝህ የበደልኸኝ አንተ
ምውተ ምግባር እኔን እግዚአብሔር ሕያው
ብንታረቅም አሁን በካሣ ነው ።
ሰጥተውኛልና ሥላሴ ፈርደው
እህሉም በቅሎ እንዳይጠፋ
ዝናመ ምሕረት ካሣን
በኢትዮጵያ አዘነምኸው
አሁንም ስጠኝ ካሣዬን በጉልቆ ፍጡራን አኃው
ጉልቆ ዘመኑን ታውቃለህና ጉልቆ ዘመኑን አታጉድለው
ወእንበለ ካሣ ተዐረቅ ኢይበሉኒ አበው
ካሣ ለተበደለ ከጥንት የመጣ ነው ።»(1)


እንደዚሁም በደረስጌ ከእቴጌ ተዋበች ጋር ስለ መጋባታቸው ፣
«ተዋቡን ሲያገባ ሠርጉ መች ደመቀ
ደረስጌ ስናየው መልሱ አንጸባረቀ
ፊትማ ሲያገባት ተክሊል መች ነበረው
ካሣ ደረስጌ ነው በሕግ የተዳረው
ሊቃውንት ፣ ካህናት ካንድ ላይ በሙሉ
ጐንደር አልነገሠም ብለው ያድማሉ
በከንቱ ነው እንጂ ፣ በራስ ፍርድ ለማምጣት
ዘውዱ ከተሠራ ሆኗል ዐሥር ዓመት(*)
ለኢትዮጵያ ሲደክም ካየነው
የነገሠበቱ ደረስጌም ጐንደር ነው ።(2)»

---

1 መጽሐፈ ቅኔ — ብላታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ገጽ 261
* ከሸፈቱበት ጊዜ ያለውን መቁጠሩ ይሆን ወይስ ተዋበችን ካገቡበት?
2 አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ — ገሪማ ታፈረ ገጽ 64




ዐፄ ቴዎድሮስ
(ከጉዮም ለዣን መጽሐፍ)



**የዐፄ ቴዎድሮስ ዘውድ**
**(ከሮጅ አክቶን መጽሐፍ)**

# ዐፄ ቴዎድሮስ የማዕከላዊ መንግሥትን ለማጠናከር የተጓዙባቸውን አውራጃዎች የሚያሳይ ካርታ ።



# ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት

የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ ያደረገችው ተጽዕኖ — ዐፄ ቴዎድሮስና ጳጳሱ አቡነ ሰላማ በኢትዮጵያ ባሉት የካቶሊክ ሚሲዮን መሪዎች ላይ ያደረጉት ተቃውሞ — በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የጸጉች ውድቀት ፤ የካሪዎች ማንሠራራት ።

የኢትዮጵያ አቀዋም ከነጻነቷ ፣ ከክብሯና ከመጠነኛ ሥልጣኔዋ አንጻር ሲታይና ሲመረመር አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ እንደምትገኝ ግልጽ ነው ። በዘር ረገድ ፍጹም አፍሪካዊ ወይም ኩሻዊ ፣ እለዚያም በሙሉ ሴማዊ ሳትሆን ከዚህም ፣ ከዚያም ደብለቅለቅ አድርጋ በአብዛኛው የቀለም ጠይምነት ያለው የዘር ህልውና የያዘች አገር ነች ። አቀማመጧም በአፍሪካ ቀንድ ሆኖ በሙሉ ከአፍሪካ መካከል ወይም ከመካከለኛው ምሥራቅ ሳትገባ ፣ በዚሁ የተነሣ ዘርና ሥልጣኔዋን ከሁለቱም ወገን ደበላልቃ ፣ ለሁለቱ ነገዶች መገናኛና መተላለፊያ ጭምር ሆና ለራሷ የተቀላቀለ ዘር ፈጥራለች ።

በኢትዮጵያ ነገሥታቱ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ሲሆኑ ፣ በአገሪቱ ውስጥ የክርስትናና የእስልምና ተከታዮች ፣ እንዲሁም ታዋቂ ሃይማኖት የሌላቸው ወገኖች የሚገኙባት ነች ። አጐራባቾቿ ደግሞ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮችና የታወቀ ሃይማኖት የሌላቸው ናቸው ። በክርስቲያንነቷ ደግሞ ፣ በፕሮቴስታንት ወይም በአድቬንቲስት ከሚያምኑት ከአንግሎ ሳክሶኖች (እንግሊዝ ፣ ጀርመን) ጋር እንዳይስማሙ ፣ በካቶሊክ ሃይማኖት በሚያምኑት የላቲን ዘሮች (ፈረንሣይ ፣ ፖርቱጋል ፣ እስፔን ፣ ጣሊያን..........) እንዳይደገፉ የነርሱ የክርስትና እምነት ለየት ብሎ ከእስክንድርያ ቤተክርስቲያን የሠረፀው ፣ «የክርስቶስ አምላክነቱና ሰውነቱ በፍጹም ተዋሕደው አንድ ሆነዋል» የሚለው ፈረንጆቹ (Monophisism) ብለው የሠየሙት ተዋሕዶ ሃይማኖት ነው ።

በዚህ ምክንያት ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ሁለት የተለያየ ሰውነታዊና መለኮታዊ ባሕርይ አለው ከሚሉት ከካቶሊክ አገሮች በጠብ ትለያይና በጸድቃን ፣ በሰማዕታት አማላጅነት በመኖር ከነርሱ ጋር ትስማማለች ። ከነርሱ ጋር በዚህ በመጨረሻው መሠመር ብቻ ስትስማማ ፣ ‘ጻድቃንና ሰማዕታት ያማልዳሉ’ በማለቷ መንግሥተ ሰማያት የሚገባው በበጎ ሥራ ወይም በክርስቶስ ደም ብቻ ነው ከሚሉት ከፕሮቴስታንት አገሮች ጋር ትፃረራለች ። ስለዚህም ለነዚህ «ፀረ ማርያም» የሚል የቅጽል ስም ሰጥታቸዋለች ። በክርስቶስ ባሕርይና በአማላጅነቱ ጉዳይ በጣም ከምትቀርባቸው ከግሪክ አብያተ ክርስቲያን ጋር እንኳን ሙሉ ኅብረት እንዳይገኝ ፣ እነርሱ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ይሠርፃል ሲሉ እርሷ በአብና በወልድ መካከል የስም ልዩነት እንጂ ፣ የተግባር ልዩነት ስለሌለ መንፈስ ቅዱስ ከአብም ከወልድም ይሠርፃል ትላለች ። ሁሉም አስታራቂውን አሳብ እየሸሹ የየራሳቸውን አባባል የሚደግፍና ሊያፋጃቸው የሚችል ጥቅስ ከመጽሐፍ ቅዱስ አያጡም ። የዚህም ጉዳይ ከልማትም ፣ ከኢኮኖሚና ከኢንዱስትሪ የበለጠ አሳሳቢና አከራካሪ ሆኖ የቆየበት ዘመን እጅግ ረዥም ነበር ።

በሥልጣኔም ረገድ ፣ ነገሥታቱ አንድ ጊዜ የያዝነው አሮጌውና መጽሐፍ ቅዱሳዊው ሥልጣኔ ለዘለቄታ ይበቃናል በሚል የግትርነት እምነት ስለጸኑ ፣ ረዥሙን የነጻነት ዘመን ያለዘመናዊ ሥልጣኔ እንድታሳልፍ አገሪቱ ተገድዳለች ። በሃይማኖት ሰበብ ከራቀቻቸው ከአውሮፓ አገሮች ሥልጣኔን በመቅሰም ለልማትና ለዕድገት በፍጹም ሳትጠቀምበት ስለ ኖረች ፣ አሁን በቅኝ አገዛዝ ቀንበር ሥር ከነበሩት ከአፍሪካዎቹ አገሮች የኢኮኖሚና የኢንዱስትሪ ፣ በጠቅላላው የትምህርትና የሥልጣኔ አቅም ጋር ሲመዛዘን ተመሳስሎ ከምሥራቆቹ አንሶ ይገኛል ። ስለዚህ ረዥሙ የነጻነት ዘመን ፣ ለትምክህትና ለኩራት ካልሆነ በቀር ፣ የሚጨበጥ የሥልጣኔ ጥቅም እንዳልሰጠና ሁኔታው ኢትዮጵያን ኋላቀር አገር እንዳደረጋት አይካድም ። ነገር ግን «ኩራት ራት ነው» ይባላልና በቅኝ ገዥዎች ተይዞ በዝቅተኛ ደረጃ ሥልጣኔ ከማግኘት ፣ የራስን ነዋሪ ባህል እንደ ያዙ በነጻነት መኖሩ የበለጠ የሚያኮራ ነው ያሰኛል ።

አሁን ግን ፣ በዚህ ምዕራፍ ለማመልከት የተነሣነው ፣ ከኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት የሚፃረረው የሮማ የካቶሊክ ቤተ



ክርስቲያን ፣ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ከሚያደርገው ተጽእኖ የተነሣ ፣ ባዔ ቴዎድሮስ ጊዜ የተቀሰቀሰውን የሃይማኖት ውዝግብ ነው ።

በአምስተኛው መቶ ምዕት በኬልቄዶኑ ጉባኤ ከክርስቶስ በሁለትና ባንድ ባሕርይ ልዩነት የተነሣ ፣ የሮማ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንና የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በጠብ ከተለያዩ ወዲህ የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ፣ የኢትዮጵያን ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ ገንጥላ ወደ ራሷ ለማድረግ በየዘመኑ ያልተቆጠበ ጥረት አድርጋለች ።

በ16ኛው መቶ ዓመት ላይ በቱርኮችና በዐረቦች የተደገፈው አህመድ ኢብን ኢብራሂም እልቂት በፈጸመበት ዘመን[1] ንጉሡ ልብነ ድንግል የፖርቱጋል ንጉሥን የጠየቁት ወታደራዊ እርዳታ በልጃቸው ባዔ ገላውዴዎስ ዘመን ደርሶ የግራኝ አህመድ ወረራ በፖርቱጋሎች ትብብር ከተደመሰሰ በኋላ ፣ የሮማ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች የፖርቱጋል መንግሥትን ተገን ይዘው ይህ መንግሥት ላደረገው ውለታ ዋጋ በመፈለግ ፣ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ወደ ካቶሊክነት እንድትለወጥ እርዳታውን ባመጣው በዣን ቤርሙዴዝ አማካይነት አጥብቀው ያዙ ። ወጣቱ ገላውዴዎስም ምንም እንኳን የፖርቱጋል መንግሥት ያደረገውን ወታደራዊ እርዳታ ከፍተኛ ግምት ቢሰጡት ፣ በዚህ እርዳታ ምክንያት የሃይማኖት ለውጥ ቢያደርጉ ፣ በግራኝ ዘመን የነበረው ሁከት እንደሚመለስ በማመን ፣ የቤርሙዴዝን አሳብ ሳይቀበሉ ቀሩ ። በዚሁ ጠብና ክርክር ተፈጥሮ እርሱም በንዴት ወደ አገሩ በ1559 ዓ. ም. ከተመለሰ በኋላ በ1575 ዓ. ም. ሞተ ። [2]

ቀጥሎም የሮማ ርእሰ ሊቃነ ጳጳስ ዩልዮስ 3ኛ እና የፖርቱጋል ንጉሥ ዮሐንስ ሦስተኛ ተመካክረው የቤርሙዴዝን አሳብ ወደ ፍጻሜ ለማድረስ ከርሱ በትምህርት የጠለቀ ፣ በክርክሩ ዘዴኛነት የታወቀው ሮድሪጎ ጐንዛሊስ ፣ ከርሱም ቀጥለው ከኢየሱሳውያን ማኅበር (Jesuites) እነአንድሪያ ኦቪዮዶ ተመርጠው መጡ ። እነዚህም በ1557 ዓ. ም. መጥተው

1 1519 — 1533 ዓ. ም.
2 HISTOIRE DU CHRISTIANISM - LA CROZE P. 153 - 154

መልካም መስተንግዶ ከተቀበሉ በኋላ፣ ኢትዮጵያ ወደ ካቶሊክነት እንድትለወጥ ላቀረቡት ልዩ ልዩ ጥያቄና ክርክር ንጉሡም ፣ ሊቃውንቱም የሚገባ መልስ እየሰጡ ሳይቀበሉዋቸው ቀሩ ። ዐፄ ገላውዴዎስ ባንድ ወገን በምጥዋ በኩል ቱርኮች ስለ ተነሡና በሌላው ወገን እነዚህ ሚስዮናውያን በሚያቀርቡት ክርክር መካከል ተቸግረው እንደ ነበረ ታሪከ ነገሥት በደንብ መዝግቦት ይገኛል ።[1]

ነገር ግን ፣ እነዚሁ የኢየሱሳውያን ማኅበር አባሎች ባንድ ጊዜ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ለሮማ ቤተ ክርስቲያን ተገዥ የማድረጉ ነገር ቢስትም ፣ ባለፈው የፖርቱጋል ንጉሥ ባደረገው ውለታ ምክንያት በኢትዮጵያ ተቀምጠው እንዲያስተምሩ ስለ ተፈቀደላቸው ፣ እነርሱም በኢትዮጵያ ተቀምጠው እያደር በዘዴም ፣ በስብከትም ሃይማኖታቸውን ሲያስፋፋቁ ። አሳባቸውም በመጨረሻ ባፄ ሱስንዮስ ጊዜ (1599—1624) ግቡን ለመምታት ቀረበ ።

አልፎንሱ ሜንዴዝ የሚባለው የኢየሱሳውያኑ ሹም ፣ ያፄ ሱስንዮስን ባለሟልነት እያደር በማግኘት ኢትዮጵያም ካቶሊክ ብትሆን የምታገኘውን አውሮፓዊ እርዳታ እያመለከተ ፣ በመጨረሻ ንጉሡ ራሳቸው የካቶሊክን ሃይማኖት መቀበላቸውን አስታውቀው ሕዝቡም የርሳቸውን አርአያ እንዲከተል ዐወጁ ። ቅጣት የፈራው ፣ ሹመትና ባለሟልነት ያማረው ሲቀበል ፣ የቀረው መኳንንትና ካህናት ከነሕዝቡ እምቢ ስላለ ባገር ውስጥ ከፍ ያለ ጦርነትና ሁከት ተነሣ ። የገዛ እንደራሴያቸውና አማቻቸው ራስ ዩልዮስ ፣ የልጃቸው የወይዘሮ መለኮታዊት ባል ፣ ከአቡኑ ከአባ ስምኦን ጋር በጦርነቱ ላይ ሞተ ።[2] ከነዚህም ጋር ብዙ ሕዝብ ለንጉሡ ታዛዥ በሆነው ወታደር እየተመታ አለቀ ።

በመጨረሻም ፣ የሕዝብን እንሣሥ በጦር ኃይል መደምሰስ አስቸጋሪ ስለሆነ እርሳቸውም ከዚህ የሃይማኖት ለውጥ የተነሣ ፣

---

1 ወበውእቱ መዋዕል ሀለወ ውእቱ ንጉሥ ገላውዴዎስ ማዕከለ ክልኤቱ ፈያት ፣ እምለፌ ይትዋበአሙ ለማዕምራነ አፍርንጅ...... ወእም ካልዕትሂ ለፌ ኮነ ሀልወ እንዘ ይመክር በዘይፀብእሙ ለወንድ ዘውእቶሙ ትርኩ (ቱርክ) ያፄ ገላውዴዎስ ዜና መዋዕል ጕንዘልማን ያሳተመው ገጽ 63—65

2 CHRONACA DE SUSENIOS - PEREIRA CHAP. 47, p, 165-166



ሁከቱም ውጣ ውረዱም ስለ አዳከማቸው ፣ ሕዝቡን አሸንፈው የባዕዱን ሃይማኖት በማስገባት ፋንታ ራሳቸው ተሸንፈው «ፋሲል ይንገሥ ፤ ሃይማኖት ይመለስ» የሚል ቃል ወርውረው ብዙም ጊዜ ሳይቆዩ ፣ በ1625 ዓ. ም. በታኅሣሥ ወር ዐርፈው ልጃቸው ፋሲል ስመ መንግሥታቸው ዓለም ሰገድ ተብሎ ነገሡ ።[1] በዚህም ጊዜ ባፄ ፋሲል ዘመነ መንግሥት ደግሞ አጥቂና ተጠቂ ሥፍራ ለሥፍራ ተለዋውጠው በያለበት የተደበቁት የካቶሊክ ሚሲዮናውያን እየተያዙ በስቅላትና አንገት በመቆረጥ ተቀጡ ።

የሮማ ቤተ ክርስቲያን ዋናው ዓላማ ፣ መንግሥታት የአፍሪካን ክፍለ አህጉር ለቅኝነት እንደሚፈልጉ ሁሉ ፣ በዚሁ መሥመር ታላቂቱ ገናናይቱ የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንም ኢትዮጵያን በግዛቷ ለማስገባት ነው ። ለዚህ ዓላማ ደግሞ ዜጎችን ለመሳብ የሚያስችላት የኢኮኖሚም ፣ የትምህርትም ፣ የሥልጣኔም አቅዋም አላት ። የፕሮቴስታንት መልእክተኞች በርቧጐን የርቧን እርምጃ የሚፃረሩ እንግሊዞቹና ጀርመኖቹ በኢትዮጵያ ለስብከት ባይጠፉም ፣ ከሁለቱም እያያዝ የካቶሊኮቹ በርታ ይላል ።

ከእስክንድርያ ፣ እንድርያስ የሚባሉት ወጣት አቡነ ሰላማ በሚል ሥያሜ ተቀብተው ፣ ጳጳስ ሆነው ፣ በደጃች ውቤ ጊዜ (1834) መጡ ። ውቤ ከተሸነፉ ወዲህና ዐፄ ቴዎድሮስን ባነገሡበት ሰዓት የካቶሊክ ሚሲዮን በኢትዮጵያ በሰሜናዊ ክፍል በምጥዋ ፣ በአካለ ጉዛይ ፣ በሌላውም በአማራው አገር በመስፋፋት ላይ በሚገኝበት ሰዓት ፣ አቡነ ሰላማና ዐፄ ቴዎድሮስ የካቶሊክ ሃይማኖት መስፋፋት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን እንዳያዳክመው በመሥጋት ፣ ይኸን ከውጭ አገር በተለይ ከፈረንጆች የመነጨውን ሃይማኖት ለመቃወም ኅብረት አደረጉ ።

በዚህም ላይ ወደፊት በሚገኘው ምዕራፍ በአባ ያዕቆብና በእነአባ እምነቱ ጐትጓችነት ደጃች ንጉሤ ከኢትዮጵያ መሬት ቆርጠው ለፈረንሣይና ለሣርዲኛው መንግሥት ሊሰጡ ፣ እነዚህም ሁለት መንግሥታት ንጉሤን በመደገፍ በቴዎድሮስ እግር

---

1 የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ ተ. ጸ. መ. ገጽ 138—146

ለማንገሥና ንጉሤም የካቶሊክን ሃይማኖት በፋንታቸው እንዲደግፉና እንደ ልብ ለማስፋፋት እንዲረዱ ታቅዶ የነበረው አሳብ እንደ ምን እንደ ከሸፈ እናነባለን ።

አሁንም ፥ ዐፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መሳፍንትን ሽረው በመንግሥ ፥ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት ለማቆም እንዳሰቡ የሃይማኖቱንም ነገር ከአባ ሰላማ ጋር በመተባበር የውጭ አገር ሚሲዮንን በተቃወሙ ቁጥር ፥ ቆንሲሎቹ እነለዣን የዜጐቻችንን መብት እንጠብቃለን በሚል ሰበብ ከንጉሡ ጋር ክረር ያለ ክርክር ይፈጥሩ እንደ ነበረ ግልጽ ነው ። በዚህም ጊዜ ዐፄ ቴዎድሮስ ፥ «አወን ዘዴያችሁን ዐውቀዋለሁ ። በመጀመሪያ ሚሲዮኖች ይመጣሉ ፥ ቀጥለው እነሱን የሚጠብቁ ቆንሲሎች ፥ በመጨረሻም ወታደር ይመጣል» አሉ ይባላል ።([1]) አባባላቸው ትክክል ነው ።

ስለዚህ ለሌሎቹ ወረዳዎች ፥ በከፋና በጉድሩ ያሉትን እነአባ ማሲያስን እነሊዎን ዲዣንቫንሸርን መቃወም ቢያቅታቸውም በቅርቡ በትግራይ ፥ በትግረና በበጌምድር ይኸንኑ ካቶሊካዊ ሃይማኖት በማስፋፋት ላይ የሚገኘውን ፥ አበሾች አባ ያዕቆብ ፥ ፈረንጆች ደግሞ ሞንሴኜር ደ. ቹኮቢስ የሚሉትን «ክርስቲያን ነኝ ካልክ የኢትዮጵያን ሃይማኖት ይዘህ ተቀመጥ ። አለዚያ አገሬን ለቀህ ውጣ» አሉት ። እርሱ ግን ፥ በዚህ ምክንያት መታሰሩንም ፥ መጉላላቱንም እንደ ጽድቅ ስለ ቈጠረውና ከታዘዘ ወዲህ እርሱም ፥ ጭፍሮቹም ባገር ላይ ስለ ተገኙ ታሰሩ ። በኋላ እርሱ የውጭ አገር ሰው በመሆኑ በግዴታ ካገር እንዲወጣ ሲገደድ ፥ ያገር ተወላጆቹ እነአባ ገብረሚካኤል እስራት ተፈርዶባቸው በእስራት ላይ እንዳሉ ሞቱ ። ([2])

በዚህ ዐይነት ፥ ባለፈው በነደጃች ንጉሤ ሰበብ ወደ ፖለቲካ እየገቡ ያወኩዋቸውን የፈረንሣይና የኢጣልያ ካቶሊኮች አበክረው ሲቃወሙ ፥ የፕሮቴስታንት ሚሲዮንን የሚመሩት እንግሊዞችና ጀርመኖች ግን ፥ የርሳቸው ረዳትና አማካሪ በመሆን ባገር ጉዳይ ገብቶ ላለመገኘት ለጊዜው ጥንቃቄ ስላደረጉ ፥

1 HISTOIRE POL. J.B. COULBEAUX P. 444
2 Vers La Lumiére...... J.B. Coulbeaux Chapitre........ XVI-XVII pp. 184-196 209-222.



ከነዚህም ጋር በፊተኛው ጊዜ የእንግሊዙ ቆንሲል ፕሎውዴን ፥ የእንግሊዙ ዜጋ ቤል (ዮሐንስ) የርሳቸው አገልጋዮች ሆነው ስለ ተገኙ ፥ የካቶሊኮችን ያህል ፕሮቴስታንቶቹን አልተቃወሟቸውም ።

እንደዚሁም ዐፄ ቴዎድሮስና አባ ሰላማ ፥ በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያለውን የቅባቶችና የጸጋዎችን ልዩነት ወደ አንድ የካራዎች መሥመር ለማግባት የኃይል እርምጃ ወሰደዋል ። የክርስትናን ጉራ በኢትዮጵያ ሳይቀር የከፋፈለው ያው የክርስቶስ የአምላክነቱና የሰውነቱ ባሕርይ ነው ። ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንደ እናት የምትቈጠረው የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን እምነት ‘አምላክ (ወልድ) በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ፥ ከነፍሷ ነፍስ ወስዶ ፥ ፍጹም አምላክ ፥ ፍጹም ሰው ሆኖ ፥ አምላክነቱና ሰውነቱ በፍጹም ተዋሕዶ አንድ ሆኗል ፤ በሁለት ባሕርይ ከከፈልነው አምላክነት ያልተዋሐደው ሥጋና ደም ለዓለም ቤዛ አይሆንም’ የሚል ሲሆን ፥ ይኸም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን እምና የተቀበለችው ነው ።

ይኸንንም እምነት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ ወርሳ ከመቀበል ጋር ክርስቶስ ከዓለም ፍጥረት በፊት ከእግዚአብሔር አብ ፥ ከዓለም ፍጥረት በኋላ ከማርያም በመወለዱ ፥ «ወልደ አብ ወልደ ማርያም ፥ ሁለት ልደት» ብላ ክርስቶስ በተዋሕዶ የአብ የባሕርይ ልጅ መሆኑን ታምናለች ።

በዚህ መካከል ፥ ያንድ ክፍል የቤተ ክህነት አባሎች የክርስቶስን አምላክነቱንና ከማርያም መወለዱን ሳይክዱ ፥ በሰውነታዊ ሥጋው የአምላክ ልጅ የሆነው በባሕርይ ሳይሆን በጸጋና በጥምቀት ነው ፤ እኛ በጥምቀት ክርስትናን ተቀብለን የእግዚአብሔር ቤተሰብ እንደሆንን ፥ ክርስቶስም ከተወለደ ወዲህ ሠላሳ ዓመት ሙሉ ማን መሆኑ ሳይታወቅ ሲያስተምር ኖሮ ፥ በመጨረሻ ሲጠመቅ ነው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ የታወቀው ።([1]) የእግዚአብሔር አብ ልጅነቱም በጸጋ ይኸውም ማለት የፈቃድ ስጦታ እንጂ ፥ እግዚአብሔር በአምላክነት ባሕርዩ ሥጋ ለባሲን አይወልድም ። ስለዚህም ክርስቶስ ከአብና ከማርያም ሁለት ጊዜ ከተወለደ ወዲህ ፥ አሁን በጥምቀቱ የጸጋ ልጅነቱን ስላወቅነው

1 የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 3/13 —17 ፥ የማር. ወንጌል ምዕ. 1/9- 11

ጥምቀቱ እንደ ሦስተኛ ልደቱ ይቈጠራል ስላሉ የዚህ ክፍል አማኞች የጸጋ ልጆች ፣ አንዳንድ ጊዜም ሦስት ልደቶች ይባላሉ ። እነዚህም በርከተው ፣ ተስፋፍተው የተገኙት በሸዋ በተለይ በሣህለ ሥላሴ ከተማ በአንኮበር ነው ። ዐልፎ ፣ ዐልፎ በሌላውም ክፍለ ሀገር ይገኛሉ ።

እንደዚሁም የክርስቶስ ሰውነት ፣ የአምላክነት ባሕርይ የተቀበለው በመቀባት ነው ። ለዚህም ምስክሩ ክርስቶስ ትምህርቱን በጀመረበት ወቅት የኢሳይያስን መጽሐፍ ከፍቶ ፣ «የጌታ መንፈስ በኔ ላይ ነው ። ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛል» ብሎ የአምላክነት ሥራውን የገለጠው ፣ ከዚህ ቅብዓት በኋላ ነው በማለት ይኸን አባባል በጽሑፍ እያስፋፉ ሦስተኛ የእምነት ጐራ ፈጥረዋል ። እነሱም ቅባቶች ይባላሉ ። እነዚህም አብዛኛዎቹ ጐጃም በደብረ ወርቅ ደብር ነው የሚገኙት ።[1]

የዚህም የሦስት ክፍል እምነት ተከታዮች በጐንደር ዘመነ መንግሥት በየጊዜው ካህናቱ ጉባኤ ይዘርጋልን ፣ አከራክሩን እያሉ ነገሥታቱን እየጠየቁ ብዙ ጊዜ ጉዳዩ ሲያፋጅና ሲያዋጋ ኖሯል ።[2] አሁንም አባ ሰላማ ከመጡ ወዲህ ይኸው የአሳብ ልዩነት እያመረቀዘ ፣ የጸጋና የቅባቶቹ ወገኖች አቡኑን እየተቃወሙ ቆይተው ነበር ። ብዙዎችም ያንኮበር ታላላቅ ሊቃውንት እነ አለቃ ኪዳነ ወልድ ፣ እነ አለቃ ገብረ ክርስቶስ በአንኮበር የጸጋዎቹን የነአለቃ ሥነ ጊዮርጊስን ፣ የነአለቃ ተክለ ጽዮንን መስፋፋት ፣ የነገሥታቱን ወደ ጸጋዎች ማዘንበል እያዩ ፣ እየተበሳጩ አገራቸውን ሸዋን እየለቀቁ ወደ ቤጌምድር ፣ ወደ ጐጃም ፣ ወደ ትግራይ እየተሰደዱ ይኖሩ ነበርና አሁን ዐፄ ቴዎድሮስና አቡነ ሰላማ በኅብረት ጸጋዎችን ለመደምሰስ ካራዎች የሚባሉትን ፣ ክርስቶስ በሰውነቱ ጭምር የባሕርይ አምላክ ነው የሚሉትን ለማጠንከር ወደሸዋ የመጡ ጊዜ ፣ ቴዎድሮስ በበኩላቸው በሥጋዊ ረገድ የተዋጋቸውን ሲቀጡ ፣ አቡኑም በእነ አለቃ ኪዳነ ወልድ እየተመሩ ጸጋዎችን እየጠቆሙ አስደብድበዋል ። ንጉሡና አባ ሰላማ በመጨረሻ እስኪጣሉ ድረስ በሸዋ ግዛታቸው ተዋሕዶ ሃይማኖትን በሚገባ እንደ አጸኑ ወደፊት በዝርዝር እናነባለን ።

1 የሉቃስ ወንጌል ምዕ. 4/16 — 20 ፣ ግብረ ሐዋርያት 4/27.10/38
2 Annales Iohannis I Iyasu et Bakaffa pp. 86-87, 91-96.



# ምዕራፍ ዐሥራ አራት

## ከንግሥ በኋላ ፤ የወሎ ዘመቻ

ዐፄ ቴዎድሮስ ከነገሡ በኋላ እዚያው ደረስጌ (ደብር ስጌ) እንዳሉ ፣ የዘመኑ ስማቸው ያልታወቀው ጸሐፊ ከዚህ የሚከተለውን ዐዋጅ ማናገራቸውን ያመለክታሉ ። «አራሽ እረስ ፤ የወንድ መኰንን ፣ የሴት ወይዘሮ ፣ ባለ ጉልት ባለርስት እየአባትህ ፤ (የአባትህን) ሰጥቼአለሁ ፤ ነጋዴም ነግድ ፤ በተቀማህበት ደንጊያ ደርድረህ ወደኔ ና (ላቤቱታ) ። ተወኝ ሌባ ፤ ተወኝ ወንበዴ ። ግባ ፤ እቀማለሁ ፣ እሠርቃለሁ ብትል ለአካልህ እዘንለት ። አይዞህ ደሃ ፤ አይዞህ ወታደር ፤ ደስ ይበልህ ፤ መጥቼልሃለሁ (ነግሼልሃለሁ) ። የኢያሱ ይብቃ»[1]

ከሥርዓተ ንግሡ በኋላ ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ አገር አቀናለሁ ብለው ወደሸዋ ሲዘምቱ[2] አቡነ ሰላማም ሃይማኖት አቀናለሁ በሚል አብረው ሔዱ ። አቡነ ሰላማ ወደሸዋ ሔደን ሃይማኖት እናቅና የሚሉት ፣ አንባቢ እንደሚያስታውሰው ፣ ከራስ ዐሊ ጋር ጐንደር በነበሩበትና ተዋሕዶ ሃይማኖትን ለማጽናት በሚያስተምሩበት ሰዓት ፣ ከጐንደርና ከሸዋ ሊቃውንት የጸጋው ክፍል ተቃውሟቸው ዛሬ እሑድ ስለሆነ ፣ ትተናቸው ነገ ሰኞ ይወጣሉ ቢባል እንደ ጋኔን ተቆጥረው ክርስቶስ በሰንበት አጋንንትን አውጥቷል ብለው ያንኑለት ከተሸሸጉበት ከገብርኤል ገዳምና ከበዓታቸው የተባረሩትን አስበው ፣ በአባረሩዋቸው የሸዋ ሊቃውንት ላይ ለመበቀል ያሰቡ ይመስላል ። ደግሞ በሸዋ ለተዋሕዶ ሃይማኖት ከፍተኛ

1 ቶዚላ...... ገጽ 12 ። የኢያሱ ይብቃ ማለት ፣ ዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ከ1674 እስከ 1699 ዓ. ም. በጐንደር የነገሡ የኢትዮጵያ ታላቅ ንጉሠ ነገሥት ናቸው ። በዘመናቸው ስለ መሬት ሥሪት ፣ ስለ ንግድ መስፋፋት ፣ ስለ ቀረጥ ልዩ ልዩ ድንጋጌ አውጥተው ስለ ነበረ ፣ እርሳቸው በዐዋጅ የደነገጉት ይርጋ ማለት ነው ።
2 ገጽ 10 — 11

ቅናት ያላቸው አለቃ ኪዳነ ወልድ በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዘመን በጸጋዎች እጥቂነት ካገራቸው ከሸዋ ካለቃ ገብረ ክርስቶስ ጋር ተሰደው በዚህ ጊዜ ቤገምድርና ትግራይ ይኖሩ ነበር ። አሁን ዐፄ ቴዎድሮስና አቡነ ሰላማ በኀብረት ሲጋደሉ የኖሩበትን ተዋሕዶ ሃይማኖት ስላጸኑላቸው ፥ የልባቸው ደርሶ እነርሱን እየ መሩ ወደሸዋ ለመውሰድና እርሳቸውም በበኩላቸው ጠላቶቻቸ ውን የጸጋ ልጆችን በንጉሡ ሰይፍ ፥ በጳጳሱ ውግዘት አማካይነት በማስቀጣት ለመበቀል ሳይቸኩሉ አልቀረም ።

ስለዚህ ንጉሡና ጳጳሱ ግራና ቀኝ ሆነው ፥ ሦስተኛ ዕጨ ጌውን ዕጨጌ ወልደ ማርያምን ጨምረው ፥ ሥርዓተ መንግሥ ትና ሥርዓተ ክህነት አጣምረው በማስማማት ሦስቱም በኀብረት በመንዝ ከደብረ ታቦር በጨጨሆ በኩል አድርገው ወደ የጁ ፥ ከዚያም ወደ ወልድያ ሔዱ ። የዕጨጌ ወልደማርያም አገር ዋል ድባ ስለ ነበረ ፥ የአካባቢውን ሕዝብ ለማስተባበር ሳያግዝ አል ቀረም ። በዚህም በሚዘዋወሩባቸው አውራጃዎች እሺ ብሎ አምኖ ለገባው ንጉሡ ሹመትና ግዛት እየሰጡ ፥ እምቢ ያለውን በመቅጣት ወይም በማሳደድ ላይ ሳሉ ፥ በዚሁ ጊዜ ባልጋዳ አር አያ ከትግራይ ግብር ይዘው መጥተው ተገናኙ ። ዳሩ ግን ፥ ከቀ ድሞ ዠምሮ የራስ ወልደ ሥላሴ ወገንና የደጃች ሰባ ጋዲስ ልጅ ደጃች ካሣ በከዳት ባልጋዳ አርአያን ከሰው ስለ ነበረ ፥ ምንም ነገሩ ከጉዞ ላይ ሆኖ ባይጣራ ፥ ንጉሡ ባልጋዳ አርአያን አስረው የትግራይን ግዛት ለከሳሹ ለደጃች ካሣ ሰባጋ ዲስ ሰጥተው ከዋልድባ ጉዞአቸውን ወደ ወሎ አመሩ ።

በጉዞ ሳሉ ፥ ከጨጨሆ እስከ ሸዋ ድንበር የሚገዙት ወይ ዘሮ ወርቂት የሚባሉ የሴት ባላባት አሉ ፤ እርሳቸውም የይማም ዐመዴ ዐሊ እናት ናቸው ። እኚህም ሴት ወደፊት ፥ እንግሊዞች በሚመጡበት ዘመን ፥ ብዙ ጊዜ በየምክንያቱ ከወይዘሮ መስተ ዋት ጋር ስማቸው ተነሥቶ ይገኛል ። ምሥራቅ ወሎ የወርቂት ሲሆን ፥ ምዕራቡን ወሎና የመቅደላን አካባቢ የሚገዙት ወይዘሮ መስተዋት የሚባሉ የአባ ዋጠው (ራስ ኃይለ ማርያም) እናት ናቸው ። ሁለቱም ከላይ የይማም (የደጃዝማች) ሊበን ልጆች ቢሆኑም የግዛት ባላንጣነታቸው የከረረ ነው ። እነዚህም የሴት ባላባቶች ትውልዳቸው የመሳፍንቱ የነራስ ዐሊ ፥ የእነእቴጌ መነን የሆነው የወሎና የየጁ ፥ የወረሼህ ቤት ነው ።



ቴዎድሮስ በወልድያ ፥ በደላንታ በነበሩበት ሰዓት ወርቂት በገረገራ ያሉትን ክርስቲያኖችን ፈጀች ፤ ቤተ ክርስቲያኑንም አቃጠለች የሚሉ ወሬ ሰሙ ። እነዚህም ባላባቶች እንዲገቡ አስ ቀድመው ተጠይቀው እምቢታቸውን አስታውቀዋል ። ስለዚህ ዐፄ ቴዎድሮስ በግሥጋሤ የወርቂትን አገር ለመምታት በሚጓ ዙበት ጊዜ ፥ «እህል ዘርፈህ ብላ ፤ ልብስና ቁም (ከብት) አት ንካ» ብለው ለጦር ሠራዊታቸው አስጠነቀቁ ። ከወታደሩ ግን ፥ አንዳንዱ ከትእዛዝ ውጭ ከቆመው የባላገር ከብት እየዘረፈ አርዶ መብላቱን ባወቁ ጊዜ ፥ «ወታደር ፥ የደሃ ውን ገንዘብ እንዳረድ ኸው ባንተም እግዚአብሔር አለ» ብለው ተቆጡ ።

እዚህ ላይ ፥ ዐፄ ቴዎድሮስ ከቀድሞ ዠምሮ ይመኙት እንደ ነበረው የመሳፍንት አገዛዝ ወድቆ ፥ የዘውዱ ሥልጣን በእጃ ቸው ገብቶ ጳጳሱ ፥ ዕጨጌው ፥ የአማራውና የትግሬው መሳፍንት በጐናቸው በቆሙበት በአሁኑ ሰዓት በተለይ ‘መጣሁልህ’ ብለው ባወጁለት በገዛ ወታደራቸው ላይ እምብዛም እጃቸው ለቅጣት ያልቸኰለ ይመስላል ። ዳሩ ግን ፥ በደላንታ ተጉዘው በሽሎ ወንዝ በደረሱ ጊዜ አሁንም ወታደሩ ያለ ትእዛዝ ወደ ባላገር ገብቶ መግደልና መዝረፍ ሲዠምር ፥ ነዋሪው የኦሮሞ ሕዝብ እየተከላከለ ብዙ ወታደር ገድሎ የተረፈው እየሸሸ መምጣቱን ሲያዩ ፥ «ድሮ ውንስ ማን ውረዱ አላችሁ? ከወረራችሁስ እንዴት ሸሻችሁ?» በማለት ይመስላል እነዚሁኑ እየሸሹ የተመለሱትን አሲዘው አንድ እጃቸውንና አንድ እግራቸውን በማስቆረጥ ቀጡዋቸው ።(1)

ንጉሡ ዐፄ ቴዎድሮስ በሐምሌ ወር 1847 ዓ. ም. በወሎ ፥ በተለይ ወረሂመኑ በደረሱ ጊዜ ፥ በዚያ ስለ ተደረገው ጦርነት ከመተረካቸው በፊት አለቃ ዘነብ ፥ «......ወረሂመኑ ፥ አሞራ ገደል ከሚባለው አገር ፥ አንድ ቃልቻ ነበረ ። ስሙም ሼህ ያሲን ይባላል ። ይኸንን ንጉሥ አላስመጣውም ብሎ ወዳጃ ያዘ ።(*) ሦስት ቀን በሆነ ጊዜ ፥ «መልአክ ከምድር እስከ ሰማይ የሚደርስ ጦር ይዞ ፥ ‘ለሁሉ መቅሜ ያወረደውን (ቴዎድሮስን) ግደልልኝ አልህ?...... አሁን ከምድር ጋር በሰፋሁህ!’ ብሎ አስፈራራኝ»

---

1 አለቃ ዘነብ ገጽ 19 አለቃ ወልደማርያም ገጽ 8 — 9
* ወዳጃ ያዘ ማለት ጫት እየታኘከ ፥ ቡና እየተፈላ ስለ አንድ ጉዳይ ከንዋኔ በጸሎት ፥ በስግደት እምላክን ሲለምኑ ማደር ነው ።

በማለት ......በነጋውም (ሲነጋ) መቅደላ ወጥቶ ወይዘሮ ወርቂትን «አንቺም ሽሺ ! አልሆነልኝም ። እኔም ዛሬ ሌሊት ልሞት ነበር ። ይህ ሰው ከአላህ የተላከ ነው ......» ብሎ ለወርቂት መንገሩን ያመለክታሉ ።

አለቃ ዘነብ ፣ ይኸን አነጋገር ራሳቸው ከያሲን ወይም ከወርቂት የሰሙት አይመስልም ። ወሬም ተዛምቶ ከሌላ ሰው የሰሙት ሊሆን ይችላል ። ምናልባትም የወይዘሮ ወርቂት ሽሽት ፣ በኋላም በሽፍትነት ቆይታ ፣ በመጨረሻ ተስፋ ቆርጣ በመግባት ልጇን ዐመዴ ዐሊን አቅርባ ንጉሡ ክርስትና እንዲያነሡት ያደረገችው ከዚህ በኋላ ይሆናል ። የሆነ ሆኖ ፣ እንደዚህ ያለው አባባል ቢታመንም ፣ ባይታመንም ከታሪኩ ላይ እንደሚነበበው ፣ ቴዎድሮስ ወረሂመኑ እንደ ገቡ ወርቂት ወደ አያቷ ሽሽታ ከራስ ዐሊ ጋር ተደባልቃለች ማለት ነው ። በመቅደላ አምባ ቀርቶ የነበረው ዣን ጥራር (ዥንፕራር) (*) ዳጋላስ የሚባለው ጥቂት ተዋግቶ እሱም ሸሸ ። ቴዎድሮስም ለመቅደላ አምባ አደም ወዳጅን ሾመው ወደ አያታ ዐለፉ ።

ንጉሡ ከነሠራዊታቸው አያታ ሲደርሱ ፣ ራስ ዐሊና ወይዘሮ ወርቂት በሩቁ በመነጽር ሲያዩዋቸው በሁለቱም ልብ ድንጋጤ እንደሚያድር የታወቀ ነው ። ቴዎድሮስም የነራስ ዐሊን ሰፈር በሩቁ አይተው ተራዛሚ ጠበንጃ ሲያስተኩሱ ፣ ጥይቷ ያንዱን ሰው ለምድ ቀራርጣ አንድ ፈረስ በመታች ጊዜ ሁለቱም ተደናግጠው ወደ በረሃ ሸሹ ። ዐፄ ቴዎድሮስም የነዚህን ወደ በረሃ መሸሽ ካረጋገጡ በኋላ ወደ ለገጐራ መጡ ።

መቼም ኦሮሞም ቢሆን አማራ ፣ ትግራይም ቢሆን ትግሬ የኢትዮጵያ መስፍን ወይም መኰንን በውስጡ ጠበንጃና ጦር የያዘ ተከታይ ወታደር እስካለው ድረስ ፣ ጊዜ ላነሣው መስፍን ወይም ሌሎቹን መሳፍንት አሸንፎ ለነገሠው ንጉሥ በፋንታው ሳይዋጋና ሳይቆራቆስ አሜን ብሎ ገብቶ መገዛትና በሰላም መኖር አይወድም ። በቆየው ልማድ ይኸን ዐይነቱን ሰላማዊ አቅዋም

---

* የዣን ጥራር እስከ መጨረሻ ዘመን ድረስ የአምባሰል ባላባቶች የሚጠሩበት የማዕርግ ስማቸው ነው ።



እናትም ሚስትም አይወዱም ። ጭፍራም ይንቃል ። ዐፄ ቴዎድሮስ ዋናውን መስፍን ራስ ዐሊን ካሸነፉ በኋላ ፣ ለደጃች ውቤ «ከእንግዲህ ወዲያ የሚያደርጉት ጦርነት ለርስዎ አይረባምና ይግቡ» ብለው ቢልኩባቸው ፣ «አያ ምንኛ የጠገበ ነው ! ሳልዋጋ ይገባልኛል ብሎ ነው» ሲሉ የተደነቁትን እንብበናል ።

ልጃቸው ጓንጉል ደግሞ ፣ አባቱ ውቤ ቆስለው ከተማረኩ በኋላ ጭፍሮቹ ፣ «እንዲህ ከሆነ እንመለስ እንጂ» ብለው ቢመክሩት ፣ «ይኸን ሁሉ የተሸከምሁትን አረር (ጥይት) ሳላረግፈው አልመለስም» ብሎ ጦርነት እንደ ገጠመና በኋላም እንደ ሸሸ አለቃ ወልደ ማርያም ይጠቁማሉ ።[1]

አሁንም ዐፄ ቴዎድሮስ በየተራ ደጃች ጐሹን ፣ ራስ ዐሊን ፣ ደጃች ውቤን ፣ ታላላቆቹን መሳፍንት ደምስሰው ሲመጡበት የትንሽ ወረዳ የለገጐራ ባላባት ፣ ዐሊ ደራ ፣ በነሐሴ ወር መዠመሪያ ላይ አልችላቸውም ልግባ የሚል ስሜት አድሮበት አልገባላቸውም ። ጭፍራውን ይዞ በመዋጋት በኃይል ተቋቁሞ ብዙ ሰው ፈጀባቸው ። እንዲያውም የብዙውን ሰው ማለቅ ሲያዩ ራሳቸው ንጉሡ ከፈረስ ላይ ወጥተው በመዋጋት ጦርነቱን በቀጥታ እንዲካፈሉ አስገድዷቸዋል ። ከዚህ በኋላ ዐሊ ደራ ውጊያው እንደ ጠናበት ሲያይ ከሸሸ በኋላ ፣ በሽሽትም ከኝህ ንጉሥ ለዘለቄታ እንደማያመልጥ በመረዳት በመጨረሻ ታጥቆ ገባላቸው ።

የሆነ ሆኖ ፣ ከጥንት ከነዐፄ ኢዮአስ አጐቶች ከነደጃች ብርሌ ከነሉቦ ዘመን ዠምሮ የወሎና የየጁ ኦሮሞዎች ባንድ ወገን ፣ የቋራ አማሮች በሌላ ወገን ሆነው የሚያደርጉት ቅራኔ ጠቡ ቂሙ ሥር የሰደደ በመሆኑ ፣ ከማናቸውም አውራጃ የቴዎድሮስን እርምጃ ጠንክሮ የተቋቋመና በጭካኔም የተቀጣ እንደ ወሎ ሕዝብ የለም ።

አሁንም ራስ ዐሊም ፣ ወይዘሮ ወርቂትም ቢሸሹም የለገጐራው ዐሊ ደራም ታጥቆ ገብቶ ቢሾምም ፣ በጐኑ ያለው ሲዴቅ ደንቃ የሚባለው የቆርቆራው ባላባት ብዙ ጊዜ ተዋጋቸው ። ከርሱም ጋር ከሰባት ቤት ወሎ የተጠራቀመው የወሎ ጦርና ባላገር

---

1 ያለቃ ወልደ ማርያም ዜና መዋዕል ገጽ 6

በያለበት እየከበበ እየወጋ ፣ ስንቅም እየከለከለ ዘራፊውንም ወታደር እየገደለ ቢያበሳጫቸውም ብስጭታቸውን ያዝ አድርገው ፣ «ጋላና አማራን ባንድ ሰዴቃ (መሶብ) የቅዱስ ዮሐንስ ለት ያላበላሁ እንደሆነ እኔ የክርስቶስ ባሪያ አይደለሁም» ብለው በጳጉሜ ፎክረው ጊምባ ላይ የከበባቸውን ጥርቅም ጦር በሙሉ የገዳግንነት መንፈስ በታተኑት ፤ በሸሸውም ላይ የፈረሰኛ ጦር ሰደው እስከ ሸዋ ዳርቻ ድረስ ያለውን የወሎ አገር ከፉኛ መቱት ። በዚህ ጊዜ ንጉሡ በወሎዎች ላይ ቁጭት አድሮባቸው ስለነበረ ፣ ወታደሮቻቸው ሲመለሱ ያመጡላቸውን 47 የኦሮሞ ምርኮኞች ሁለት ሁለት እጃቸውን እየቆረጡ ፣ የተቆረጡትን እጆች በገመድ አንገታቸው ላይ እያሰሩ ለመቀጣጫ በያለበት ሲሰዱዋቸው ጊዜ ፣ ሊዋጋ የተሰለፈውም ሌላውም ይኸን ሲያይ ፣ «ግማሹ አላህ ምን ጉድ አወረድህብን» ብሎ ተገረመ......([1])

ይኸም ዐይነቱ የጭካኔ ቅጣት የወሎን ሕዝብ በሙሉ አላም በረከከውም ። አንዱ አሚን ብሎ ሲገባ ሲሾም ፣ ሌላው ሲሸፍት ሲያዝ ፣ ሲታሰር ፣ ሲፈታ ፣ ሲያመልጥ ፣ ያመለጠውም ሲያዝ ፣ ሲገደል እስከ ዐመዴ በሽር ደረሰ ። ከሁሉ የወሎ ባላባት ዐፄ ቴዎድሮስን እስከ መጨረሻ የተቋቋመ ዐመዴ በሽር ነው ። ዐመዴ አባቱ በሽር የእቴጌ መነን ፣ የዐመዴ አባ ሙጃ ፣ የዐሊ አባ ቡላ (የወርቂት ባል) ወንድም ፣ የይማም ሊበን የልጅ ልጅ ነው ።

———

1 ቶዜሊ ገጽ 12 — 14 ፣ አለቃ ዘነበ ገጽ 19 — 22 አለቃ ወልደማርያም ገጽ 8 — 10



# ምዕራፍ ዐሥራ አምስት

*የሸዋ ዘመቻ ፤ የንጉሥ ኃይለ መለኮት ሞትና የምኒልክ በምርኮ ወደ ጐንደር መምጣት ፤ የወይዘሮ በዛብሽና የወይዘሮ ተደነቂያለሽ ልዩነት*

ከወሎ ዘመቻ በኋላ ቴዎድሮስ ያተኮሩት ሸዋን ከማስገበሩ ላይ ነው ። ሸዋ ከቀሩት የኢትዮጵያ አውራጃዎች ለየት ያለ አቅዋም አለው ። በግራኝ አህመድ ጥቃት ምክንያት የመንግሥቱ መደበኛ መቀመጫ ከሸዋ ወደ ጐንደር ሲዛወር ፣ የጐንደር ነገሥታት በቀጥታ ከሌላውም አውራጃ ከሸዋም ተወላጅ እየሾሙ በቀጥታ ያስተዳድሩት ነበር ። በመጨረሻ ደግሞ ፣ ካፄ ልብነ ድንግል ልጅ ፣ ከአቤቶ ያዕቆብ የሚወለደው አቤቶ ነጋሢ ፣ ለጐንደር ነገሥታት እየገበረ ለሸዋ መስፍን ሆኖ ሲያስተዳድር፣ ካፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ጋር ለመገናኘት ወደ ጐንደር እንደሔደ እዚያው ሞቶ ፊት አቦ ተቀበረ ። ([1])

ከነጋሢ በኋላ ስብስቴ ፣ ከስብስቴ መርድ አዝማች አብዩ ለጐንደር ነገሥታት የተለመደውን ግብር እየገበሩ ሲኖሩ ፣ መርድ አዝማች አብዩ የክርስትና ስሙ ፣ ቀዳሜ ቃል ፣ ባንድ ወገን እኔም የነጋሢዎቹ የነልብነ ድንግል ልጅ ነኝ በማለትና የጐንደር መንግሥት በርስ በርስ ጦርነት ለመድከም የተቃረበ መሆኑን በመረዳት ፣ ግብር ስለ ከለከሉ፣ ባፄ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ ዘመነ መንግሥት በ1730 ዓ. ም. ከጐንደር እርሳቸውን ለማሳመን የመጣውን ጦር አሸንፈው መለሱት ። ([2]) ይሁን እንጂ ፣ የአብዩ ተከታዮች መርድ አዝማች አስፋ ወሰን በነጻነት ከቆዩ በኋላ ፣ ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ የቀድሞውን የነገሥታት ሥልጣን እመልሳለሁ ብለው

———

1 Chronique du Régne de Menelik II - G. Selassé - de Coppet - Vol. II, p. 56.

2 ሳይጠረዝ የቀረው የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የታሪክ መጽሐፍ ገጽ 20 — 21

በሚጣጣሩበት ሰዓት ፥ እምቢ ብሎ ያፈነገጠውን ሸዋን እወጋለሁ በማለታቸው አስፋወሰን ለተክለ ጊዮርጊስ በግንቦት 14 ቀን 1775 ዓ. ም. ሰይፍ ፥ ጉራዴና ጦር ከልዩ ልዩ የሽልማት ልብስ ጋር መላካቸው ተመዝግቧል ። (1) ነገር ግን ፥ በሚቀጥለው ጊዜ የጐንደር ነገሥታት በመሳፍንቱ እነሣሥና የርስ በርስ ጦርነት በተዳከመበት ወቅት ፥ የሸዋዎቹ መሳፍንት እየተጠናከሩ በሸዋ ግራና ቀኝ ያለውን የኦሮሞዎች ይዞታ በመያዝ ተስፋፉ ። በተለይ አባትየው ወሰን ሰገድ ከሞቱ በኋላ ልጃቸው ሣህለ ሥላሴ ካለፉት የበለጠ ገናና ስመ ጥር በመሆን የሸዋን ግዛት በምሥራቅም ፥ በደቡብም አስፋፉት ።

በዚህ ጊዜ ፥ ያባቶቻቸው የማዕረግ ስም የነበረውን መርድ አዝማችን ትተው ንጉሥ ይባሉ ዠመር ። ለውጭ አገር ነገሥታትም በሚጽፉት ደብዳቤ አናት ላይ «..........ራስ ሣህለ ሥላሴ የሸዋ ፥ የይፋት ፥ የአዳል ፥ የጋላ ንጉሥ» እያሉ ይጽፉና በዚሁ ሥያሜ ከእንግሊዝና ከፈረንሣይ መንግሥታት ጋር ይዋዋሉ ነበር ። በጐንደርም ከሚቀመጡት ነገሥታትና መሳፍንት ጋር የበላይና የበታችነቱ ቀርቶ የጓደኝነት ግንኙነት ሆነ ። በዚሁ ደረጃም ከነራስ ዐሊ ጋር መልካም ግንኙነት ነበራቸው ይባላል ።

ሣህለ ሥላሴ 33 ዓመት ከአምስት ወር ሸዋንና በሸዋ ዙሪያ ያለውን አገር ሲያስተዳድሩ ኖረው በ1840 ዓ. ም. በጥቅምት 12 ቀን ደብረ ብርሃን ላይ ዐረፉና አስከሬናቸው ወደ አንኮበር ሔዶ ራሳቸው ባሠሩት በአንኮበር ሚካኤል ተቀበሩ ።

ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ለፖለቲካም ፥ ለአስተዳደርም ፥ ዘር ለማደባለቅም ሲሉ ከደንበኛ ባለቤታቸው ከወይዘሮ በዛብሽ በቀር ከኦሮሞም ፥ ከጉራጌም ፥ ከአዳልም ፥ ከአማራም ፥ በያለበት ዕቁባት እያስቀመጡ ብዙ ልጆች ወልደዋል ። (2) በሞቱ ጊዜ በዙፋን የተከተሏቸው ግን ፥ ከደንበኛ ባለቤታቸው ከወይዘሮ በዛብሽ የሚወለዱት ፥ መጠሪያ ስማቸው በሻህ ውረድ ፥ የክርስትና ስማቸውና ስመ መንግሥታቸው ኃይለ መለኮት የተባለው ነው ።

1 በይእቲ ዕለት ወእመ ዐሠርቱ ወዐርባዕቱ ተረክበ ንጉሥ በፍትሕ እስመ ቦአ ዘተፈነወ እመርድ አዝማች አስፋወሰን እኂዞ ሜላተ ወአልባሰ ወርቅ ለምደ ወዞይናተ ወመጥባሕተ ...... ታሪክ ነገሥት ፓሪስ ቁጥር 142 ገጽ 309

2 የሣህለ ሥላሴ የዘር ሐረግ—በላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወ.መ.



ሣህለ ሥላሴ እንደ ደከሙ ፥ «በእግሬ የረገጥሁትን ፥ በእጄ የጨበጥሁትን ለልጄ ለወዳጄ ሰጥቸዋለሁ» የሚል አጽፈው ስለ ነበረ ፥ ይኸው ቃል ከሞቱ በኋላ በደብረ ብርሃን ከተማ በአደባባይ በዐዋጅ ተነገረና ኃይለ መለኮት ነገሡ ። (1) እንደ ነገሡም በአባታቸው አሟሟት ምክንያት ለንግሥት ቪክቶሪያ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ በዚያው በቀድሞ ስማቸው ጻፉ ። «ዛቲ ጦማር ዘተፈነወት እምኀበ በሻህ ውረድ ንጉሠ ሸዋ ፥ ትብጻሕ ኀበ ንግሥተ ፈረጅ (ፈረንጅ) እንዴት አሉ ። አባቴም ወዳጅዎ ነበሩ ። እኔም ልጃቸው ነኝ። የሞቱ ጊዜ ምነው አንድ አሽከር አላኩብኝ፣ አሁንም ሺህ አምስት መቶ (1500) ብር ፥ ወርቅ እንዳለ ጨምረው ፥ ከራምፍ አሽከር ጨምረው ቶሎ ይላኩልኝ በምጥዋ ። የልብዎን ይንገሩኝ አደን ድረስ አሻግራለሁ ።»(2)

ንጉሥ ኃይለ መለኮት በነገሡ በሰባተኛው ዓመት ዐፄ ቴዎድሮስ በደረስጌ ማርያም ከነገሡ በኋላ ፥ ፊታቸውን ወደ ወሎ ከመመለሳቸው በፊት ያፄ ቴዎድሮስን አያያዝና የዋናውን እንደራሴ የራስ ዐሊን መሸነፍ ሰምተው ነገሩ ከሥጋት ላይ ስለ ጣላቸው ፥ ከአንኮበር ወደ ወሎ ዘልቀው ፥ በጉዳዩ ከጉጃም ጦርነት ሸሽተው በዚህ ጊዜ ወሎ ከሚገኙት ከራስ ዐሊና ከባላባቷ ከወይዘሮ ወርቂት ጋር ቴዎድሮስን በምን አኳኋን ለመቋቋም እንደሚችሉ ለመወያየት ወደ አያታ (ወሎ) መጡ ።

ስለ አመጣጣቸው አለቃ ዘነብ የሚከተለውን አስፍረዋል ። «ያን ጊዜም የሸዋው ገዥ ኃይለ መለኮት ወርቂትንና ራስ ዐሊን ለመርዳት መጡ ። ንጉሥ ቴዎድሮስ የኃይለ መለኮትን መምጣት በሰሙ ጊዜ አያታ ወጥተው አዋ ሜዳ ላይ ሠፈሩ ። ራስ ዐሊም ከኃይለ መለኮት ጋር አንድነት ሆነው መከሩ ፥ እንዲህ ብለው ። «እርስዎም ሸዋ ይመለሱ ፣ ይህነን ሰው አንችለውም» አሉ ። ኃይለ መለኮትም ተመለሱ ። ብዙ ሰው ውሃ ወሰደባቸው ። ከወሎ ዠምሮ እስከ ሸዋ ዳርቻ እየታመመ ያለቀው ፈረስ(*) (ሰፍር) ቁጥር የለውም ። ኃይለ መለኮትም ብርቱ ሕመም ታመሙ ።» (3)

1 የጋላ ታሪክ አቶ አጥሜ በቤተ መጻሕፍት የተቀመጠ ቁጥር 47

2 Public Record Office, London, Fol — 407 ገጽ 110

* ሰፍር ቁጥር ለማለት መሆን አለበት ።

3 አለቃ ዘነብ ገጽ 20 — 21 ። በሽታው የመጣው የጨርቋ (እሸት እህል ከመብላት የተነሣ መሆኑን አለቃ ወልደ ማርያም በገጽ 9) ላይ ጠቁመዋል ።

በሌላ ጽሑፍ ደግሞ ፣ ንጉሥ ኃይለ መለኮት ለዘመቻ ወዳ
ሩሲ ሔደው ሲመለሱ፣«ካሣ የሚባል ከቋራ ተነሥቶ ፣ ጐጃም
ንና በጌምድርን ፣ ስሜንንም አሸንፎ ፣ ቴዎድሮስ ተብሎ ነገሠ ።
ወደ ሸዋም መምጣቱ የማይቀር ነው» ተብሎ ስለ ተነገራቸው፣
ወደ ወሎ ተጉዘው ከራስ ዐሊ ጋር መወያየታቸውን ፤ በኋላም
ራስ ዐሊን ይዘው ወደ ሸዋ አምጥተው ዐሊ በቱለማ አገር እንደ
ቆዩ ፤ ወደ ወሎ ወደ በረሃው ክፍል ሔደው ሲቀመጡ በዚያ
መሞታቸው ተጽፏል ። እንደዚሁም ሦስተኛው ጸሐፊ ራስ
ዐሊ ሸሽተው የሔዱበት ዋቄ ዲቦ የሚባለው የደራ ባላባት እጃቸ
ውን ለቴዎድሮስ አሳልፎ ሊሰጣቸው መሆኑን በመገንዘባቸው ፣
ወደ ኃይለ መለኮት ልከው ስለነበረ መጥተው አዳኗቸው ይላሉ።([1])

ዐፄ ቴዎድሮስ ባለፈው ምዕራፍ እንዳነበብነው ፣ ደጃች
ውቤ «አልገባም» የሚል መልስ በሰጡአቸው ጊዜ ፣ «እንኳን
ይኸን ቁርጥማታም (ውቤን) ፣ ወሎን መትቼ የሸዋውን ንጉሥ
እይዘዋለሁ» ብለው የፎከሩት ይታወሳል ። በዚህ ምክንያት
በወሎ በየበረሃው የሸፈተው እንዳለ ሆኖ፣ የቀረውን የወሎ ተከ
ላካይ ከደመሰሱና የገቡላቸውን ሹማምንት እነ ደጃች ሊበንን
ሾመው በጥቅምት 1 ቀን 1848 ዓ. ም. ከወሎ ወደ ሸዋ ድንበር
መጥተው ፣ ግሼ ወንዝ አጠገብ ዋያት ላይ አደሩ ። በሦስተኛው
ቀን የግሼው አቶ ሀብተ ማርያም መያዙን ፣ ከዚያ ዐልፈው ወደ
ፍርኩታ (መንዝ) ምድር ሲደርሱ የይፍራታው ገዥ አቶ
በድሉ መግባታቸውን አለቃ ዘነብ ሲያመለክቱ ፣ አለቃ ወልደ
ማርያም በጥቅምት 7 ቀን የግሼው ሀብተ ማርያም ከበሩ ላይ
ጽኑ ውጊያ ካደረገ በኋላ መያዙንና ወንድሙ መሞቱን ፣ እነ
አቶ ሰሙ ንጉሥም እርሱን ለመርዳት መጥተው እንደ ነበረ
ከጠቀሱ በኋላ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ መንዝ ሲደርሱ ከጳጳሱ ከአቡነ
ሰላማ ጋር ሆነው ጳጳሱ በክህነት ፣ ንጉሡ በመንግሥት ሆነው
ቢያያቸው የምሥራቁ የግድም የኤፍራታ ሰው ሁሉ ደስ እያለው
አምኖ መግባቱን ፤ ወዲያውም ንጉሡ «በየአባትህ ግባ ፣ ሰጥ
ችሃለሁ ። አባት የሌለህ እኔን ደጅ ጥና ፤ አባትህ እኔ ነኝ» ብለው
የሸዋን ሰው እንዳስደሰቱት(*) ፤ ከዚህም አከታትለው ቴዎድሮስ

1 የብላቴን ጌታ ኅሩይ መጽሐፍ ገጽ 71—ዳግማዊ ዐጤ ምኒልክ ነጋ
ድራስ አፈወርቅ ገጽ 22

* በየአባትህ ግባ ማለት፣ባባትህ ሹመት ባባትህ ርስት ተሠማራ ፣
ከአባትህ ርስትና ሹመት ያልወረስህ ወደ እኔ ና ፣ እኔ እሰጥሃለሁ
ማለት ነው ።



በጥቅምት 14 ቀን ጅብ ዋሻ ሲደርሱ የጠራው ሀብተ ማርያም
ተዋግተዋቸው እንደ ሞቱና በዚህ ጊዜ ንጉሥ ኃይለ መለኮት
ከወሎ ጉዟቸው ጀምሮ ታማሚ ስለ ነበሩ፣ወደ ሰላድንጋይ ሔደው
ስለነበረ ቴዎድሮስ ቢገሠግሡ እንዳላገኗቸው ፤ በጥቅምት 16
ቀን የኃይለ መለኮት መኳንንት በምክር በአንኮበር ያለውን
የንጉሡን ቅጥር (ቤተ መንግሥት) «የጌታችንን ቤት ጠላት
አይግባበት» ብለው ማቃጠላቸውን ፤ የኃይለ መለኮት ሕመም
እየጸና ሔዶ በነገሡ በስምንት ዓመታቸው ፣ በኅዳር 30 ቀን ፣
ዐርብ ሌሊት ዐርፈው ደብረ በግዕ መቀበራቸውን ያመለክ
ታሉ ። ([1]) ደብረ በግዕ ያባ ሕፃን ሞዓ ጽላት ያለበት ቤተ ክርስ
ቲያን ነው ። በጐኑ የገሊላ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ይገኛል ።

በዚህ ጦርነት የግሼውም ፣ የጠራውም ሹሞች እነ አቶ
ሀብተ ማርያም ዐፄ ቴዎድሮስን በግሼ ፣ በጅብ ዋሻ ጠንክረው
እየተዋጉ ካፄ ቴዎድሮስ ወገን ብዙ ወታደር ከፈጁ በኋላ ፣ ሲሞ
ቱና ሲማረኩ ይኸን በመሰለ የጦርነት ሰዓት ፣ ከወገን ሁልጊዜ
ከዳተኛ እንደማይጠፋ በየዘመኑ ያለውም የዓለም ታሪክ እንደ
ሚያሳየን ፣ አሁንም የኤፍራታው አቶ በድሉ በሩቅም በቅር
ቡም ላፄ ቴዎድሮስ ሰላይና መንገድ መሪ ሆኖ ማገልገሉ በየ
መጽሐፉ ተጠቅሷል ። ገና ዐፄ ቴዎድሮስ ሸዋ ሳይመጡ ኃይለ
መለኮት በወሎ ከራስ ዐሊና ከወይዘሮ ወርቂት ጋር ለመከ
ላከል ያደረጉትን የስምምነት ምስጢር ተከታትሎ ላፄ ቴዎድ
ሮስ እንደ ላከባቸው አለቃ ወልደ ማርያም ጠቅሰውት ይገ
ኛል ። ([2]) በዚሁም ወቅት የንጉሥ ኃይለ መለኮት እናት ከአዲሱ
ንጉሠ ነገሥትና ከጳጳሱ ሞገስ ለማግኘት ሲሉ ገብተዋል ።

ከወልደ ማርያም አጻጻፍ ይልቅ ፣ ያቶ በድሉ ክዳት በጸሐፌ
ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ብርዕ የበለጠ በዚህ ዐይነት ተብራርቷል ።
«..........ይሁዳ ክርስቶስን አሲዛለሁ ብሎ አይሁድን እየመራ እንደ
መጣ ፣ አቶ በድሉም የይፍራታው ገዥ ካባትዎ (ካባታቸው)
ጀምረው ሾመው ፣ ሸልመው የሚያኖሩትን ጌታውን ዐፄ ኃይለ

1 ብ.ጌ. ኅሩይ ገጽ 8 — 9

2 አለቃ ወልደ ማርያም ገጽ 13

መለኮትን ከድቶ ፣ ወደ ዐፄ ቴዎድሮስ ገብቶ መንገድ መሪ ሆኖ መጣ»[1] የሸዋው አቶ በድሉ በኃይለ መለኮት ፊት ፣ ስሜነኛው ብላታ ኮከቤ በደጃች ውቤ ፊት በተመሳሳይነት ጌቶቻቸውን የመክዳት አቅዋም ሲኖራቸው ፣ ከኮከቤ የበድሉ ክዳት የበለጠ ግልጽ ይመስላል ። የክዳታቸው ዓላማ የእድር ባይነትና የሹመት ፍሊጋ እንጂ ፣ ላገር አንድነት ሲሉ አለመሆኑን የተረዱት ሐቀኛው ቴዎድሮስ ሁለቱንም ገሸሽ እያደረጉ ፣ ከጦርነት በኋላ ሹመቱን የሰጡት ፣ ለየጌቶቻቸው ታምነው የወጉዋቸውን ወይም በዘር አለዚያም በችሎታ ያስተዳድራሉ ፤ እኔንም አይከዱም ብለው የተማመኑባቸውን ነው እንጂ እነዚህን አቅርበው ሾመው ሸልመው ባለሟል አላደረጉም ። ባሁኑ ጦርነት ደህና አድርጎ ወግተዋቸው ቆስለው የተማረኩትን አቶ በዛብህን ፣ ወደፊት እንደምናነበው ፣ ከመርድ አዝማች ኃይሌ በኋላ በሸዋ ላይ ሲሾሙአቸው ቴዎድሮስ በጠባያቸው ጉበዝን እንጂ ከዳተኛን አይወዱም ማለት ነው ።

የሆነ ሆኖ ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ በነአቶ በድሉ መሪነትና አስተናባሪነት ከግሼ ፣ ከኤፍራታና ከመንዝ ዐልፈው ፣ ጳጳሱን አቡነ ሰላማንና ጓዛቸውን ቁንዲ ላይ ሰፍሮ እንዲጠባበቅ አድርገው ፣ እርሳቸው የኃይለ መለኮትን ሞት አልሰሙም ነበርና ወደ ደብረ ብርሃን ፣ ከዚያም አታክልት ወደሚባለው ሥፍራ እንደ መጡ የንጉሥ ኃይለ መለኮትን መሞትና መኳንንቶቻቸው ልጃቸውን ምኒልክን ይዘው ወደ በረከት ሔደዋል ማለትን በሰሙ ጊዜ ፣ ወደ በረከት ራስ እንግዳን ፣ ቢትወደድ ብሩንና ቢትወደድ ውቤን ልከው ፣ እርሳቸው የንጉሥ ኃይለ መለኮትን ሞት ለማረጋገጥ በነ አቶ በድሉ መሪነት ከአታክልት በቶራ መስክና በጠላሳ በኩል ቁልቁል ወርደው ፣ ደብረ በግዕ ደረሱና መቃብሩን አስቆፍረው የኃይለ መለኮትን ሬሳ አዩ ። ምንም የፖለቲካ ጠላታቸው ቢሆኑ ፣ ሬሳቸውን ሲያዩ እንዳዘኑና እንዳለቀሱ ጸሐፊዎቹ አረጋግጠዋል ።[2]

ከዚህ በኋላ ዓፄ ቴዎድሮስ የቀራቸው ምኒልክን ይዘው ለመመከት ፣ በየአለበት የተበታተኑትን መኳንንት መደምሰስ

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ምዕ. 15 ገጽ 45
2 አለቃ ዘነብ ገጽ 23 ፣ ነጋድራስ አፈወርቅ ገጽ 12



ነው ። በዚህ ጊዜ ምኒልክ 12ኛ ዓመታቸውን ይዘዋል ። በኃይለ መለኮት ሞት አዝነው እርሳቸውን ይዘው ለመከላከል የተዘጋጁት የሸዋ መኳንንት አቶ እንዳርጋቸው ከልጃቸው ከኃይሌ ጋር ፣ አቶ ሸሸጉ ፣ አቶ ሀብቱ ከልጃቸው ከአባይሬ ጋር ፤ አቶ በዛብህ (በዙ አባ ድከር) አቶ አቦዬ(*) ፣ አቶ አባ ውርጃ ፣ አቶ እንተን ይስጠኝ ከልጃቸው ከከተማ ጋር ፤ አቶ ወልደ ገብርኤል (**) አቶ ገርማሜ (***) ፣ አቶ ወልደ ጻድቅ (****) ፣ አቶ ናደው (*****) ፣ አቶ አባይነህና ሌሎችም አሉ ። ነገር ግን እነዚህ ሁሉ አንደኛ መሪያቸው ኃይለ መለኮት ስለ ሞቱና ምኒልክንና ወጣት ስለሆኑ ፣ በደንብ የተዘጋጀውንና የታጠቀውን ዓፄ ቴዎድሮስን ጦር በፊት ለፊትና አስተባብሮ ለማዋጋት የቻለ መሪ ስለ አላገኙ ፣ ጦርነቱ ሁሉ የተደረገው በተበታተነ ሁኔታ ግማሹ በግሼና በመንዝ ፣ ግማሹ በአንኮበር ፣ የቀረውም በምንጃርና በበረከት ነበር ። ይኸም ሁኔታ ባንድ ንጉሠ ነገሥታዊ ሥልጣን ለሚመራው ለቴዎድሮስ መንግሥትና ለጦራቸው አመቺ ሁኔታ እንደ ፈጠረ አይጠረጠርም ።

በዚህ መካከልም ፣ በሸዋ ዙሪያና በሸዋ ውስጥ ያሉት አርሞዎች የንጉሥ ኃይለ መለኮትን መሞትና ዓፄ ቴዎድሮስን መምጣት በመስማት ተነሥተው ፣ ከሸዋ መኳንንት ጋር ጦርነት ቀስቅሰው ስለ ነበረ፣ በማናቸውም ረገድ ለሸዋ መኳንንት ጊዜው የተመቸ አልነበረም ። ቢሆንም በግሼና በመንዝ እነ አቶ ሀብተ ማርያም በጀግንነት እየተዋጉ ካፄ ቴዎድሮስ ብዙ ወታደር እንደ ገደሉ ሁሉ ፣ አሁንም እነ አቶ በዛብህና እነ አቶ ሀብቱ እየተዋጉ ከቴዎድሮስ ወገን ደጃዝማች ገለታ ሲሞቱ ፣ የጠራው ሀብተ ማርያም የሞቱት አቶ በዛብህም የቆሰሉት በዚህ ጊዜ ነው ። ምኒልክንም ለማባረር በምንጃር አድርገው ከሰምን ተሻግረው ወደ በረከት የሔዱት እነ ራስ እንግዳ ምንም እንኳ የመጨረሻው አሸናፊነት የነርሱ ቢሆንም ፣ ከነርሱ ወገን አራት የመቶ አለቆች ሲሞቱ ከምኒልክ ወገን እነ አቶ ሸሸጉ ሞተው ፣ በመጨረሻ እነ አቶ በዛብህ ቆስለው ተማረኩ ።[1]

* የንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስና የደጃች በሻህ አባት
** ደጃች ወልደ ገብሬል አባ ሰይጣን የራስ ብሩ አያት
*** የሞጃው ደጃች ገርማሜ
**** በኋላ ያንኮበር ወሀኒ አዛዥ የሆኑት
***** የራስ ተሰማ አባትና ያፄ ምኒልክ ሞግዚት
1 አለቃ ዘነብ .... ገጽ 22 — 24

ከዚህ በኋላ፣ እነ አቶ ሀብቱና እነ አቶ አንዳርጋቸው(*) ባንድ ወገን ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ በሥርዐት ነግሠው ባማረ ግርማ የኢትዮጵያን አንድነት ለመመሥረት ከስመ ጥሩው መናገሻ ከተማ ከጐንደር መጥተው የመንግሥትን አቅዋም ሲያጠናክሩ በይፋ ባናገሩት ዐዋጅ ላይ፣ «አባት ያለህ ያባትህን ስጥቻሃለሁ ። አባት የሌለህ እኔን ደጅ ጥናኝ» ብለው ስለ ዐወጁ ፣ በዚሁ ብዙ ሰው ተደስቶ እንደ ገባላቸው ፣ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ባለቤት የራሳቸው የንጉሥ ኃይለ መለኮት እናት ወይዘሮ በዛብሽ ሳይቀሩ ለንጉሡ መግባታቸውን በማጤን ፣ ዕቅመ አዳም ያልደረሰውን ልጅ ምኒልክን ከነራስ እንግዳ ፊት ይዞ ዳገት ቁልቁለቱን መዞሩና ውጊያውም እንደ ሰለቻቸው ይታያል ።

ስለዚህ ምክር ተያዘና ግማሹ ፣ «ምኒልክን ይዘን ወደ ቴዎድሮስ ከመግባት ወደ ኦሮሞ አገር እንሽሽ» ሲል የቀረው ፣ «ወደ ቴዎድሮስ እንግባ» ይል ጀመር ። በዚህም የምክር ስብሰባ ላይ አንዱ ፣ «ምንም ልጅ ቢሆን እስቲ የርሱን አሳብ እንጠይቀው» ብሎ ልጅ ምኒልክ ከሁለቱ አማራጭ መንገድ ሲጠየቁ ወደ ኦሮሞ መሸሽን መረጡ ይባላል ። በዚሁ ጊዜ እላይ ስማቸው የተጠቀሰው አቶ አንዳርጋቸው ፣ «ንጉሡ 'አባት ያለህ ያባትህን ስጥቻሃለሁ' ብለው ቃል ከሰጡ ፣ ቃል ኪዳናቸውን የማያፈርሱ ቆራቢ ንጉሥ ናቸው ፤ አቡነ ሰላማም ደግ ጳጳስ ናቸው ይባላልና እንግባ» ብለው ፣ ለምኒልክም ለመኳንንቱም አስረድተው ወደ ዐፄ ቴዎድሮስ የመግባቱ ነገር ተወሰነና መልእክተኛ አስቀድመው ፣ እነሱም ወደ ዐፄ ቴዎድሮስ መንዝ ዠመሩ ።

በዚህ ጊዜ እነ ራስ እንግዳ ወደ በረከት በዘመቱበት ሰዓት ንጉሡ ወደ ደብረ ብርሃን ሒደው ፣ ከዚያም ደብረ ሊባኖስ ዘልቀው ተሳልመው ተመልሰው ፣ በደብረ ብርሃን በኩል ሲያልፉ «በሬሳ ወንዝ ፣ ከባሕሩ ላይ የተጣለ ፣ 300 የንጉሥ ኃይለ መለኮት ጠበንጃና መድፍ አለ» ብሎ ወሬ ነጋሪ ስለ ጠቆመ ፣ ወደዚያ ሒደው እየዋኘ መሣሪያውን ላወጣ በቅሎም ፈረስም ሸላልመው ከዚያ በጠባሴ ኮሶ ዐልፈው ሞጣጢት በሠፈሩበት ወቅት ፣

---

* አንዳርጋቸውን ፣ ዘነብ እንደ ተማረኩ አድርገው የጻፉት አይመስልም ።



በፊተኛው ጊዜ እንዳደረጉት ፣ ያንኮበር ካህናት ታቦት ይዘው መጥተው ፣ ወደ ንጉሡ ቀርበው ሁሉም እጅ ከነሣ በኋላ ካህናቱ ፣

«እስመ ጽድቅ ቃሉ ለቴዎድሮስ
ወኵሉ ግብሩ በሃይማኖት »(*)

እያሉ በመወረብ አስደሰቱዋቸው ። የመሃይምኑ ገጣሚም ፣

«ሺህ ሐመር ፣ ሺህ ዳለች ፣ ሺህ ቦራ.........ይሉት
የነበረ የሸዋ ፈረስ ፣
አንድ ጥርኝ ቀረ፣ ቢዘልቅ ቴዎድሮስ» ይል ጀመር ።

አለቃ ወልደማርያም በጽሑፋቸው «.........በኅዳር 10 ቀን (1848) ሰኞ ተዋጉ ። ቁጥር የሌለው ሰው ከነራስ እንግዳ ወገን አለቀ ። ከወዲህም (ከሸዎችም) የታወቁት እነ አቶ ሸሸጉ እየ ተዋጉ ሞቱ ። አቶ በዛብህ ተዋግቶ ድል ሆኖ ተያዘ» ካሉት አከ ታትለው ፣ ስለ ምኒልክ አገባብ ቀጥሎ ያለውን አስፍረዋል ። «ከዚህ በኋላ እነ አቶ ሀብቱና እነ አቶ ገብሩ ልጅ ምኒልክን ይዘው ወደ ቴዎድሮስ ገቡ ። ቴዎድሮስ ግን፣ ምኒልክን እንደ ልጅ ወደው ፣ እንደ ንጉሥ አክብረው ከተቀበሉ በኋላ ሜዳውን በገርማማ ወጥተው ከነራስ እንግዳ ተገናኙ» በማለት አስረ ድተዋል ። ([1])

በዚያን ጊዜ ፣ ምኒልክን ለቴዎድሮስ ይዘው በገቡት መኳ ንንት ላይ እንደዚህ ተብሎ ተገጠመ ።

«ቁርጡን ዐወቁና አለመኖርህን
በረከት አገቡት ጌታዬ (ኃይለ መለኮት) ልጅህን»([2])

ቢሆንም ፣ ምኒልክ ባጠገባቸው ከነበሩት መኳንንቶች ጋር ቢገቡና ቴዎድሮስ በፍቅር ዐይን አክብረው ቢቀበሉዋቸውም ፣ የቀሩት መኳንንት እጃችንን ለጠላት አንሰጥም በማለት ቁንዲ ከጓዝ ጋር የሰፈረውን የንጉሥ ወታደር እየወጉ ስላስቸገሩ ፣ ወደ

---

* የቴዎድሮስ ቃሉ ትክክል የሚያደርገውም ሁሉ በሃይማኖት ላይ የተመሠረተ ነው ።
1 ዐፄ ቴዎድሮስ ታሪክ የራስ እምሩ የእጅ ጽሑፍ አለቃ ወ.ማ.ገጽ 13
2 አለቃ ዘነብ ገጽ 13

አንኮበር መጥተው ምኒልክን ነጥቀው ሊወስዱ ይችላሉ በሚል ጥርጣሬ በምኒልክና በመኳንንቶቻቸው ሰንሰለት አግብተ ውባቸው ነበር ይባላል። የ12ቱ ዓመት ወጣት ምኒልክ ፣ እስከዚህ ጊዜ ድረስ አንጐላላ ተወልደው በአንኮበር ሲያድጉ ከጌትነት ኑሮ በቀር የሰንሰለት እስራትን አይተው ስለማያውቁ ፣ በደረሰባቸው እስራት ተደናግጠው ፣ ሌሊቱን ሲያለቅሱ አድረው ኖሮ ፣ ቴዎድሮስ የምኒልክን ማልቀስ በሰሙ ጊዜ «ፍቱለት» ብለው አዘዙ ።([1]) እንደዚሁም ፣ «አባትህ ምን አውርሶህ ሞተ?» የሚል ጥያቄ ከንጉሡ ቢቀርብላቸው ፣ ምኒልክ ከታባቸውን አሳዩ። ከታቡም ቢፈታ ብዙ ሀብት ያለበትን ሥፍራ የሚጠቁም ስለ ነበረ ፣ በዚያ እየተመሩ ቴዎድሮስና ሹማምንቶቻቸው ብዙ ሀብት አገኙ ይባላል ።

በጐጃምና በበጌምድር ፣ በስሜንና በወሎም ከአውራጃ አውራጃ እየተዘዋወሩ ፣ የአገርን አንድነት ለመመሥረት ዐፄ ቴዎድሮስና ጦራቸው ብዙ የጉዞ ድካም እንደ ተቀበሉ አይጠረጠርም ። አሁንም ያን ሁሉ ተራራና ቋልቋለት የሞላበትን የግሼንና የኤፍራታን ፣ የመንዝና የግድምን ወረዳዎች ዐልፈው ደብረ ብርሃንና አንኮበር በደረሱበት ሰዓት ፣ የጉዞው ፍጻሜ ሆኖ የጸጥታና የሰላም ጊዜ አግኝተው የማረፍ ዕድል አላገኙም ። ሊያገኙም አይችሉም ። ስለዚህ ንጉሡ ጓዛቸውን በቁንዲ አስቀምጠው ፣ ራሳቸው ከቁንዲ አንኮበር ፣ ከአንኮበር ደብረ ብርሃን ፣ ከደብረ ብርሃን በአታክልትና በጠራ በኩል ዐልፈው ደብረ በግዕ ፣ ከደብረ በግዕ እንደገና ደብረ ብርሃን ፣ ከዚያ ደብረ ሊባኖስ ፣ እንደገና ተመልሰው አንኮበርና ጨፋ ፣ ከዚያ ወደ ቶራ መስክ ፣ የደጋውን ብርድና የቆላውን ሙቀት ችለው ፣ ያለ ዕረፍት ሲዘዋወሩ የጦር አለቆቻቸው እነ ራስ እንግዳ የምኒልክን ጦር ለማባረር የቶራ መስክን ፣ የቅምብቢትን ፣ የምንጃርን ፣ የቡልጋንና የአሳግርትን ፣ ያን የመሰለ ዳገትና ቋልቋለት ወርደው ፣ ድልድይ የሌላቸውን ወንዞች በመሻገር ፣ ቆንጥር የመላበትን ጫካ በመተላለፍ እስከ በረኸት በረሃ መድረሳቸውና ምኒልክን ከነመኳንንቶቻቸው ወደ ቴዎድሮስ እንዲገቡ በጦር ኃይል ማስጨነቃቸው

---

1 ሳይጠረዝ የቀረው የብላቴን ጌታ ኅሩይ መጽሐፍ ገጽ ...38—39



የመንፈሳቸውንና የጉልበታቸውን ጽናት ፣ ለጌታቸው ለቴዎድሮስ ያላቸውን ፍጹም ታዛዥነትና ታማኝነት ያሳያል ። በምሥራቅ በኩልም አገር አሰሳ ፣ ቀለብ ፍለጋ መርድ አዝማች ስብስቴ ወደ ከተሙት ወደ ሐራምባ እኝሁ የራስነት ማዕረግ በመሸከም የሚወጡት ፣ የሚወርዱት እንግዳ መላካቸውን ዘነብ ጠቅሰውታል ።

የዚህኛውም የሐራምባው የጉዞ መሥመር እንደዚያው እንደ በረኸት ባይጠነክርም ፣ ከደብረ ብርሃንም ቢሆን ከአንኮበር ለተነሣ እንግዳ ጦር ጉዞው በጣም አስቸጋሪ ነው ። በሐራምባና በአንኮበር መካከል ብዙ ውጣ ውረድ ያለበትን ተራራማ ሥፍራ መውረድ ፣ በአልዮ አምባ አካባቢ ያለውን የአዳልን በረሃ ማቋረጥ ፣ የመንጥቅን ወንዝ ተሻግሮ እንደገና ሽቅብ ወደ ሐራምባ መውጣት ያስፈልጋል ። በዚህም ላይ አሁን ያሉበት ከኅዳር እስከ የካቲት ወር ያለውም ጊዜ ቀን ሐሩሩ ፣ ሌት ቁሩ ከጦርነቱና ከውጣ ውረዱ የድካም ጉዞ ጋር ከባድ ነው ።

በዚህ ምክንያት ፣ ከቤተሰቡና ከቤቱ ተለይቶ ከጐጃም ፣ ከዳሞት ፣ ከቤጌምድር ፣ ከጋይንት ከስሜንና ከወሎ የመጣው ጦር ወጊያ ብቻ ሳይሆን የጉዞው ውጣ ውረድ ስለ መረረው ፣ ማንጎራጎሩን አለቃ ዘነብ በጽሑፋቸው ላይ እንደዚህ ሲሉ ጠቅሰውታል ። «..........ራስ እንግዳን ወደ ምሥራቅ ከመርድ አዝማች ስብስቴ ከተማ ሐራምባ ቀለብ (ለመጫን ወይ ለመዝረፍ) በሰደዷቸው ጊዜ ከንጉሡ ጋር የቀረው ወታደር እንዲህ ብሎ አንጎራጎረ ። «እነዚህን አስቀድሞ መስደዱ እኛንም በኋላ ኢየሩሳሌም ወስዶ ሊያስፈጀን ነው» ሲሉ ሁለት ወታደሮች ሌሊት አንኮበር ላይ (ጉረቤላ) ከአፋፉ ሆነው ፣ «ለዚህ ንጉሥ ለቴዎድሮስ ዕንጨት የሰበረ ፣ ውሃ የቀዳ ፣ ሣር ያጨደ ፣ የተከተለውም ውጉዝ ይሁን ። ይህ ቃል የአቡነ ሰላማና የዕጨጌ ወልደ ማርያም ነው» እያሉ ገዘቱ ። በዚህ ጊዜ ዐፄ ቴዎድሮስ ብዙ ሠንጋ ታርዶ ግብር ሊበላ ሲል ፣ ግግሹ ወደ ግብር ተጠርቶ የቀረው ቀለብ እንዲያመጣ ወደ ሐራምባ ሒድ በተባለ ጊዜ

«እግዚኦ! እግዚኦ!» እያለ በመጮህ እምቢታውን ሲያሰማ ቴዎድሮስ ወደ ጨፋ ወርደው(*) ጠበንጃና ጦራቸውን እንደ ያዙ ከፈረሳቸው ላይ ወጥተው ፣ «የኔ የሆንህ» ብለው ታማኙንና ታዛዡን ከለዩ በኋላ በቁጣና በብስጭት ከሠራዊታቸው ውስጥ በጠበንጃ ሰደፍ የመቱት ፣ ጦር ወርውረው ጠበንጃ ተኩሰው የሳቱት እንዳለና በዚህም የትርምስ ጊዜ ግማሹ ሲመታ የቀረውም ሲሸሽ በመካከሉ አቡነ ሰላማና ዕጨጌ ወልደ ማርያም እንደ ገላገሉ ፣ ከዚያም ንጉሡ እንደ ተበሳጩ ወደ ቆራ መስከ መውጣታቸውን ያመለክታሉ ።[1]

እነዚያም በጳጳሱና በዕጨጌው ስም ሲገዝቱ የነበሩት ወይም በዚህ የግዝት ዐድማ የተገኙት ንጉሡ ወደ ቆራ መስክ ከወጡ በኋላ ፣ በስላይ ተይዘው ቀርበው በአደባባይ የተፈረደባቸውን ዐርባ ስምንቱን ሰዎች በጥይትና በጐራዴ እያስመቱ አስገደሏቸው ። ከዳሞት የመጡና ክህነት ፣ ቅስና ሳይኖራቸው በጳጳሱ ስም የገዘቱት ግን ፣ እንደ ታሰሩ ተቀመጡ ። አባ ሰላማ «የዚህ ክፍል ጉዳይ የእኔ ነውና ለእኔ ይስጡኝና ልቅጣቸው» ቢሉ ፣ ንጉሡ ተናደዋልና አልተቀበሏቸውም ።

ከዚህ በኋላ ፣ በቆራ መስክ ወደ ደብረ ብርሃን ሔደው ፣ ከነአቶ በድሉም ከራሳቸውም መኳንንት ጋር መክረው ዘክረው ፣ ከዚህ በፊት «በየአባትህ ግባ» ብለው በዐወጁ ጊዜ ሰዉ ደስ ብሎት «ያባቴ ሹመት ፣ ያባቴ ርስት ይገባኛል» እያለ በየምክንያቱ የቀረበት ሁሉ ሙግትና ክርክር በማንሣቱ ፣ ችግር ተፈጥሮ ነበርና ለጐጃምና ለቤጌምድር ሕዝብ «ኢያሱ የደነገጉት ይርጋ» እንዳሉ ፣ አሁንም ለሸዋው «የሣህለ ሥላሴ ሥርዓት ይርጋ» ሲሉ እንደ ወሰኑ ይነገራል ። እንደዚሁም በሸዋ፣«ቀድሞ አንዱ በገደለ ቤተዘመዱ እየተያዘ ይጉላላል ፤ ይወረሳል» ማለትን ስለ ሰሙ ፣ «ቢገድልም ገዳዩ ይሙት እንጂ ዘመዱ በግድያ ካልመከረ ፣ በጠቡም ላይ ካልነበረ (ካልተባበረ) አይሙት» ብለው ዐወጁ ።

---

* ጨፋ ከአንኮበር ከተማ በደቡብ ምዕራብ በኩል 5 ኪሎ ሜትር ያህል ቁልቁል ወርዶ የሚገኝ ጨፈጨፍማና ሜዳማ ሥፍራ ነው ። አንኮበር ተራራማና ወጣገብ ስፍራ ስለሆነ ፣ ምናልባት ብዙው ጦር ሠራዊት የሰፈረው ከእዚህ የጨፋ ሜዳ ላይ ነው ማለት ነው ።

1 አለቃ ዘነብ ገጽ 24 — 25



ሸዋን በዚህ ዐይነት ከጐንደር ከማዕከላዊው መንግሥት ጋር ካገናኙ ወዲህ፣ ላንደኛው ለንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ልጅ ለኃይለ ሚካኤል ከጥንት እንደ ነበረው ሥርዓት የመርድ አዝማችነት ማዕረግ ጨምረው የሸዋን ጠቅላላ ግዛት ፣ ላቶ አንዳርጋቸው የጦር አበጋዝነቱን ከሾሟቸው በኋላ ፣ ምኒልክን በቢትወደድ ውቤ ጠባቂነት እንደ ያዙ ከደብረ ብርሃን በጠባሴ ኮሶ ፣ በሳላይሽ ፣ በዋዩ ፣ በጅሩ አፋፍ እየተጓዙ እንደ ደረሱ በመራቤቴ ሊያልፉ ነው እየተባለ ከተወራ በኋላ ፣ ይኸኛው መሥመር ቀረና ወደ ግራ ቀና ብለው በሰላሌ ፣ በጃርሶ አድርገው ደብረ ሊባኖስን ተሳልመው አባይ ደረሱ ። ሠራዊቱ በውሃ ጥም ተቃጥሎ ነበርና በጥም ባረረ ጉሮሮው በጥድፊያ ሲጠጣ ብዙ ሰው ሞተ ፤ እንደ ልብ የሚያሻግርም መልካ እየጠፋ ፣ የአባይ ወንዝ አንዳንድ ሰውና ከብት እየቀማ ማስቀረቱ ፣ ፈንግል የሚባለውም በሽታ ተነሥቶ የነበረው በዚሁ ወቅት እንደ ነበር ይወሳል ።

በዚህ ሁሉ ችግር መካከል፣ ንጉሡና የሠራዊታቸው እጋማሽ ወንዙን ተሻግሮ ከማዶው እንዳለ የወዲህኛው እስኪሻገር ድረስ እዚያው እዳር ሆኖ ሠራዊቱ ተጠቃሎ ከተሻገረ በኋላ ከዚያ ተነሥተው ጐጃም ሲገቡ እነዚያን «ለዚህ ንጉሥ ማር አትጨድ ፤ ውሃም አትቅዳ ፤ አትከተለው» እያሉ ሲገዝቱ የተያዙትን ሁለቱን የዳሞት ተወላጆች በዘመዶቻቸው ፊት እጅና እግራቸውን እያስቆረጡ በስቅላት ቀጧቸው ። ከዚህ በኋላ ለጐጃም ግዛት ራስ እንግዳን ሾመው ፣ ለቢትወደድ ውቤም በዚሁ በጐጃም አንድ ክፍለ ሀገር ሰጥተው ፣ በየመንገዱ የሸፈተውን እየቀጡ ፣ ለታመነው ሹመት እየሰጡ ፣ በአራት መከራከር ፣ በደምበጫ ፣ በአመዳሚት ፣ በሚዛን ፣ በደብረ መይ (መዊዕ)፣ በአምባ ጫራ በኩል ዐልፈው ፣ ደብረ ታቦር ደርሰው ፣ እያረፉም ውሳኔም እየሰጡ ሰንብተው ከሸዋ በየካቲት ወር የተነሡት በሐምሌ ወር ጐንደር ገቡ ።[1]

ከአንኮበር ከመነሣታቸው በፊት ፣ ወይዘሮ ትደነቂያለሽ የሚባሉትንና በደም ግባት የተዋቡትን የንጉሥ ኃይለ መለኮትን ባለቤት ቴዎድሮስ አይተዋቸው ነበር ። ኃይለ መለኮት

---

1 አለቃ ዘነብ ገጽ 25—27 ። አለቃ ወልደ ማርያም ገጽ 14—20
Histoire Pol. Rel. J. B. Coulbeaux vol. 11, p. 421

ከትደንቂያለሽ በፊት ከምኒልክ እናት ፣ ከወይዘሮ እጅጋየሁ ጋር ይቀመጡ ነበር ። በኋላ ግን ፣ የኘህ ሴት የቁንኧና ውበት ስለ ባሰባ ቸው ፣ እጅጋየሁን ትተው እርሳቸውን አግብተው ይኖሩ ነበር ። ቴዎድሮስ አንኮበር በነበሩበት ሰዓት የባላቸው ሞት ያሳዘናቸው ሴትዮ ፣ አሽናፊውን ቴዎድሮስን እጅ መንሣት ግዴታ ሆኖባቸው ቀርበው እጅ ሲነሡ ፣ ንጉሡ «ከእኛው ጋር ወደ ጐንደር እን ሒድ» ቢሏቸው ሴትዮዋ በትሕትና ፣ «ጃንሆይ አሁን አብሬ ለመሔድ አልተዘጋጀሁም ። በኋላ ተዘጋጅቼ ስጨርስ በትግሬ በኩል ዐልፌ ፣ አክሱምን ተሳልሜ ወደ ጐንደር እንድመጣ ይፍ ቀዱልኝ» ብለው አስፈቀዱ ።

ወጣቷ ወይዘሮ ትደንቂያለሽ ስንቃቸውን በደንብ አዘጋ ጅተው ከጨረሱ በኋላ ፣ ወደ አክሱም ሔደው በልባቸው እንደ ተመኙት ፣ የጽዮን ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ከተሳ ለሙ በኋላ ፣ 'ከኃይለ መለኮት ወዲያ ዓለም አልሻም' ብለው ከአ ክሱም ወደ ምጥዋ ሔደው ፣ በብዙ ችግር መርከብ ፈላልገው ወደ ኢየሩሳሌም በመጓዝ ከዚያ በምነና ተቀምጠው ፣ እዚያው ሞተው በኢትዮጵያ ገዳም ተቀበሩ ። (1)

የዚህም ወሬ ቆይቶ ላይ ቴዎድሮስ ይደርሳቸዋል ። በዚያው ወቅት የንጉሥ ኃይለ መለኮት እናት ፣ የመራቤቴዋ ባላባት ፣ አሮጊቷ ወይዘሮ በዛብሽ ላይ ቴዎድሮስ የትውልድ አገራቸውን የመራቤቴን ወረዳ ሹመት እንዲሰጧቸው የልመና ማመልከቻ ጽፈው ሲደርሳቸው ፣ የሁለቱ ሴቶች ሁኔታ በጣም ይገርማ ቸውና ኃይለ ቃል ያለው ዐረፍተ ነገር መወርወር የሚያውቁት ቴዎድሮስ ለአካባቢያቸው ፣

«አያችሁ ጉድ ፣ የሚስት መናኝ
የእናት ሹመት ለማኝ» አሉ ይባላል ።

1 የሕይወት ታሪክ — ብላታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ገጽ 40




ንጉሥ ኃይለ መለኰት ሣህለ ሥላሴ
(ከለቱር ዱ ሞንድ መጽሐፍ)



የአንኮበር ከተማ
(ከአባ ማስያስ መጽሐፍ)

## አፄ ቴዎድሮስ በ1848 ዓ.ም ሸዋን ለማስገበር የመጡበትንና የተመለሱበትን የጉዞ መስመር የሚያሳይ ሰሌዳ



## ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት

### የእቴጌ ተዋበች ዐሊ ዕረፍት

እቴጌ ተዋበች ፣ ከወሎና ከየጁ ባላባቶች የዘር ግንድ የወረዱ ባላባት ናቸው ። አባታቸው ራስ ዐሊ የመጨረሻው መስፍን አያታቸው እቴጌ መነን መሆናቸውን ባለፈው አንብበናል ። የእቴጌ መነን አባት ደጃች (ወይም ይማም) ሊበን የወረሂመኑና የውጫሌ ባላባት ናቸው ። አሁንም ዐመዶ በሽር የቴዎድሮስን ዐይን አላይም ብሎ ፣ በወሎ ላይ ቴዎድሮስ የማይጠመድ የሺፍታ ባላጋራ ሆኖ የሚያውከው ለእቴጌ ተዋበች አባት ለራስ ዐሊ የአጉት ልጅ ነው ። እቴጌ ተዋበች ግን ፣ ገና ቴዎድሮስ በሽፍትነትና በደጅ ጥናት ላይ እንደ ነበሩ ከተጋቡ ዠምሮ እነዚህኑ ሁሉ የባላባትና የሚያኩሩ ዘመዶቻቸውን እርግፍ አድርገው በመቀው ፣ ዕድላቸውን ከባለቤታቸው ጋር ያስተሳሰሩ ታማኝ የጓደኛ ባለቤት ሆነው ኖረዋል ።

የታመኑላቸው ካሣ ፣ ንጉሠ ነገሥት በመሆናቸው እርሳቸውም የእቴጌነት አክሊል ቢቀዳጁም ያባ ታጠቅ የቴዎድሮስ ሕይወት ሁል ጊዜ ዘረት ፣ ሁል ጊዜ ጦርነት ስለሆነና በአብዛኛውም ዘረትና ጦርነት እቴጌይቱ ንጉሠ ነገሥቱን መከተል ስለ አለባቸው ፣ በዘመናቸው ከገጠማቸው የተድላና የደስታ አዱኛ ፣ የሰላምና የጸጥታ ጊዜ በዙረት ፣ በሁካታ ፣ በሥጋትና በጭንቀት ያሳለፉት ጊዜ መብለጥ አለበት ። በያለበት የሚፈነዳውን ሽፍትነት ለመደምሰስ ንጉሡ በተጓዙ ቁጥር ፣ «ያሸንፉ ይሆን ወይስ ይሸነፉ ይሆን? ተመትተው ይወድቁ ይሆን ወይስ ይድኑ ይሆን?» እያሉ መሸበር የሚስት ሁሉ በተለይ እንደ ተዋበች ዘመዶቿን ለባሏ ፍቅር በሠዋች ዘንድ የበለጠ ዐይነተኛው ዕድል ነው ።

በ1851 ዓ.ም. ንጉሠ ነገሥቱ ፣ ዐመዶ በሽርን ለመውጋት ወደ ወሎ ሲመጡ እቴጌይቱ — እንደ ታመሙ በአልጋ ይጓዙ ነበር ።

ለአየር መለወጥም ተብሎ ወደ ወረሂመኑ ወስደዋቸው ነበር ። ነገር ግን ፣ ሕመማቸው እየጠነከረ ሔዶ በነሐሴ 13 ቀን ማረፋቸውን አለቃ ዘነብ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል ። «......ንጉሥ ቴዎድሮስም...... ወደ ወሎ ተጓዙ ። ይቴጌ ተዋበች ታመው ነበር ። ከዐርብ ገበያ ዠምሮ በአልጋ ላይ ይጓዛሉ (ይጓዙ ነበር) ። በወርኃ ሰኔ ወረሂበኖ(*) መቅደላ ደረሱ ። ከጋይንት ዠምሮ እስከ ወሎ ድረስ ፈረስ በቅሎው አህያውም አለቀ ። ......ሰዉም ተርቦ ነበር ።...... ወደ ዐመዴ በሺርም ገሠገሡ ። ሳያገኙት ተመለሱ...... ። በነሐሴ 13 ቀን ረቡዕ ማታ ይቴጌ ተዋበች የንጉሥ ቴዎድሮስ ምሽት (ሚስት) ከዚህ ዓለም መከራ ዐረፉ......»

ንጉሡ ሕመምተኛዋን ባለቤታቸውን በአልጋ እያስጓዙ እርሳቸው ወደ ወሎ ሔደው ፣ ዐመዴ በሺርን ለማደን ከመቅደላ ብዙ ጉዞ አድርገው ፣ የበሽሎን ወንዝ ተሻግረው ግራኝ ሜዳ በሰፈሩበት ሰዓት ሴትዮይቱ ስለ ዐረፉ ፣ ቴዎድሮስ በታላቅ ሐዘን ላይ እንዳሉ ከግራኝ ሜዳ የእቴጌ ተዋበችን ሬሳ ወደ መቅደላ ለመመለስ አስበው ነበር ። የዘመኑ ሁኔታ ደግሞ ንጉሡ ከነሠራዊቱ ባንድነት መኖር ፣ ባንድነት መጓዝ እንጂ አይለያዩም ። ንጉሡ ፣ በተለይ እንደ ቴዎድሮስ ያለው ፣ ከጦር ሠራዊቱ ተለይቶ ቢገኝ ለሕይወቱ አደገኛ ነው ። ከንጉሡ ተለይቶ ረዘም ላለ ጊዜ የቆየ ጦርም ፣ መንፈሱን አንድ ባላንጣ ሰባብኮ ሊያሸፍተው ይችላል ።

በዚህ ምክንያት ፣ አሁን ቴዎድሮስ ጦራቸውን እንዳስከተሉ የተዋበችን ሬሳ ከግራኝ ሜዳ ወደ መቅደላ ሊመልሱ ነው ተብሎ ሲወራ ፣ ወታደሩም ከብቱም በዚህ ወቅት በተነሣው ረኃብ ተበሳጭቶ ማንገራገሩን ሲሰሙ ፣ ቴዎድሮስ የወታደሩ ችግር ስለ ተሰማቸው ወደ መቅደላ የመጓዙን ነገር ከተነሡ በኋላ እርግፍ አድርገው በመተው ፣ የእቴጌይቱን ሬሳ በሣጥን አድርገው ከጓዝ ጋር ባለው የድንኳን ቤተ ክርስቲያን አስቀመጡት ። ንጉሡም እቴጌይቱ ከታመሙበት ጊዜ ዠምሮ ጥሬ ሽምብራ እየተመገቡ አዳራቸውም በጸሎት ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደ ነበረ አለቃ ዘነብ ጠቅሰውታል ።

* በዛሬ አነጋገር ወረሂመኑ



የሆነ ሆኖ ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ ከራሳቸውም ፣ ከቤተሰባቸውም ዕረፍትና ሰላም ያገራቸው አንድነት ፣ የማዕከላዊው መንግሥታቸው ጽናት ስለ በለጠባቸው የሚወዷቸውን ፣ ክፉውንና ደጉን ፣ መከራውንና ደስታውን ሲካፈሉዋቸው የኖሩትን የባለቤታቸውን ሬሳ እንደ ያዙ ፣ ሁለት ወር ሙሉ አገር ላገር እየዞሩ ዐመዴ በሺርን ሲያሳድዱ ቆይተው በመጨረሻ በጥቅምት 11 ቀን 1851 ዓ. ም. ግሸን ማርያም ወስደው ባማረ ፍታት ደጀ ሰላሙ ውስጥ አስቀበሩዋቸው ።(*)

እቴጌይቱ ላፄ ቴዎድሮስ ሲናደዱ እንደ እናት መክረው ፣ እንደ ገረድ ሠርተው የሚመግቧቸው የሚስት ጓደኛ ነበሩ ። እንደነሊቀ መኳስ ዮሐንስ የንጉሡ ባለሟል የነበረው ወልዳ ማዬር ንጉሡ በተዋበች እጅ የተሠራውን ካልሆነ በቀር በሌላ ሰው እጅ የተሠራውን እንደማይቀምሱ ፣ የሚጎዳ መጠጥም እንዳይጠጡ ይመክሩዋቸው እንደ ነበረ ገልጾታል ።([1]) ስለዚህ ንጉሡም ይኸ ሁሉ ትዝ ብሏቸው ቀጥሎ ያለውን ገጠሙ ፤

«እስቲ ጠይቁልኝ ርቃ ሳትሔድ
እቴጌ ተዋበች ሚስት ናት ገረድ» (ሚስት ፣ እናት ፣
ገረድ)

ደግሞ በትልቅ ሰው ልጅነታቸውና የንጉሥ ሚስት በመሆናቸው ላይ በእጅ ሥራ በኩል ባለሙያ ስለ ነበሩ ፣ አሁንም የደስታም የሐዘንም ግጥም ለመግጠም ችሎታ ያላቸው ንጉሥ ፣

«እጅግ ሥራ ዐዋቂ ትናንትና ሞተች
መድኃኒቱን ምሳ ታበላኝ ነበረች»

ብለው ገጥመዋል ።

እቴጌ ተዋበች ፣ ዐፄ ቴዎድሮስን ገና ልጅ ካሣ ሲባሉ ካገቧቸው አንሥቶ ፣ ሞት እስኪለያያቸው ድረስ ካጠገባቸው አልተለዩም ። ዕድላቸውም ከባላቸው ጋር የተያያዘ በመሆኑ ፣

* በቅድሚያ ሐይቅ ደሴት ከደጀ ሰላሙ ተቀብረው ቆይተው ነበር ።
1 Ten Years With King Theodore - pp. 78 - 79

ዐፄ ቴዎድሮስ ካያታቸው ከእቴጌ መነን ወይም ካባታቸው ከራስ ዐሊ በተዋጉ ጊዜ ፤ ላባታቸውና ላያታ ቸው አድልተው ከባላቸው ከዐፄ ቴዎድሮስ አልተለዩም ።

ነገር ግን ፤ እቴጌ ተዋበች ምንም እንኳ ካባታቸው ባላቸውን መርጠው ቢቀመጡ አስፈቅደውም ቢሆን ፤ በስውርም ቢሆን የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እየጠየቁ አሉበት ድረስ ይልኩላቸው ነበርና ፤ አባታቸው ራስ ዐሊ የልጃቸውን ሞት በወሎ በረሃ እንዳሉ በሰሙ ጊዜ ፤ መሪር ሐዘን አዝነው ቀጥሎ ያለውን የልቅሶ ግጥም ገጠሙ ።

«ጠጅ አማረኝ ስላት ማሩን ታስጭናለች
ራብኝም ስላት እህሉን ታስጭናለች
በረደኝም ስላት ሸማ ትሰዳለች
ሌባዩ ተይዛ ባልጋ ትሔዳለች
የት አባቷን ዐውቃ ታሳዝነኛለች ።
የጣቴን ቀለበት አንተ አድርገው ካሣ
በኔማ ጣት (በኔ ማጣት) ገብቶ አስጨነቀኝሳ »(1)

1 አለቃ ዘነብ.........ገጽ 36—37 ፤ አለቃ ወልደ ማርያም ገጽ 21—22 አለቃ ዘነብ የእቴጌ ተዋበችን ሞት ከሰይፉ ጦርነት በፊት አስ መስለውታል ። ወልደ ማርያምና ብዙ ጸሐፊዎች ከሸዋ መልስ አድርገው ጽፈውታልና መሠረት ያደረግነው ይኸንኑ ነው ።



# ምዕራፍ ዐሥራ ሰባት

## የሣልሳይ ዮሐንስ ዕድል ፤ ለናፖሊዮን ሣልሳይ የጻፉት ደብዳቤ

ምንም እንኳን የንጉሡ ነገሥትነት ሥልጣናቸው በነራስ ዐሊ ቢገፈፍም ፤ ለዐፄ ቴዎድሮስ የነጋሢነት አባት ዐፄ ዮሐንስ ሣልሳይ ናቸው ። የዮሐንስም ዘር ከላይ ከጐንደር ነገሥታት በቀ ጥታ የመጣ ነው ። አወራረዱም ባንድ መሥመር ከዚህ እንደሚ ከተለው ይሆናል ።

ዐፄ ፋሲል ፤ ዐፄ ዮሐንስ አንደኛን (ጻድቁን) ዮሐንስ ዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድን ፤ ኢያሱ ዐፄ በካፋንና ዐፄ ዮሐንስ ሁለ ተኛን ፤ ዮሐንስ ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስን ፤ ተክለ ጊዮርጊስ እኝህን ዐፄ ዮሐንስ ሣልሳይን ይወልዳሉ ። በዘመነ መሳፍንት የድብል ቅልቅ ዘመን አንዱ መስፍን ሲያነግሣቸው ፤ ሌላው ሲያባርራ ቸው አባታቸው ተክለ ጊዮርጊስ ስድስት ጊዜ ወደ ዙፋን ከወጡ በኋላ ፤ ስድስት ጊዜ ከዙፋን ተባርረዋል ። ግዕዝኛው መጽሐፍ «ተፍጻሚተ መንግሥት ተክለ ጊዮርጊስ» ይላቸዋል ።

አሁን ደግሞ ፤ የራስ ዐሊ እናት ወይዘሮ መነን ከልጃቸው ከራስ ዐሊ ጋር በመስማማት ፤ የእቴጌነት ዘውድ ለመድፋት ሲሉ በዙፋን የነበሩትን ዐፄ ሣህለ ድንግልን አባረው ፤ ዮሐንስን በዙ ፋን አስቀምጠው እንደ አነገሡዋቸው ባለፈው አንብበናል ። ከዚያ ወዲህ ባልና ሚስቱ ስምምነት ስለአጡ ፤ ዮሐንስ በቅያሜ ስሜን ወደ ደጃዝማች ውቤ ዘንድ ሔደው እንደ ተቀመጡ ውቤና ዐሊ በመካከሉ ሲታረቁ ዮሐንስም ተመልሰው ከባለቤታቸው ከእቴጌ መነን ጋር በስምምነት ተቀመጡ ። ቀጥሎ መነንም ፤ ዐሊም በደጃዝማች ካሣ ተሸንፈው በነበሩበት ጊዜ ዮሐንስም ከተሸና ፊዎቹ ጋር ትንሽ ጊዜ እንደ ቆዩ ከነዚያ ተለይተው ለብቻቸው ተቀመጡ ።

ዐፄ ቴዎድሮስ በጳጳሱ በአቡነ ሰላማ ተቀብተው ሲነግሡ ከበዓሉም ሳይካፈሉ ፥ ከጳጳሱም ጋር ሳይገናኙ ገርበብ ብለው ለብቻቸው በተቀመጡበት ጊዜ ፥ «ከኔ አባት (ከአቡነ ሰላማ) ጋር ለምን አይተባበሩም ? እስከ አሁንስ ለምን ሔደው ሳይገናኙዋቸው ቆዩ ?» የሚል ተግሣፅ ከቴዎድሮስ ስለ ደረሰባቸው ፥ በፍርሃት ጭምር ከዕጨጌ ወልደማርያምና ከቄስ ዐፄ ገብረ መድኅን ጋር ሔደው ከጳጳሱ ጋር ተገናኙ ።(1)

የሆነ ሆኖ ፥ አንድ ጊዜ ዘውድ ደፍቶ በይፋ የነገሠ ሰው ከዙፋን ወርዶ ከቤተ መንግሥት ከተባረረ በኋላ አኗኗሩ አስቸጋሪ ይሆንበታል ። እዚያው የነጋሢ ዘሮች በግዞት የሚቀመጡበት ወህኒ አምባ ሆኖ በድርጎ ካልኖረ በቀር እንደ ልቡ ማናቸውንም ሥራ ሠርቶ ፥ ትምህርትም እንደ አለው እንደ ተራ ካህን እቤተ ክህነት ገብቶ እያገለገለ ወይም ገበሬ ሆኖ እያረሰ ፥ ነጋዴም ሆኖ እየነገደ መኖር አይችልም ። ይኸን ቢያደርግ ትርፉ የተመልካች መሣቂያና መሣለቂያ መሆን ነው ።

በዚህ ምክንያት ፥ ዕድለ ቢሱ ሣልሳይ ዮሐንስ ቀደም ባለው ጊዜ በቤገምድርም ፥ በትግሬም ከነበሩት በተለይ ከሞንሲኞር ደጃኮቢስና ከነአባ ገብረ ሚካኤል ፥ ዕውቂያ ነበራቸውና በነርሱና በፈረንሣዮች ምክር ተመርተው የእርዳታ ገንዘብ ለመለመን ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ለፈረንሣዊ ንጉሠ ነገሥት ለናፖሊዮን ቦናፓርት (ሙሉ ስሙ ሻርል ሉዊ ናፖሊዎን ቦናፓርት) እንደዚህ ሲሉ ጽፈዋል ።

«ዛቲ ጦማር ዘተፈነወት እምኀበ ንጉሥ ዮሐንስ ፤ ትብጻሕ ኀበ ንጉሥ ሉዊ ናጶልዮን ፤ እንዴት ነዎ ? ደህና ነዎን ? እግዚአብሔር በቸርነቱ ባባቴ መንግሥት አስቀምጦኝ ነበረ ። ኋላ ግን ፈቃዱ ባይሆን ሻረኝ ። ዛሬ ተቸግሬ ተቀምጨአለሁ ። ምግቤን እንደ ተቻለዎ ይርጠቡኝ ። በኛ አገር ሥራት ንጉሥ ከተሻረ በኋላ ከቤቱ ይቸገራል እንጂ ፥ ከሰው ቤት አይሔድም ፥ ተርቤ አለሁ ። ይኸንን ያስላከኝ ምክንያት የየሱስ ክርስቶስ ፥ የእግዚእትነ ማርያም ልጆች ከሆነ (ከሆንን) አንድ ነን ብዬ ነው እንጂ ከዚህ ቀደም መተዋወቅ (ዕውቂያ) ኖሮኝ አይደለም ።

እግዚአብሔር ይዕቀብከ ተ አሜን»(2)

1 Vieende Dell' Ethiopia E Delle Missioni Catoliche Al Tempi Di Ras Ali......... Conti - Rossini - pp. 29. 31, 40. 42.

2 Correspondence and Treaties 1800 - 1854 Edited by Jenven Rubenson Document no. 185 p/248.



ደብዳቤው ቀንና ዓ. ም. አልተመለከተበትም ። ፕሮፌሰር ሩበንሰን እንደ አውሮፓ አቆጣጠር 1854 ዓ. ም. ላይ መድበውታል ። ይኸም በኛ ወደ 1847 ዓ. ም. ላይ ይሆናል ። ይኸወም ማለት ዐፄ ቴዎድሮስ በነገሡ በሁለተኛው ዓመት መሆኑ ነው ። ይኸም ዓመት ዐፄ ቴዎድሮስ የማሳመን ፊታቸውን ወደ ወሎና ወደሸዋ የመለሱበት ዓመት ነው ። ለዚህም ደብዳቤ ናፖሊዮን ሣልሳይ መልስም መስጠቱ ፥ እርዳታ መላኩም ተመዝግቦ አልተገኘም ።